# ኀምሌት

ከዊሊያም ሼክስፒር

ጸጋዬ ገብረ መድኅን
እንደተረጐመው



# ኀምሌት


ዊሊያም ሼክስፒር

እንደጻፈው



የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ቤተ መጻሕፍት
ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES



ጸጋዬ ገብረ መድኅን

እንደተረጐመው



ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

፲፱፻፷፪ ዓ.ም.

አዲስ አበባ

OXFORD UNIVERSITY PRESS, ELY HOUSE, LONDON W. 1.

*Glasgow New York Toronto Melbourne Wellington*
*Cape Town Ibadan Nairobi Dar es Salaam Lusaka Addis Ababa*
*Delhi Bombay Calcutta Madras Karachi Lahore Dacca*
*Kuala Lumpur Singapore Hong Kong Tokyo*

OXFORD UNIVERSITY PRESS, P. O. Box 1024, ADDIS ABABA, ETHIOPIA

# HAMLET

© OXFORD UNIVERSITY PRESS 1972

መብቱ ፡ በሕግ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
በ፵፪ኛ ዘመነ መንግሥት ታተመ ።

Printed by Commercial Printing Press
and
Published by Oxford University Press

LIBRARIES

# ማ ው ጫ


መግቢያ ... መ

ተዋንያኑ ... ሰ

የድርጅቱ ጓድ ... ሸ

የየባሕርዩ ተዋንያን መለዩ ... ቀ

ገቢር አንድ ... ፩

ት ፡ ፩ ... ፩

፪ ... ፫

፫ ... ፲፪

፬ ... ፲፭

፭ ... ፳፩

ገቢር ሁለት ... ፳፱

ት ፡ ፩ ... ፳፱

፪ ... ፴፫

ገቢር ሦስት ... ፶፭

ት ፡ ፩ ... ፶፭

፪ ... ፶፭

፫ ... ፷፯

፬ ... ፷፱

ገቢር አራት ... ፹፭

ት ፡ ፩ ... ፹፭

፪ ... ፹፭

፫ ... ፺፩

፬ ... ፺፫

፭ ... ፺፯

፮ ... ፻፪

፯ ... ፻፬

ገቢር አምስት ... ፻፱

ት ፡ ፩ ... ፻፱

፪ ... ፻፳፪

# ኀምሌት

ከማክቤዝ በኋላ ፥ የከርሞ ሰውን በአማርኛ ፥ የወርካ ሥር ንግር ትን ፥ በእንግሊዝኛ ጻፍኩ ። የኀምሌትን ትራጀዲ ወደ አማርኛ የተረጐ ምኩት ፥ ወይም አዳፕቴሽን እንደሚሰኘው ቋንቋው በቋንቋ የተመ ለሰው (የተዳቀለው) ፥ በ፲፱፻፶፯ ዓ ም በክረምት ወራት ፥ እሥራኤል ሆኜ ነው ። መልካም ተሰጥዎአቸውን ፥ ጊዜአቸውንና ትዕግሥታቸውን በመ ለገሥ ዝግጅቱን እንድመራና ለሕዝብ እንዳቀርብ ላበቁኝ የኀምሌት ዝግጅት ክበብ አባሎች ዕድሜ ይስጥልኝ ማለቴን እያስቀደምኩ ፥ ከተ ተረጐመ ከሁለት ዓመታት በኋላ ኀምሌት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትር ሊታይ በቃ ።

በቪተንበርግ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ቤት ሕይወት ውስጥ አእ ምሮ ልቦናው በምርምር የተመሰጠ ጐልማሳው ልዑል ኀምሌት ፥ ያረ ጋዊ አባቱን ድንገተኛ ሞት እንደተረዳ ፥ ኤልሲኖር ወደሚሰኘው የም ድረ-ዴን ቤተ መንግሥት በርግጎ ገሠገሠ ። አጎቱ ገላውዴዎስም የኀ ምሌትን እናት ፥ መንፈሰ ደካማይቱን ንግሥት ገርትረድን አግብቶ ዘውዱን በመሠሪ ጭኖ ፥ ኀምሌትን በጽኑ ያይን ቁራኛ አስጠበቀው ።

ኀምሌት ፥ ከሰቀቀኑ ፋታ በተነፈገበት ሰዓት ፥ ብቸኛ ልቡን ለአፈ ንጉሡ ለጶሎኔዎስ ሴት ልጅ ፥ ለውቢቱ ለወይዘሪት ሆይ ወፌ-ይላ ፥ በፍቅር ከፈተላት ። ወጣቷ ወፌ-ይላም በጮርቃ ስሜቷ መሸበር እንጂ ከኀምሌት የመንፈስ ድቀትና ግለኛ ባሕሪ ትካዜ ጋር ስላልተመጣጠ ነች ፥ ከቶውኑ ሊግባቡ አልቻሉም ። በተጨማሪም አፈ ንጉሥ አባቷና ዓለመኛ ወንድሟ ልጅ ላርቶስ ፥ በኀምሌት የደረጃ ከፍተኛነት እያሳ በቡ የፍቅር ስሜቷን ስላጥላሉባት ፥ መራራቃቸው ጠና ።

ወዲያውም ፥ ደገኛው የኀምሌት ጓደኛ ፥ ሆራትዮስ ፥ የሟች አባት ክን ጣዕረ መንፈስ ከሌሎች የመቃብር ቤት ዘበኞች ጋር አየነው ብሎ ስለሚነግረውና ኀምሌትም ማታውኑ ሄዶ ስለሚፋጠጠው ፥ ጣዕረ መን ፈሱ ራሱ ፥ የሞትኩት በወንድሜ በአጎትህ በገላውዴዎስ እጅ ነው ብሎ ያዋየዋል ። ደሙንም እንዲበቀል ገዝቶ ያስምለዋል ።

ያረጋዊ አባቱ ጣዕረ መንፈስ በሚያሰቅቅ ሁናቴ ከተማፀነው በኋላ ፥ ኀምሌት ልቦናው እንደተሰለበች ተመስሎ ፥ የታወከች መንፈሱን በግለኛ ምሥጢር ፥ ለበቀል ያቅድባት ጀመረ ። ምንም አፈ ንጉሥ ጶሎ ኔዎስ የኀምሌትን ባሕርይ መሸበር በልጁ በወፌ-ይላ ፍቅር ሳቢያ ነው ብሎ ቢሞግት ፥ ተጠራጣሪው ሴረኛ ንጉሥ ገላውዴዎስ ሐሳቡ ዕረፍት

አላገኘምና ፣ የልዑሉን የትምህርት ቤት የቅርብ አብሮ አደጎች ፣ ሮዘ ንቅሮስንና ገድለ ስምዖንን ይገዛበትና ፣ እንዲነግሩበት በጎን ይልካቸ ዋል ። በዚሁኑ ጊዜ የኀምሌት ወዳጆች የሆኑ ተዘዋዋሪ የቴአትር ቢነ ጥበብ ተዋንያን ወደ ኤልሲኖር ቤተ መንግሥት ስለሚመጡና ፣ ከአባቱ አገዳደል ጋር እጅግ የሚመሳሰል አንድ የሮማዊ ትራጀዲ በኀ ምሌት የቴአትር ዝግጅት መሪነት ለንጉሡ ስለሚቀርብ ፣ የግፉ ወቀሳ በገዛ ሕሊናው ላይ ያተኮረበት አጎቱ ገላውዴዎስ ፣ በደሉ የተገለጠ ስለመሰለው ፣ በትርኢቱ ጊዜ በርግጎ ይነሳና ተንደርድሮ ይወጣል ። ያባቱ ገዳይ አጎቱ መሆኑን አሁን ያለጥርጣሬ የተገነዘበውም ኀም ሌት ፣ ገላውዴዎስ ይጸልይበት በነበረ ሰዓት ለብቻ አግኝቶ ሊገድለው ከቃጣ በኋላ ፣ በጸሎቱ ላይ አልገድለውም የሚል የፈላስፋ ባሕርዩ አሸንፎት ከመሠንዘር ይቆጠባል ። ወዲያው እናቱ ንግሥት ገርትረድ ኀምሌትን ወደ መኝታ ክፍሏ አስጠርታ በጋጠ ወጥ ተግሣፅዋ ልት ፈታተነው ስትሞክር ፣ ልዑሉ በቁጣ አንደበት ከንቱነቷን ዘርዝሮ ስለ ሚጋተራትና ሲቃ ተናንቋት ስለምትጮህ ፣ አንድ ተደብቆ ያዳምጥ የነበረ ሰው ኡኡታውን እንዳስተጋባ ፣ ኀምሌት ፣ አጎቱ ሊሰልለው ያደፈጠ ስለሚመስለው ሳንጃውን መዞ መጋረጃው ውስጥ በተሸሸገው ሰው ይሸጥበትና ፣ ጶሎኔዎስን ሳያውቅ ይገድለዋል ።

ያባቱም ጣዕረ መንፈስ ድንገት ይመለስና የበቀሉን መሃላ እን ዳይዘነጋ ከነገረው በኋላ በናቱ ላይ ግን እጁን እንዳያነሳ ያሳስበዋል ።

ቀጥሎ ፣ ንጉሡ ኀምሌትን ባድራጎቱ ካወገዘው በኋላ ፣ በሮዘን ቅሮስና በገድለ ስምዖን ያይን ቁራኛ ወደ እንግሊዝ ምድር እንዲጋዝ ይፈርድበታል ። ይሁንና ልዑሉ የገላውዴዎስን ሴራ ስለጠረጠረና ፣ ማዘገቡውን ከቁራኛዎቹ ጥብቅ በድብቅ ወስዶ ባነበበ ጊዜ ፣ እንግ ሊዝ ምድር እንደደረሰ መገደሉን የሚያዝዝ መሆኑን ተረዳ ። ወዲ ያው ሌላ ማዘገቡ አዘጋጅቶ ፣ ሁለቱ ገሮ ጠቢዎች እንዲገደሉ የሚል ፊርማ ካሠፈረበትና ካኖረላቸው በኋላ ፣ ተሣፍረውበት የነበረውን መርከብ ሌላ የወንበዴ መርከብ ውጊያ በገጠመው ጊዜ ፣ ኀምሌት ቶሎ ወርዶ ወደ ምድረ-ዴን ወደብ ይመለሳል ። ወደ ሀገሩ ወደብ መመ ለሱንም ለወዳጁ ለሆራትዮስና ለንጉሥ ገላውዴዎስ ይጽፍላቸዋል ።

ይሁንና በኤልሢኖር ቤተ መንግሥት ግቢ ፣ አባቷ ጶሎኔዎስ በምትወደው ልዑል ኀምሌት እጅ ተገድሎ በምሥጢር ከመቀበሩ ሌላ ፣ የኀምሌት ባሕርይ መሳከር ስላወናበዳትና ፣ ለጋ አእምሮና ልቦ ናዋ ስለሚናጋባት ፣ ወፌ-ይላ ቀልቧ ተሰልቦ ባንዲት ኩሬ አዘቅት ተወርውራ ትደፈቅና ትሞታለች ። ችኩልና ግልፍተኛ የነበረ ወንድሚ ልጅ ላርቶስም ፣ ባባቱ ሞት ምክንያት ከፓሪ ዩኒቬርሲቲ ተጠርቶ እንደመጣ ፣ ያባቱን ደም እበቀላለሁ በማለት ወሮበሎች አሳድሞ በንጉሡ ይነሳበታል ። መሠሪው ንጉሥ ገላውዴዎስ ግን ፣ ፉከራ

ውን በብልሐቱ ካቀዘቀዘ በኋላ ፥ ባላንጣህ ኀምሌት ነው በማለት ቁጣና በቀሉን በልዑሉ ላይ ያስጭረዋል ። በቤተ መንግሥቱም ውስጥ ፥ ኀምሌት እንደተመለሰ ፥ ሁለቱ ጐልማሶች በጦር ሥልት የውድድር ግጥሚያ ሲያደርጉ ፥ ላርቶስ መርዝ በሚቀባ ጦሩ ሊያጠፋው እንደሚችል ፥ ዶለቱ ።

ኀምሌት ከሆራትዮስ ጋር ወደ ኤልሲኖር በሚመለስበት መንገድ ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር አጠገብ የወፌ-ይላ ሬሣ ለቀብር መጥቶ ስላየ ፥ በሲቃ ተገፋፍቶ ወደ መቃብር ውስጥ ከገባው ከላርቶስ ጋር ፥ በእዝንተኝነቱ ቀደምትነት ስለሚፈካከሩ ፥ ይጣላሉ ። ወዲያው ላርቶስ ኀምሌትን በጦር ስልት ውድድር ግጠመኝ ብሎ ስለሚልክበት ልዑሉ ውድድሩን እቀበላለሁ ሲል ይመልስለታል ። በግጥሚያውም ጊዜ ፥ ገላውዴዎስ ቀምሞለት የነበረውን የመርዝ መጠጥ ሳይቀምሰው ስለዘገየና ፥ ንግሥቲቱ ግን ባለማወቅ ስለምትጐነጨው ፥ ትሞታለች ። ላርቶስም ፥ ምንም አስቀድሞ ኀምሌትን በመርዛም ጦሩ ቢወጋው ፥ በትግላቸው ጊዜ ጦራቸው ተቆላልፎ ስለሚወድቅና ጦር ለጦር ስለሚለዋወጡ ፥ ኀምሌትም መልሶ በመርዛሙ ጦር ይወጋውና ሁለቱም ይበከላሉ ። ላርቶስም በሞት ሲያጣጥር ፥ ንግሥቲቱ በስህተት ጠጥታ የወደቀችውን መርዝ የቀ[illegible]ና ፥ ሁለቱም የተበከሉበትን መርዛም ጦር የነከረ ንጉሡ መሆኑን ስለሚናዘዝ ፥ ኀምሌት ሴረኛውን ገላውዴዎስ እዚያው ይገድለዋል ። የልዑሉ ወዳጅ ሆራትዮስም ፥ ከመርዙ ዋንጫ ተጐንጭቶ ከኀምሌት ጋር ሊሞት ቢሻም ፥ ሙሉ ስሜም ከኔ ጋር እንዳትጠፋ ቆይና አጽዳት ብሎ ከገዘተው በኋላ ፥ ወዲያው ይወድቃል ።

ቀደም ብሎ ያባቱን ግዛት ዳር ድንበር ለማስከበር በምድረ-ዴን አልፋለሁ ይል የነበረው የኖርዌይ ልዑል ፎርጠንብሮስ ድንገት ስለሚደርስ ፥ ኀምሌትን በሥርዓት ያስቀብርና ፥ ባዶውን አልጋ ሊወርስ ይዘጋጃል ።

* * *

በሼክስፒር ትርጉሞቼ ውስጥ ፥ አንዳንድ የኦሮሞና የኩሽ ሥርወ ቃላትን ፥ ለምሳሌ እንደ 'ሴራ' ፥ 'ቃልቻ' ፥ 'ቦረንቲቻ' ወዘተ. ያሉትን የተጠቀምኩባቸው ፥ እንደ ቀደምት መሠረተ አስተሳሰባቸው ሳይሆን ፥ ወደ አማርኛ በተመለሱበት ጊዜ በተቀየሩበት አስተሳሰባቸው መሆኑን ለአንባቢያን እገልጻለሁ ።



# ተዋንያኑ

በመጀመሪያው የኀምሌት ዝግጅት የቴአትር ኪነ ጥበባት አማተር ክለብ ጊዜ ፥ የየባሕርዩና የድርጅቱ ተካፋይ ሆነው የሠሩትን ተዋንያንና ሞያተኞች ከምሥጋና ጋር ፥ ለአንባብያን ላስታውሳቸው እወዳለሁ ።

| | |
|---|---|
| ተስፋዬ ገሠሠ | —እንደ ልዑል ኀምሌት |
| ቫዮሌት ዛኪ | —እንደ ወይዘሪት ሆይ ወፌ-ይላ |
| ተስፋዬ ተሰማ | —እንደ ንጉሥ ገላውዴዎስ |
| ወንድ ወሰን ገብረ የሱስ | —እንደ አፈ ንጉሥ ጶሎኔዎስ |
| ሶሎሞን ዴሬሣ | —እንደ ኀምሌት አባት ጣዕረ መንፈስ |
| ኃይሉ ገብረ ማርያም | —እንደ ሻቃ ሮዘንቅሮስ |
| ሰዋሰው ጥዑመ ልሣን | —እንደ ንግሥት ገርትሪድ |
| ውብሸት ወርቅ አለማሁና | —እንደ ተረበኞቹ መቃብር ቆፋሪዎች |
| ጌታቸው ደባልቄ | |
| ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር | —እንደ ጌታ ሆራትዮስ |
| ዓምደ ሚካኤል ሃብቴ | —እንደ ልጅ ላርቶስ |
| ነጋሽ ዘለቀ | —እንደ ልዑል ፎርጠንብሮስ |
| ጐሹ አበበ | —እንደ ዚቀኛው ተዋናይ ንጉሥ |
| አስቴር ሞገስ | —እንደ ተዋናይት ንግሥት |
| ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ | —እንደ ባልደራስ ክልሉ |
| ኃይሌ ገሪማ | —እንደ ባሻ ገድለ ስምዖን |
| ኢዩኤል ዮሐንስ | |
| ዓለማየሁ ፋንታ | |
| ምኒልክ ወስናቸው | —እንደ ሊቀ ዲያቆናት መዘምራን |
| ፍሬው ኃይሉ | |
| ተሾመ ኃብተ ማርያም | |
| መርዕድ ቅጣው | —እንደ ሐተታ አንባቢው |
| ለማ ወርቄ | —እንደ መርከበኛው መልእክተኛ |
| አበበ ይመኔ | —እንደ ቄሰ ገበዙ |
| መኰንን አመና | —እንደ እልፍኝ አስከልካይ |
| ታደለ ገብረ ሕይወት | —እንደ ፍኖቴዎስ |
| ወንድሙ ቶላ | |
| ጥላዬ ገብሬ | |
| አበራ ፈይሳ | —እንደ ቤተ መንግሥት ቋሚ አሽከሮች |
| መልካሙ ተበጀ | |
| ብሩክ ከበደ | |

# የድርጅቱ ጓድ

| | |
|---|---|
| የመድረክ ሥራ ድርጅት | አብርሃም ተክለ ሃይማኖት<br>በቀለ የሻው<br>ጥበቡ ካሣዬ<br>መኰንን ገብረ እግዚአብሔር |
| የድምፅና የአማካይ ሙዚቃዎች | —መኰንን ወልደ ሚካኤል |
| ቅርጽ | —ኃይሉ ደጀኔ |
| የመብራት ተቆጣጣሪ | —ፋኑ እስክንድር ቦጉሲያን |
| የልብስና የገጽ ቅብ ተቆጣጣሪ | —አዳነ ደርሰህ |
| የዕቃ ተቆጣጣሪ | |
| የዝግጅቱ ሥራ መሪ ረዳቶች | ኃይሉ ገብረ ማርያም<br>ሙሉጌታ መክብብ<br>ተስፋዬ ተሰማ<br>ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ<br>ለማ ወርቄ |

በሐምሌ ወር ፲፱፻፷ ዓ ም ከሼክስፒር ታላላቅ ትራጀዲዎች ውስጥ የተፈቀዱልኝን ምርጥ ትዕይንቶች ባቀረብሁበት ጊዜ ፣ ወጋየሁ ንጋቱ እንደ ልዑል ኀምሌት ፣ ደበበ እሸቱ እንደ ዚቀኛው ተዋናይ ንጉሥ ፣ አስለፈች በቀለ እንደ ወይዘሪት ሆይ ወፌ-ይላ ሆነው መታየታቸውን ፣ ዳግም ከምሥጋና ጋር ላንባብያን ላስታውስ እወዳለሁ ።



# የየባሕርዩ ተዋንያን መለዮ

| | |
|---|---|
| ገላውዴዎስ | —የምድረ-ዴን ንጉሥ |
| ኀምሌት | —የቀድሞው ንጉሥ ልጅ |
| ጶሎኒዎስ | —አፈ ንጉሥ (ባለሟል) |
| ገርትረድ | —የምድረ-ዴን ንግሥት (የኀምሌት እናት) |
| ሆራትዮስ | —የኀምሌት አሽከርና ወዳጅ |
| ላርቆስ | —የጶሎኒዎስ ልጅ |
| ፍኖቴዎስ<br>ቆርነሌዎስ<br>ገድለ ስምዖን<br>ሮዘንቅሮስ | —ባለሟሎች |
| ባልደራስ ክልሉ | —የፈረስ ጉግሥ ሥርዓትና የጦር ስልት አዋቂ |
| ፍራንቺስኮስ<br>መርቆሬዎስ<br>ቤርናርዶስ | —ዘበኞች |
| አንድ ቄስ | —ንስሐ አባት (ቄሰ. ገበዝ) |
| ምእመኑ | —የጶሎኒዎስ አሽከር |
| ወፌ-ይላ | —የጶሎኒዎስ ሴት ልጅ |
| ተዋንያን | |
| መቃብር ቆፋሪዎች | |
| ፎርጠንብሮስ | —የምድረ ኖርዌይ ልዑል |
| የፎርጠንብሮስ ባልደራስ | |

የኀምሌት አባት ጣዕረ መንፈስ (ጣዕረ መለኮት)

መርከበኛ መልእክተኞች

መኳንንት ፣ ወይዛዝርት ፣ መኰንኖች ፣ እልፍኝ አስከልካይ ፣ አጋፋሪዎች ፣ ቋሚ አሽከሮች ።

ለላቂ ቤተው

LIBRARIES

# ገቢር አንድ

## ት*፡ ፩

—በአንድ የምድረ ዴን ቤተ ክርስቲያን የመቃብር ቅጥር አካባቢ ሁለት ዘበኞች ቤርናርዶስና ፍራንቺስኮስ ይታያሉ—

ፍራንቺስኮስ
ማነህ ቁም !

ቤርናርዶስ
ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ገላውዴዎስ !

ፍራንቺስኮስ
አንተ ነህና ቤርናርዶስ ።

ቤርናርዶስ
ነኝ ።

ፍራንቺስኮስ
እኔ ደሞ ያ የመጣብኝ መስሎኝ ልቤ ተመነጠቀ ።

ቤርናርዶስ
እኩለ ሌሊት ሆኗል ፤ ተራህን እንድትተኛ ልቀይርህ መምጣቴ ነዋ ፤ ያም ሆነ ይኸ ጭንቀቱ እንቅልፍ አልሰጠኝም ። ያው መርቀሬዎስ ሆራትዮስን ይዞት መጣ መሰለኝ ።

—መርቀሬዎስና ሆራትዮስ ይገባሉ—

መርቀሬዎስ
ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ገላውዴዎስ ፤ . . . እኛ ነን ፍራንቺስኮስ ።

ፍራንቺስኮስ
ከሩቅ አወቅናችሁ ፤ ለመሆኑ ጌታ ሆራትዮስ በጄ ብሎ መጣልህ በል ?

መርቀሬዎስ
እንደምንም መጥቷል መችም ። ትንግርት ዓይን አወጣ ቢባል የናንተ ወሬ ነው ይላል ። መሆኑን ከመሸ ይኸ ነገር አልመጣባችሁም ጉበዝ ?

* ት ፡ ትዕይንት

ቤርናርዶስ

የዛሬንስ ሌሊት ተመስገን ሊታረቀን ነው መሰለኝ ። እንዴት ሰነ
በትከ ጌታዬ ።

ሆራትዮስ

እንደምነህ ቤርናርዶስ ፤ ፍራንቺስኮስ እንደምነህ ። ደሞ የምን ምጣት
አመጣችሁ በሉ?

መርቆሬዎስ

ምጣት አልከው? እኔ ጌታዬ ምኑንም ምንም ብዬ አልሰይመውም ፤
በመጣ ባልመጣ ቁጥር ተመንጥቄ ማበዴን እንጂ ፤ . . . እግዚኦ . . .
እግዚኦ . . . ለማን እግዚኦ ይባላል ?

ቤርናርዶስ

በደረቅ ሌሊት ድንገት ፣ ብቅ ሲል ልሣንም ድርቅ
ወኔም ጉረሮዋን ታንቃ ፣ ማለት እንጂ ክችች ሕቅ
እሱ እንደሁ ዶሮ ካልጮኸ ፣ ዝር አይል ጎህ ሳይፈነጥቅ ፤
ይኸነዜ ትላንት ሌሊት . . . .

መርቆሬዎስ

ቆይ

ፍራንቺስኮስ

ቆ - ቆ - ቆ - ቆ - ቆይ . . . .

—የሟቹ የዴን ንጉሥ የልዑል ኀምሌት አባት ጣዕረ መንፈስ ይገባል—

ቤርናርዶስ

ያ - ያ - ያ - ያውልህ . . . .

ሆራትዮስ

ቆ - ቆይ ።

መርቆሬዎስ

አ - አ - አነጋግረው . . . ማ - ማ - ማነህ በለው ሆራትዮስ . . . .

ሆራትዮስ

ቁ - ቁ - ቁም ! - - - - በ - በአብርሃም በ- በይስሐቅ ጌታ . . . .
ቁ - ቁም !

ቤርናርዶስ

ሟቹን ንጉሥ . . . የኀምሌትን አባት ቁ - ቁርጥ . . . .

ሆራትዮስ

ቁ - ቁም ! ማ - ማነህ ምንድነህ ተ- ተናገር ! . . .

—ዶሮ ይጮሃል ። ጣዕረ መንፈስ ይወጣል—



# ት ፡ ፪

—በምድረ ዴን የኤልሲኖር አዳራሽ ውስጥ ንጉሥ ገላውዴዎስ ፣
ንግሥት ገርትሪድ ፣ ልዑል ኀምሌት ፣ አፈ ንጉሥ ጶሎኔዎስ ፣ ልጅ ላርቆስ ፣ ባለሟሎችና
አጋፋሪዎች ይታያሉ—

ንጉሥ

በግርማዊ ወንድማችን ፣ ድንገተኛ ሞት መቀጠፍ
ቅስማችን በሐዘን ሲገረፍ
ቁስሉ እስከ ወዲያኛውም ፣ በልቦናችን ሲነደፍ
ዳር እስከ ዳር ግዛታችን ፣ በዋይታ ዓዋጅ ስትመታ . . . .
ግና የተግባር ግዴታ
በእንባ ስለማትገታ ፣
ልቅሶአችንን በመጽናናት ፣ እግበናችን ሥር ቋጥረን
ፍቅሩም ፍቅራችን መሆኑን ፣ ተገንዝበን አስገንዝበን
የተፈጥሮና የጊዜን ፣ ፍቃድ እንቀበላለን ።
እና እስከዛሬ ድረስ ፣ የሟቹ ወንድማችን ሚስት
የነበረችይቱን ንግሥት
ሕገኛ ባለመብቲቱን ፣ ለዚህ ጦር ላሳሳው መንግሥት . . . .
የፍስሐችን ፈገግታ ፣ ለሐዘን ግንባር ገብሮ
አንድ ዓይን የሳቀ ቢመስል ፣ ሌላው በእንባ ወዝ ተቋጥሮ
ባክፋይ ምሳ እንዳመቁት ምርቅ
መከራና ደስታችን ፣ ባንዲት ጀንበር ላይ ብትወድቅ
ሁለቱንም አነጻጽረን ፣ ተከታትለው እንዲውሉ
ብንወስናቸውም ቅሉ ፣
ልባችን ከቀብሩ ሥርዓት ፣ ተግባራችን ከተክሊሉ
መሆኑንም አስተውሉ ፤ . . . .
ታድያ እናንተም በዚህ ጉዳይ ፣ በሃሳብ እንደምታብሩ
ለሀገር ነውና ዕድሩ
የግብረ አበርነታችሁ ፣ መታመን ነው ምስክሩ ።
ከዚህ ጉዳይ ጋር አስታክከን ፣ በየልቦናችሁ ማኀደር
የኖርዌይን መስፍን ድፍረት ፣ እንፈቅዳለን ለማሳደር ፤
በፎርጠንብሮስ በልጅ አፍ ፣ ዴን አትዘልቅም ተሰድባ
በዚያ በአፍላ ኰበሌ ፣ ምራቁን ባልዋጠ ጉርባ ፤
የጦር ኃይላችንን ንቆት ፣ አቅማችንን ገምቶት
በወንድማችን ሞት ሳብያ ፣ የተነጣጠልን መስሎት
የኔ ነው የሚለው ግዛት ፣ የሱ አለመሆኑን አጥቶት

ሟቹ ጀግናው ወንድማችን ፡ አባቱን ፉክክር ገጥሞት
በጕበዝ ወግ አሸንፎት
በጕግሥ ሥርዓት ገድሎት
በሕግ መርታቱን ረስቶት . . . .
የልቡ ልብ ደንድኖ ፡ የድፍረት ድፍረት ደፈረን
ነጋ ጠባ በደብዳቤው ፡ በነገሩ አሰለቸን ።

—ፍኖቴዎስንና ቆርነሌዎስን የእልፍኝ አስከልካዩ ያስገባቸዋል—

እና ይኸን ማስጠንቀቂያ ፡ ለሕመምተኛ አጎቱ
በእጃቹ እንዲሰጡልን ፡ ይሂዱ እኒህ ሁለቱ ፤
ውርድ ከራሳችን እንጂ ፡ ባይመከር ጦር ክተቱ ። . . . .
የፎርጠንብሮስን ትዕቢት ፡ አጎቱማ ከየት አውቆ
በአልጋ ቁራኛ ተይዞ ፤ በእግዜር ደዌ ተጠብቆ ፤
እስከዚህ መንጠባረሩን ፡ በኩራት ሞራ ታፍኖ
ካባቱ የረታነውን ፡ ዐፅመ ርስቴ ነው ብሎ አምኖ
አሥራትና እርቦ ሊቃረጥ ፡ መታጠቁን ያ አላወቀም
እንግዲህ ለማናቸውም ፡ እስቲ እናያለን ግድ የለም ።
አሁን እናንተ ሁለታችሁ
ሌትና ቀን ገሥግሣችሁ
ያንን ሕመምተኛ አጎቱን ፡ ሞት ሳትቀድመው ቀድማችሁ
ይኸንን ወጅባራ ጉርባ ፡ እንዲያስጠነቅቅ ነግራችሁ
እንድትሰጡት እንካችሁ ።
በተጨማሪም ደብዳቤው ፡ የልዑካን አቋማችሁን
በአንደኛው ዓምድ አጠቃሏል ፡ የታማኝነታችሁን
ለናንተም እሱን ማድረሱ ፡ ተቀዳሚ ተግባር ይሁን ።

—ፍኖቴዎስና ቆርነሌዎስ እጅ ነስተው ይወጣሉ—

ላርቆስ ምን ጉዳይ ነበረህ ፡ አቤቱታ አለኝ ያልከን
አይዞህ ንገረን ግድ የለም ፡ ፍቃድህን አትሸሽገን ።
አባትህን አማክረህ እንደሁ ፡ አንቃወምም አታስብ
እጅ ለአፍ ሃሳብ ለልብ
ያህል ነው እሱ እኛን ሲቀርብ ።

ላርቆስ
እንግዲያስ ደጅ ጥናቴን ፡ ልናገር ጃንሆይ ካጽናኑኝ
ወደ ፓሪ እንድመለስ ነው ፡ ፍቃድዎን እንዲለግሱኝ ፤



አስቀድሞም አመጣጤ ፡ ስለነበረ በድንገት
ለዘውድዎ መጐናጸፊያ ፡ ክበረ በዓል ለመገኘት ፤
ዛሬ በዓሉን አክትሜ ፡ የሚገባኝን ካደረስኩ
ልቦናዬን ወደ ፓሪ ፡ ዳግመኛ ስላዘነበልኩ
ግርማዊነትዎ ስንብት ፡ እንዲቸረኝ ነው የቀረብኩ ።

ንጉሥ
እኮ ሃሳብክንስ ሰማን ፡ አስፈቅደሃል አባትክን ?
እዉን አንተ ጶሎኔዎስ ፡ ሰጥተኸዋል ምርቃትክን ?

ጶሎኔዎስ
አዎን ጃንሆይ ፈቅጃለሁ ፡ . . . አላስተነፍስህ ቢለኝ
በንትርክ አሰልችቶ ፡ ልቤም ባይፈቅድ እሺ አሰኘኝ ፤
ምርቃቱማ ባባት ሆድ ፡ እምቢ ብልም አይሆንልኝ
የርስዎ ቡራኬ ይልቃል ፡ ፈቅደው ቢያሰናብቱልኝ ።

ንጉሥ
በጄ እንግዲያው እንዳልከው ይሁን ፡ ልጅህንም አይበለው ቅር . . . .
ፈቅደንልሃል ላርቆስ ፡ ሂድ ወደ ፈረንሣይ ምድር ፤
ከእንግዲህ ጊዜህ ያንተው ናት
እንዳሻህ ተጠቀምባት ።
አንተስ የወንድምዬ ልጅ ፡ ኀምሌትስ ምን ያሰኝሃል
የወንድም ልጅ እኮ ልጅ ነው ፡ 'ባይወልዱትም ልጅ' ይባላል ።

ኀምሌት
ይባላል አዎን እርግጥ ነው ፤
የፍቅሩንማ ሆድ ይፍጀው ።

ንጉሥ
ታድያ አሁንም ምነው ልብህ ፡ ይመስላል የቀዘቀዘ ?

ኀምሌት
ኧረ ምን ቆርጦት ጌታዬ ፡ ወብቆት ነው የነበዘ ።

ንግሥት
ተወው ልጄ ተወው ኀምሌት ፡ ካልተዉት አይተውም ሐዘን
ለሀገሪቱ ስትል ይፍካ ፡ ልብህ በሷስ አይጨፈን ፤
አባትክን ታስመልስ መስሎህ ፡ በሐዘን ጥልቀት ምርምር
በምድረ ዴን ትቢያ ላይ ፡ ግንባርክን ከቶ አታኮስትር ፤
ኗሪ ሁሉ ሟች መሆኑን ፡ ታውቃለህ ሁሉም በተራ
በዕድሜ ድልድይ ተሻግሮ ፡ ወደዘለዓለሙ ሥፍራ
የማታ ማታ እንዲያመራ ።


ኀምሌት
አውቃለሁ አዎን እናቴ ፤ ሞት በዓለም መሆኗን ተራ ።

ንግሥት
ተራ መሆኑን ታውቅኸው
ታዲያ ላንተ ብቻ ምነው
ልዩ መስሎ የሚታየው ?

ኀምሌት
'መስሎ' አልሺኝ እናት ዓለም ? ነው እንጂ የምን 'መስሎ' ነው !
'መስሎ' የሚሉ ነገር ነው ፤ ይልቅ እኔ የማላውቀው ።
የደረብኩት ጥቁር ካባ ፤ የኀዘን መለዮ ኩቴ
ወይንም በሮሮ ሲቃ ፤ እፍን እፍን ማለቴ
እንባ የሚያቀርረው ዓይኔ ፤ የተኮሰተረው ፊቴ
ገጽ መንጨት ደረት መጣል ፤ መንሰቅሰቅ መርገፍገፍ ሁሉም
የውስጤን አይመሰክሩም ፤
ለምስክርም አይበቁም ።
'መስሎ' ማለት ይሄ ይሄ ነው ፤ ማንም ዘንድ የማይታጣ
ለይሉኝታ ለወግ ለስም ፤ በአደባባይ የሚሰጣ ፤ . . . .
መች እንዲህ ነው የኔ ጣጣ
ለይስሙላ ይፋ የሚወጣ ፤

ንጉሥ
እኛም አላጣነው ኀምሌት ፤ ልብህ የሬት ማቅ ማጥለቁን
መክፈል ግብርህ እንደሆነ ፤ ለአባትህ የሐዘን ምሱን ፤ . . . .
አባትክም አባት ነበረው ፤ የዚያም አባት አለው አባት
ግን በየተራው ሲለየው ፤ የሞትን ጽዋ እየጠጣት
የዚያም ልጅ እንዳንተው አዝኗል ፤ እንደየሐዘኑ ጽናት ፤
ግን ሐዘንን እንደድግምት ፤ ከዕለት ወደ ዕለት ማኘክ
ፍሬ ቢስ መሰላቸት ነው ፤ እንዲሁ በከንቱ መቸክ ።
የወንድ ልጅ ወግ አይደለም ፤ ይኸ እንደዚህ ብጤው ግድፈት ፤ . . . .
ለመንግሥተ ሰማይ ድፍረት
ለመለኮት ኀይል ንፍገት
የአእምሮም ሰላም ማጣት ፤ ከመንፈስ ጸጋ መራቆት
አለመገመት ይባላል ፤ ያንዳች አስተያየት እጦት ።
ሞት የተለመደ ጽዋ ፤ መፈጸሙ የማይወገድ . . . .
እኛ ምን እንደሆንን ሳናውቅ ፤ ዛሬ ሰው ነገ ትቢያ ዐመድ
እምን ላይ ነው መበለጡ ?
የከንቱ መንፈራገጡ ?





እምን ላይ ነው መበለጡ ?
በከንቱ መንፈራገጡ ?

በተፈጥሮ ግፍ መዋል ነው ፤ ይኸ ሕገ ወጥ ሐዘን
ከእግዚአብሔር አብ መቀናቀን
ከሙታንም መቀናቀን ፤ . . . .
ፍሬ ከንቱ ነው ጥበቡ ፤ በአእምሮም ሚዛን ቢሆን
—ሰው ሆይ አንተ አፈር ነህ—ብሏል ፤ ከዘፍጥረት እስከጽዮን ፤. . . .
በል እንግዲህ ተለመነን
ይኸን የዋይታ ሰቀቀን
ከልብህ አውልቀህ ጥለህ ፤ እንደ አባት ተቀበለን
አገር በይፋ ይወቀው ፤ አባት እንሁንህ ልጅ ሁነን ።
ለኛ ሆነ ለአልጋችንም ፤ አንተው ብቻ ነህ እምትቀርበን
እኛ እንደ ልጅ ፈቅደንሃል ፤ አንተም እንደ አባት ፍቀደን ። . . . .
ቪተንበርግ ዩኒቨርሲቲ ፤ ልትሄድ ላሳሰበህ ጉዳይ
ልባችን ቅር ተሰኘ ፤ . . . ርቀኸን ፊትክን እንዳናይ
ይሆናልና አትሂድብን ፤ አንተው ነህ ያለኸን ሲሳይ
ልጃችን ባለሟላችን ፤ ፍቅራችን የዓይናችን አዋይ ።

ንግሥት
ሰሞኑን ጸሎቴ ይኸው ነው ፡ ኀምሌት ልጄ አታሳፍረኝ
አትሂድ ወደ ቪተንበርግ ፡ እኔን እናትክን ጥለኸኝ ።

ኀምሌት
እናት ዓለም ከምታፍር——ልቅር እሺ ፡ ምን ቀረጠኝ ።

ንጉሥ
እሰየው ልጄ ፡ ተባረክ ፡ ቀና አንደበት እንደዚህ ናት
ምድረ ዴን የኛም ያንተም ነች ፡ እና አብረን እናገልግላት ። . . . .
ይኸው በጥሞና ስሜት ፡ ግንባርህ ድንገት ቢፈካ
የኛም ልቦና ተነካ ።
ንሳ አንተ ጶሎኔዎስ
የምሥራች መድፍ ይተኮስ ።
ሁሉ ሰምቶ ይቀበለን ፡ ምድሩ ፡ ሕዝቡ ፡ አገሩ
አዲስ ፀሐይ መፈንጠቋን ፡ ለመላው ዓለም ያብሥሩ
አድባራቱ በየአድማሱ ፡ አስተጋብተው ይመስክሩ ።

—መድፍ ይተኮሳል፡ ከበሮ ይጕሰማል፡ እምቢልታ ይነፋል። ከኀምሌት በቀር ሁሉም ይወጣሉ—

ኀምሌት
አዬ ሥጋዬ ታዘብኩህ ፡ ዓይኔ በወጋህ ጦር ሆኖ
ጤዛህ ባካፋ ደምኖ
ጥጥሩ ስጋዬ ቀልጦ ፡ እንፋሎት ቢሆን መንምኖ
አዬ ሥጋ ፡ አዬ ከንቱ ፡ አዬ አዋይ ፡ አዬ መቅኖ ! . . .
ምነው አንተ ሕያው አምላክ ፡ የምድረ ዓለም ተአምኖ ፡ . . . .
አንተ የዘለዓለሙ ፡ ምን ቸገረህ ባትጣረር
ሕይወቴን በገዛ እጆቼ ፡ በተገላገልኳት ነበር ፤
ኧረ ምን የቁም መቁሰል ነው ፡ ሕይወት የሚሉት ትርጉሙ
ማደፉ ፡ መርከሱ በቀር ፡ አልታይህ አለኝ ጥቅሙ ፤
አረሙ ካበባው ጐልቶ ፡ ሙጃ የዘፈቀው ተክል
ኧረ ወዲያ - ወዲያ ይቅር ! ይኸ ደን ያፈነው ዕድል
ሕይወት የምትሉት እክል . . . .
ሆነ እንግዲህ ለዚህ በቃን . . . ገና ሳይሞላ ሁለት ወሩን
ያን የመሰለ አዛውንት ፡ የዚህ የአርዮስ ፌዝ ይሁን ! . . .
ሁለት ወር ? ኧረ አይሆነውም ፤ . . . መቼ ሞልቶት ሁለት ወራት
እንዲያ እሚወዳት እናቴ ፡ ክፉ አይንካብኝ እሚላት . . . .
ምድርና ሰማየ ሰማይ ፡ እሱ ብቻ ይወቅላት
እዚህ ጉግ ማንጉግ ሞገድ ላይ ፡ ምን እንዲህ እንዳጣበቃት ፤
ያቀመሳት የግፍ ጣዕም ፡ ሰጥቷት በላተኛ ወስፋት



ባንዲት ወር ውስጥ ለዚህ ያብቃት ! . . .
አዬ የወላዋይ ወኔ
ሴት ብዬ ሰየምኩሽ እኔ ።
በዚህች ባንዲት ወር ዕድሜ ፡ ጫማዋ እንኳ ወዙ ያው ነው
ያባዬን አስከሬን ያኔ ፡ ሸኝታበት የነበረው ፤
ስታነባ . . . ወዮ ስትል ፡ ሕቅ ስትል
እንደ አቴናዋ ናዮብ ፡ የእንባ ጋን አርጓት ይመስል ።
ወይ እናቴ እናት ዓለም ፡ ቀን አይወልደው ጉድ የለውም
አውሬ እንኳ ጓደኛው ሲሞት ፡ ጥንቡ እስኪሸት አይበላውም ። . . . .
በገዛ አጎቴ ለወጥሽው ፡ በኔው አጎት የኔን አባት . . . .
እኮ አጎቴ አባቴ ሊሆን . . . ባንዲት ወር ለዚህ ጉድ ያብቃት !
የቀዳችው የእንባ ባሕር ፡ ምንጩ በግፏ ጨው ደርቆ
የቦዘ ዓይኗም ፍልቅቅ አለ ፡ ከሞት ቀን የሠርጉን አውቆ ።
አይ አንቺ ጊዜ ፡ አይ ጥድፊያሽ ፡ ይቺን የግፍ ዕፅ ለማጽደቅ
የቅኑን አባቴን አልጋ ፡ በእርኩስ ፍትወት ለማዳሸቅ ፤ . . . .
መቼም ላንዳች መቅሰፍት ነው ፡ ጊዜን ጊዜ ያጣደፋት
ብቻ ያም ሆነ ፡ ያም ሆነ ፡ ምላሴን ጸጥታ ዳኚያት . . . .

—ሆራትዮስ ቤርናርዶስና መርቆሬዎስ ገብተው እጅ ይነሱታል—

ከየት መጣህ ሆራትዮስ ! . . . ገርጥተሃል ! ተሳሳትከኝ

ሆራትዮስ
ኧረ አልተሳሳትክም ልዑል ፡ ያው ያንተው ትሁት አሽከር ነኝ ።

ኀምሌት
ዛሬስ ይኸነን ስም ካንተ ፡ መለዋወጥ በተቻለኝ ። . . . .
እኮ በል እንጂ ሆራትዮስ ፡ ከቪተንበርግ ምን መለሰህ . . . .
አንተንም አስታውሳለሁ ፡ መርቆሬዎስም አደለህ ?

መርቆሬዎስ
ልዑል አልተሳሳቱም ፡ ነኝ ።

ኀምሌት
ይልቅ በል እንጂ ሆራትዮስ ፡ ምን እግር ጣለህ ንገረኝ ፤

ሆራትዮስ
ትምህርት ሸሽቼ ለዕረፍት
ጥቂት ጊዜ ለመዝናናት ፡ ለመስነፍ ፡ ለንዝህላልነት . . . .

ኀምሌት
እንኳን ጠላትህ ወዳጅህ ፡ ሆራትዮስ ሰንፏል ቢለኝ

እውነት እኔ የማምን ነኝ ?
የለም ይኸስ አያስመኝም
እንኳን ላንተ ለጠላትም ።
አንቅቶ ያተጋህ አምላክ ፣ መች ፈጠረህ ለስንፍና ?
እኔስ መች አጣሁህና ፤
ይልቅ እውነቱን ንገረኝ ፣ ለምን መጣህ ፣ ምነው ደኅና ?

ሆራትዮስ
ልዑል ይሞ ምን ሆንክብኝ ፣ አመጣጤን እያወቅኸው . . . .
ለግርማዊ አባትህ ሞት ፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት ነው ።

ኀምሌት
ለዚያማ ደርሰህ ሄደሃል ፤ . . . . ወይስ እስከዛሬ አልሄድክም ?
እውነትም ሰንፈሃል ልበል ፣ ስንፍና ነው መዋሸትክም ፤
ይልቅ ለንግሥት እናትህ ፣ የሠርግ በዓል አትልም ?

ሆራትዮስ
እንግዲያስ የመጣሁበት . . . ጉዳዩን ባታምነው እንኳን . . . .
ጉበዝ ብንነግረው ይሻላል ። እንግዲህ እግዚአብሔር ይርዳን
ይወቀውና እንወጣው ፣ ልዑል ፣ ባክህ አንዴዜ ስማን ፤ . . . .

—በጆሮው ይነግረዋል—

ኀምሌት
ምን !
እግዚኦ አበስኩ ገበርኩ . . . .
ያባትህ ጣዕረ መለኮት ? . . . አንተ ነህ እኔ ነኝ ያበድኩ ?

መርቆሬዎስ
እውነት ነው ልዑል እውነት ነው ፤ የእውነት አበስኩ ገበርኩ ነው ፤
ልቦናዬ እንኳን ባያምነው
ዓይኔ በውኑ ነው ያየው ።

ሆራትዮስ
እና እኔም ከቪተንበርግ ፣ የመጣሁበት ጉዳዬ
ይኸንኑ ‘አበስኩ ገበርኩ’ ፣ ስለሰማሁ ነው ጌታዬ ፤
ታዛዥ አሽከርህ ወዳጅህ ፣ ሆኜ ፣ ቀርበን ስለሚያዩኝ
የዓይን ምስክር እንድሆን ፣ እነኝህ ጉበዛዝ ጠሩኝ ፤
መቸም ዘበት ነው የሚባል ፣ አየው ወይም አላየው ዓይን
ሥጋ የለበሰ ፍጡር ፣ ይኸን እውነት ብሎ ላያምን ፤ . . . .
ጨረቃ በደረቀ ሌት ፣ ምድርን በብርሃን ስትለኩስ
ነጐድጓድና መብረቁ ፣ ሰማየ ሰማዩን ሲድስ



ያባትህ ጣዕረ መለኮት ፣ በሙሉ የጦር ትጥቅ ልብስ
የመቃብሩን ቤት ከፍቶ ፣ አንፋሮና ለምድ አጥልቆ
እንደ አንድ ቱም ዋንተኛ ፣ ሁለት እግሩ ምድር ለቅቆ
በጋሻ ጦር በዘር ዝናር ፣ በደግ እንደተንጣለለ
ነጐድጓዱ ሲያዝገመግም ፣ ፊት ለፊታችን ተግ አለ ፤
ሰብሐት ለአብ ሥሉስ ቅዱስ ፣ ኧረ ሞት በስንት ጣዕሙ
ያንን የመንፈስ ተአምር ፣ በዓይን ሥጋ መቋቋሙ ! . . .
በፍርሃት ላንቃዬ ነቅቶ . . . በእሥራኤል አምላክ ገዘትኩት
በአብርሃም በይስሐቅ አምላክ ፣ ምንድነህ ተናገር አልኩት . . . .
እንኳንስ ሊያነጋግረኝ ፣
አሽቆልቁሎ ገላመጠኝ
እንደ ጉድፍ ገረመመኝ ።
ብገዘተው ፣ ባስፈራራው ፣ ብማለደው ፣ ባግባባውም
ኩቶ ያንታ አልነበረውም ።
የዚያን ጊዜ ነው ትዝ ያለኝ ፣ የዚያን ጊዜ ነው ያወቅሁት
የግርማው ምጥቀት አንቅቶኝ ፣ ያንጊዜ ነው ያስታወስኩት . . . .
ግርማዊ አባትህ ያኔ ፣ ከድሮው ኖርዌይ ንጉሥ ጋር
በአንድ ወረዳ ግዛት ምድር ፣ ሲረታቱ ፣ ያላንድ አጋር
በሁለቱም አህጉር መኳንንት ፣ የዓይን ምስክርነት
በተገጣጠሙበት ወቅት ፣
በጉግሥ ጦር ውጊያ ሥርዓት ፣ ተፈካክረው ድል ሲነሱ
ለካ የዚያን ጊዜው ነበር ፣ ክብሩና ግርማ ሞገሱ
የጥሩር አለባበሱ
ምድረ-ደዬን በእልልታ ፣ ፈክታ ፣ ወሰን እስከ ወሰን
አንድ ወረዳ ግዛት ምድር ፣ ለሕዝቡ በረቱበት ቀን . . . .
ይኸ ነው ትዝ ያለኝ ነገር
ያቋሙና የሞገሱ ፣ ልክ የዚያችን ዕለት ነበር ። . . . .
ወዲያው እንደገረመመኝ ፣ ግንባሩ ወግቶኝ እንደሾህ
ከበተክሲያኑ አካባቢ ፣ አውራ ዶሮ ብጤ ቢጮኽ ፣
የጨረቃው ብርሃን ፈዞ ፣ ድብዝዞ እንደፈነጠቀ
እንደምሽት ጀንበር ወርዶ ፣ እመቃብሩ ጠለቀ ፤ . . . .
እና እኔንም ከቪተንበርግ ፣ ያመጣኝ ቴህ በቀር የለም
ጉዳዩ ይህ ተአምር ነው ። ቀብር ወይም ሠርግ አደለም ። . . . .
በእውነቱ ሆራትዮስን ፣ እስካሁን ድረስ ካመንከው
ዛሬ በይበልጥ እመነው ፣ እምነት የሚሻው ዛሬ ነው ፤
ሰውን አመንኩ የሚባለው
አካሉን ሳይሆን ፍቅሩን ነው
ሆራትዮስ ያው የቀድሞው ፣ አሽከርና ወዳጅህ ነው ፤

ከቶ አትጠራጠር ልዑል ፥ . . . እሷ ትጠርጥረኝ ጽዮን
ዓይኔ ብረቱ ነው ያየው ፥ ዓይን የሚታመን እንደሆን ።

ጎምሌት
ይኸን ጉድ ከናንተ በቀር ፥ ሌላ የሰማው ሰው አለ ?

መርቆሬዎስ
የለም ልዑል ፥ ማንም የለ ።

ጎምሌት
አሁንም እንደነበረ ፥ በገበናችሁ ይቀመጥ
ወዳጆቼ አደራችሁን ፥ ለማንም ሰው አይገለጥ ፤ . . . .
ሌሊት ፥ ጨረቃ ስትፈካ ፥ ምድር ስትል እርጭ ጸጥ
እመቃብሩ አካባቢ ፥ ከናንተ ጋር እንድናደፍጥ ፤
ሆራትዮስ እንድትወስደኝ ፥ . . . ጉዴን እኔው እንድፋጠጥ ።

—ይወጣሉ—

# ት ፡ ፫

—ላርቆስና ወፌ-ይላ ይገባሉ—

ላርቆስ
በይ እንግዲህ መሄዴ ነው . . . ጓዜንም ጠዋት አስጫንኩት
ግን ባትጽፊ እንጣላለን ፥ የምሬን ነው ፥ አባባ ይሙት ።

ወፌ-ይላ
እጽፍልሃለሁ አልኩህ ፤ . . . ጋሽዬ ሙት እጽፍልሃለሁ
ሰነፍ አደረከኝ እንዴ ፥ አባባ ይሙት እልሃለሁ . . . .

ላርቆስ
ደብዳቤው እንኳ ግድ የለም ፥ ተቀይሜ እረሳዋለሁ
ግን የዚህን የጎምሌት ነገር ፥ በእማማ አጥንት ይገርሻለሁ ፤
ነጋ ጠባ ሲሳለምሽ ፥ ደልሎሽ ስታናግሪ
የቤተ ሰባችንን ስም ፥ መሳቂያ አርገሽ እንዳትቀሪ ፤
ቀልብሽን ሳይነጥቅሽ በፊት ፥ ለዘብ ይበል መዛመዱ . . . .
ፈገግታውን ብትመልሺም ፥ እንደወጉ እንደልማዱ
ነቅተሽ ተግተሽ መዝነሽ ነው ፤ ኋላ ቀን ጉድ እንዳይፈላ
ተጠንቀቂ ወፌ-ይላ ።
ያልዘረዘረች ለጋ እምቡጥ ፥ የማትዘልቅ ትኩስ ስሜት
ያንዳፍታ ጣፋጭ ብልጭታ ፥ ነገር ግን የዕድሜ ልክ ሬት
ሆኖ እንዳይቀር ያንቺም ውጤት ።

ወፌ-ይላ
እውነት ጋሼ በአባባ ሞት ፥ እንደዚህ ነው የሚመስልህ ?
ይኸ ብቻ ነው እሚታይህ ?

ላርቆስ
ኋላ ምን ሊታየኝ ኖሯል ፥ ጊዜ ከፈተነው ሌላ
ምድር ዕፅዋት ብቻ አታበቅል ፥ ያለሾህ ያለአሜከላ ፤
ወይንም የተፈጥሮ መልክ ፥ ሲካበት ሞልቶ ደርጅቶ
ብቻውን አደለም ከቶ
ግን እንደዚሁ እንደ ሕንፃ ፥ ላዩ በሰም አንጸባርቆ
አካባቢው በጌጥ ደምቆ
መሠረቱ ግን በግድፈት ፥ በአገም ጠቀም ተደባብቆ
በመሐንዲስ ጥበብ ጉድለት ፥ ወይ ባጉል መራቀቅ ዘፍቆ
ከስህተቱም ፥ ከጥራቱም ፥ ተቻችሎ ፥ አለ ተጣብቆ ። . . . .
እንግዲህ ጎምሌት ምናልባት ፥ ዛሬ እወድሻለሁ ሲል
በፍቅሩ የልብ ጥራት ፥ አይገኝ ይሆናል እክል ፤
ግን የልደቱን ደረጃ ፥ ስታስቢው የደሙን ቅጅ
እሱም ራሱ መወሰኑን ፥ ያው በልደቱ ሥልጣን እጅ
ፍቃዱ የሱ እንዳልሆነ ፥ አስተውዪ ፥ የናቴ ልጅ ፤
እንደየተራው ሰው አቅም
ምኞቱን ልቡ አይመጥንም ፤
ከሆነም ፥ የፍቅሩ ምርጫም
የጸጥታ ዋስትና ናት ፥ ለመንግሥቱ ጠቅላላ አቅዋም ፤
ስለዚህ የጎምሌት ፈቃድ ፥ ለተባለው የአቅዋም ድምፅ
ስልቱን መቃኘት አለበት ፥ ያው እንደመሪነቱ ቅጽ ።
ማለት ፥ እወድሻለሁ ሲል ፥ አንቺም ቃሉን ስታረቅቂ
የምድረ ዴንም ድምፅ አብሮት ፥ ማስተጋባቱን እወቂ
ተግባሩን እንጂ ፍቃዱን ፥ ሰማሁ ብለሽ አታዳምቂ ፤
ለደቂቅ ሰዓትም ብትሆን ፥ ኢያሳስትሽ ነገሩ
ሌት ተቀን ቢነተርክሽ ፥ ከፍትወት አታልፍም ፍቅሩ
ማለት ፥ ያንቺ ብቻ ሳይሆን ፥ የቤተ ሰብሽ ነው ክብሩ ፤
ፍቅርሽም ገብራ እንዳትቀር ፥ በማያዛልቅ ልብ ውላ
ለጎምሌት ፍላጐት ተጥላ
ተጠንቀቂ የናቴ ልጅ ፥ ተጠንቀቂ ወፌ-ይላ ።
ማንም ድንግል ልጃገረድ ፥ መቀነቷን እስካልፈታች
ላባቷም ክብር እኮ እስዋ ናት ፥ አሳጋጅ ወይንም አፋች ፤ . . . .

ሁሉ በልጅነት ዕድሜው ፣ ሁሉ በአበባ ዘመኑ
ማሳቻው ወጥመድ ይበዛል ፣ ሥጋት ነው ሌትና ቀኑ ፤
የሚያስተው እንኳ ባይኖር ፣ ለልጅ ደም ምሱ ነው መቅበጥ
አንቺን ግን ፍርሃት ታግድሽ ፣ ልቦናሽ ትበል ለጥ ጸጥ
የፈራና የነቃ ነው ፣ የማታ ማታ እሚበለጥ ።

ወፌ-ይላ
ጋሽዬ ከምክርህ ፍሬ ፣ ሁሌም እንዳተረፍኩ ነኝ
ዛሬም ለስሜቴ ስህተት ፣ ተግሣፅህ ዳኛ ስትሆነኝ . . . .
ምነው ጨለማዋን ብቻ ፣ አሳየኸኝ የሕይወትን
ራሱ የማያጸድቀውን ፣ ሕግ እንደሚሰብክ ካህን ፣
ለሌሎች ያስተማራትን ፣ ሥርዓት እሱው ቢያፈርሳትም
ከቶ ገደፍክ አይባልም ፤
አንተም እንዲሁ ጋሽዬ ፣ ፓሪ ስትኖር ከኛ ርቀህ
ዛሬ ያስተማርከኝን ሕግ ፣ ሳታፈርሳት ትቀራለህ ?

ላርቆስ
አንቺ ይልቅ ተጠንቀቂ እንጂ ፣ የኔ ስህተት አይቸግርም
ለኔ አትስጊ ፣ ግድ የለሽም ። . . . .
ይልቅስ አባባ መጣ ፣ . . . መሄጃዬም ረፈደና

—ጶሎኔዎስ ይገባል—

ከቤት ሳልወጣ ከመጣህ ፣ . . . አሰናብተኛ እንደገና ፤

ጶሎኔዎስ
አሁንም አልሄድክም አንተ ? . . . ቤት ለቤት ስትንደፋደፍ
ይልቅ መርከቡ መልሕቁን ፣ እንዳይነቅል እዚሁ ስትሰንፍ ፤
በል ፍጠን እኮ አሁን ንሳ . . . .
በምትሄድበትም ሥፍራ ፣ ስሜን በአጉል አታስነሳ ፤
ሃሳብክን ምላስ አይምራት ፣
ያልተመዘነችንም ቀልብ ፣ በነገር አታስቀድማት ፤
ከሰው ፣ ከጊዜም ተላመድ ፣ ግን ስትላመድ አጣራ
ከዚያም ከዚያም አትዳራ ፤
ሆኖም አንዴ ወዳጅ ካልከው ፣ አስተዳደጉን መዝነህ
በነፍስህ ገበና ያዘው ፣ በብረት መቀነት ቋጥረህ ፤
ይህም ሲባል ፣ መቀነትህ ፣ ተሰላችቶ እንዳይላሽቅ
ባስተያየት ካልበሰለ ፣ ከጥሬው ፣ ካልተቀጣ ልቅ
ከማንም ርዝራዥ ጋራ ፣ አፍ ተካፍተህ እንዳትስቅ ፤
ጠብ ውስጥም በርረህ አትስጠም
ግን አንዴ ከገባህበት ፣ እጅህ ከባላንጣህ ይቅደም ፤



ጆሮህን አንቅተህ አድምጥ ፣ እሱን ለማንም አትንፈግ
ቃልህ ግን ውስጥህ ይሽሽግ ፤
የያንዳንዱን ዝንባሌ ፣ በልቦናህ ጽላት ጻፋት ፤
ዳኝነትክን ግን አቆያት ፤
ዐመልና ሱስ አታብዛ ፤
ከአቅምህ በላይ ወግ አትግዛ ፤
ለይስሙላ ጉራ አትንዛ ፤
እንደሃብትህ ልበስ እንጂ ፣ በብልጭልጭ አትንዛዛ ፤
ምክንያቱም ፣ ጌጥ የሚያሳየው
የወረትን መለዮ ነው ፤
ማለት ፣ ደርሰህ ጥራዝ ብትነጥቅ ፣ ማንንም ሰው አታስደንቅ ፣
እንዲያውም ፓሪ ነው እሚልቅ
በማዕረግ መንጸባርቅ
ባልተጌጠም ልብስ ቢሆን ፣ በጭምቱ የጨዋ ትጥቅ ።
አበዳሪም ፣ ተበዳሪም ፣ ከቶ አትሁን ፣ ምክንያቱም
ተያይዞ ጠፊ ነውና ፣ ብድሩም ወዳጅነቱም ፤
ማለት ፣ በዕዳ ወረትን ፣ ማፍረስ እንጂ አያደረጁም ።
ከሁሉ ይልቅ ላርቆስ ፣ በራስ መታመን አይንሳህ
ከዚያ ኋላ እንደቀን ቍጥር ፣ ተከታትሎ ሁሉም አይጠፉህ ፤
አስቀድሞም አእምሮህን ፣ ራስክን ካልቻልክ ማጭበርበር
በሌላውም ሰው ላይ ከቶ ፣ አትችልም በሃሰት መመስከር ፤
በል በዓይኔ ሥጋ ይግጠመን ፣ . . . ቡራኬዬም ይኸን ምክር
ያርገው በልብህ እንዲያድር ።

ላርቆስ
ዓሜን ፣ ያንተም አምላክ ይርዳኝ ፣ . . . ደኅና ሰንብቺ ወፌ-ይላ
ቅድም የነገርኩሽን ቃል ፣ እንዳትዘነጊ ኋላ ፤

ወፌ-ይላ
ዘግቼው በልቤ ማኅደር ፣ ሌት ተቀን እንዳይለየኝ . . . .
ቁልፉም ትእዝብትህ ይሁነኝ ።

—ላርቆስ ይወጣል—

ጶሎኔዎስ
በይ አንቺ ፣ ምንድነው ደሞ ፣ ፊቴ እምትመሣጠሩ ?

ወፌ-ይላ
አ-አይ ኸረ ሌላም አደል ። ስ-ስ-ስለ ኀምሌት ነው ነገሩ ።

ጶሎኔዎስ

እ . . . ም . . . .
እኔም ደርሼበታለሁ ፣ ሰሞኑን ካንቺ ጋር በግል
መጥቶ ሲያወጋ እንደሚውል . . . .
አንቺም ፊት እንዳልነሳሽው ፣ ሽው ብሎኛል ታሪኩ
ግን ያወቅሺው አይመስለኝም ፣ የት ድረስ እንደሆን ልኩ ፤
የቱን ያህል እንዲከብድ ፣ የልጇ የክብርሽ አቅም . . . .
ዳሩ ክብሩ ይቆይና ፣ ራስሽንም ታውቂ አይመስለኝም ።
ምንድነው ይኽ በምሥጢር ፣ የሚያስዶልታችሁ እክል
በይ ንገሪኝ እኮ ነው እምል !

ወፌ-ይላ

ኧረ አባባ እስከዚህም ፣ የለን የሚደበቅ ምሥጢር
ሊያዋየኝ ይመጣል እንጂ . . . በ-በኔ ባደረበት ፍቅር . . . .

ጶሎኔዎስ

ፍቅር ! . . . ኧረ ወዲያ ፍቅር
እንዲህ አርጎም የለ ምሥጢር ። . . . .
መሆኑንስ ሆነ እንበል ፣ ነጋ ጠባ ስላዋየሽ
የእውነት ውይይት መሰለሽ ?

ወፌ-ይላ

ኧረ እንጃ እሚመስለኝንም ፣
አባባ እኔ አላውቅሁትም ።

ጶሎኔዎስ

ሊመስልሽ የሚገባሽን ፣ እንግዲያውስ ይኸው ስሚኝ
እኔን ጅል ነው እምትመስዪኝ ።
ውይይቱን ከተቀበልሽ
ሕፃን ነሽ ፣ ገና ጡት ያልጣልሽ ።
እንዲህ በርካሽ ሲያዋይሽ ፣ ውይይትሽ ዋይታ እስኪሆን
እኔን መወያያ አታርጊኝ ፣ በከተማው ፣ ለአንድ ሰሞን ።

ወፌ-ይላ

ኧረ መወያያ አትሆንም ፣ ከልብ ነው የሚወደኝ ፣
እንደ ወጉ ፣ እንደ ሥርዓቱ ፣ ለጋብቻ ነው የሚፈቅደኝ ፤

ጶሎኔዎስ

እሰየው የኔ ወገኛ ፣ ' እንደ ወጉ ' ትበል አያ !
ወግ አደል የናንተ ሞያ
እኮ በይ ውጪልኝ ወዲያ ።




LIBRARIES

ወፌ-ይላ

ኧረ ሰጥቶኛል የውል ቃል
በእግዚአብሔር ስም ምሎልኛል ።

ጶሎኔዎስ

ላይምልልሽ ኖሯል ኋላ !
ያጥምድ እንጂ በመሃላ
ያንቺ ብጤዋን ተላላ ።
የልጅነት ደሙ ፍሞ ፣ ሥራ ሥሮቹ ሲነዱ
ለእግዚአብሔር ቃል ለመሃላ ፣ ለግዝቱ ነው ሽጉዱ ፤
ይማል እንጂ ምነው አይምል
ስታሳስቂው የኔ ጅል ።
የእውነት መሸፈኛው ይሄ ፣ እንደዚህ ብጤው መሃላ
የልብ እሳት አይምሰልሽ ፣ ጭላንጭል ነው ወፌ-ይላ ፤
መቸም ያለፈው አለፈ ፣ ከእንግዲህ ግን ተቆጠቢ
የልጃገረድ ክብርሽም ፣ እስኪጐድፍ አትቃረቢ ፤
ቃሉን በጨዋ ጥሞና ፣ በቅንነት ተቀበዪ
ለመሳት ግን አትቸኩዪ ፤
አየሽ ልጄ ፣ ልዑል ኀምሌት ፣ የመቀነቱ ዙር መጠን



ይማል እንጂ ምነው አይምል
ስታሳስቂው የኔ ጅል ።

የወርዱና የቁመቱ ፣ ባንቺ ዕድልም ባይወሰን
ልጅ ነውና ይዘነጋል ፣ ምንም በልብሽ ቢታመን ።
ስለዚህ የሱን መሃላ ፣ መቀበል እንደ ወንጌል ቃል
በዝማሬው ፣ በውዳሴው ፣ ተሰልቦ ቀልብንም መጣል ፣
ውጤቱንና ፍሬውን ፣ ቁም ነገሩን ሳይገምቱ
ተሸብሮ መማረክ ነው ፣ እንዲያው በሽለላ ከንቱ ።
አዎ ፣ እሱም እንዳንቺው ልጅ ነው ፣ ለጊዜው ብቻ እሚሳስቅ
የነገ ሃላፊነቱን ፣ የተግባሩን ልክ የማያቅ ፤ . . . .
እንዲያውም ከዛሬ ወዲያ ፣ ማንም አብሮ አየኋት ቢለኝ
ክርስቶስ አንቺን አያርገኝ ።
ዘልዛላ ! . . . ውይይት አልሺኝ ? በቁም ቅገርትሽ ወትውቺ ! . . .
ዳግም ከልዑል ኀምሌት ጋር ፣ ባይሽ አፍ ስትካፈቺ
ትእዝብት ይሁንሽ እንግዲህ ፣ በቃ ፣ ወዮ እኔና አንቺ ።
ለዚህም በቃሽ እሜቴ ? . . .
በይ እኮ ዞር በይ ከፊቴ . . . .

—ይወጣል—

ወፌ-ይላ
ም - ምን ባጠፋ ነው ፣ ምን ያለኝ ? . . . ም - ምንድነው ያሳቡ ሚዛን
ም - ምንድነው እሚለው አምላኬ ? ም - ምን አረግሁት እመ - ብርሃን ?

—ትወጣለች—

# ት ፡ ፩

—ኀምሌት ሆራትዮስና መርቆሬዎስ ይገባሉ ። ውርጭ ፣ ጭጋግና የካፊያ ውሽንፍር ነው ። ነጐድጓድና መብረቅ እያስተጋባ ያንጸባርቃል ። ጣዕረ መንፈስ ባሻገር ብቅ ይላል—

ኀምሌት
ስብሃት ! እግዚኦ ! እግዚአብሔር አብ ፣ እግዚአብሔር ኃያል መንፈስ !
ነፍስን ከሥጋ እምትገሥ !
ሰውረን ! ሰውረን ! በለስ ! . . .
ተናገር ! ምንድነህ አንተ . . . እግዚኦ ሠለስቱ ምዕት !
ጣዕረ መንፈስ ነህ የእውነት ፣ ወይ የደረቀ ሌት ልክፍት
ከገሃነም ሽምጥጠህ ነው ፣ ከሣጥናኤል የእሳት ብብት
ወይስ ከመንግሥተ ሰማይ ፣ አለ የመለሰህ መልእክት
በእሥራኤል አምላክ ተገዝተ
የጤና ነህ ወይ የመቅሰፍት !




ፍላፃህ ይውገረኝ እንጂ ፣ አልተውህም ካልተሰየምክ
አረጋዊውን አባቴን ፣ ተመስለህ ከተገለጥክ . . . .
አደናቁረህ አታስቀረኝ ፣ ፍታልኝ ይኸን መሠሪ
አባዬ ልበልህ ወይስ ፣ የረቂቅ መለኮት ጥሪ
ንገረኝ . . . ንገረኝ ባክህ ፣ . . . .
እስትንፋስ የነሳት ነፍስህ
ትቢያ የጠቀማት ዐጽምህ
ለምን መጣች ዕረፍት አጥታ !
በመኖር ባለመኖር ጋድ ፣ የጋርዮሽ ተከስታ
የሙታንን ግድብ ከፍታ
በመልአክ ሞት ተተፍታ
ለምን መጣች በል ተናገር ! . . .
ወይ ጥላህን አትጣልብኝ ፣ ላትናገር ላትጋገር
ፊት ለፊቴ አትደንቀር . . . .
የሙታንን ሥርዓት ደፍረህ ፣ መቃብር ድሰህ ከመጣህ
በእግዚአብሔር እምነታችንን ፣ ለማጠራጠር ካበቃህ
በሕልውናችን አፍረን ፣ ነፍሳችን እስክትዘላብድ
ዓይነ ሥጋም ብትመሰክር ፣ ልቦናችን ፈርታ እስክትክድ
ሞገድ መብረቅ አስከትለህ ፣ በዚህ በደረቅ ሌት ቁር
ከራስ ፀጉርህ እስከ እግር ጥፍርህ ፣ አጥልቀህ ያባቴን ጥሩር
መለኮት ባለበሰህ ኃይል ፣ ተደናቁረህ አትገተር
በሕያው አምላክ ተናገር ! . . .

ሆራትዮስ
ወዴት ነው እሚያመለክትህ . . . .
ተከተለኝ ነው የሚልህ . . . .
ወደ ባሕሩ ሠላጤ ፣ ወደ አዘቅቱ ነው እሚያሳይህ ! . . .

መርቆሬዎስ
ቆይታ ያለው ይመስል ፣ ና ነው እሚል ወደ ገደሉ . . . .
ልዑል ተዉ አይከተሉ ! . . .

ሆራትዮስ
አይሆንም ጌታዬ አይሆንም
ዓይኔ እያየ አብረህ አትሄድም ! . . .

ኀምሌት
እዚህ አልናገር ካለ ፣ ይምራኝ እሄዳለሁ የትም !



ሕይወቴ እንደሁ መቅኖ አጥታለች ፣ ተከተለኝ ካለ ልሂድ ! . . .

ሆራትዮስ
ልዑል በጭራሽ አይሆንም !
እገደሉ አፋፍ አድርሶህ ፡ እሚፈጥረው አይታወቅም . . . .

ኀምሌት
እንኳንስ ገደሉንና ፣ ሰማዩንም አብሮኝ ቢንድ
ሕይወቴ እንደሁ መቅኖ አጥታለች ፣ ተከተለኝ ካለ ልሂድ ! . . .
ዕድሌ ካለቺኝ ልሂድ ! . . . እንግዲህ ባወጣው አውጪኝ
ዕጣ ክፍሌ ከጠራሽኝ ! . . .
ባንቺ አደራ ትቆይ ነፍሴ . . . .
ልቀቁኝ ነው የምል ጉበዝ ! ከእንግዲህ መዘዝ ነው ዋሴ !
ከእንግዲህ ውርድ ከራሴ ! . . .

—ኀምሌት እባሕሩ ሰላጤ ድረስ ጣዕረ መንፈሱን ተከትሎት ይወጣል—

# ት ፡ ፭

—ጣዕረ መንፈሱና ኀምሌት ፈፋው ዳርቻ ይታያሉ—

ኀምሌት
ቱህ ወዲያ አልከተልህም ! ንገረኝ የምትነግረኝን
በሞት ባለመሞት መሐል ፣ የተበተበህ ምሥጢርክን
ፍታልኝ እንቆቅልሽክን ።

ጣዕረ መንፈስ
ጠንቀቅ ብለህ አድምጠኝ ፤
ልብ ብለህ ተከተለኝ ።

ኀምሌት
አደምጥሃለሁ ንገረኝ ።

ጣዕረ መንፈስ
ወደ ነበልባል እሳት ከርስ ፣ ወደ ድኝ ፍም ስቃዬ
የምከሰትበት ዕለት ፣ ደርሷል ቀነ ቀጠሮዬ . . . .
ልብህ በሐዘን አይቀለስ ፣ ሳይረባኝ የሰው ልጅ እንባ
ይልቅ የነገሬ ፍሬ ፣ እልቦናህ ጽላት ትግባ ፤

ኀምሌት
አዋየኝና ልፅነሳት
ስጠኝ ቃልክን ልመዝግባት . . . .

ጣዕረ መንፈስ
የደሜን ኡኡታ ሰምተህ ፣ በደም እንድትበቀላት !

ኀምሌት
ደም ?

ጣዕረ መንፈስ
የሙት አባትህ መንፈስ ነኝ ፣ የነፍሱ ጣዕረ መለኮት
በዕረፍትና በዕረፍት እጦት
በሞትና ባለመሞት
በፍርጃ የተቸነከርኩ
ሌት በድፍን ጭለማ አናት ፣ በሕልም እየተመላለስኩ
ቀን ቀን በእቶን ነበልባል ፣ እንድመገብ የተገዘትኩ . . . .
ቀነ ቀጠሮዬ እስኪሠምር ፣ በሰማዕታት እየታገድኩ

እስኪከፈል ፣ እስኪታጠብ ፣ የደምና የሚራው ቂም
በሕይወቱ ጊዜ በቅሎ ፣ የታጨደ በዕድሜዬ አዚም
የወህኒዬን ስቃይ ዜና ፣እንድደብቅ ባልታዘዝ
አዋይህ ነበረ መዘዝ
የነፍስን ጥላ እሚገፍ ፣ እሚያመጥ የእስትንፋስዋን ወዝ
የልጅነት ትኩስ ደምህ ፣ ቆሌህም ገንፍሎ እስኪነብዝ
ሲቃህ አብስሎህ እስኪበልዝ . . . .
ግን ይኸ ያመጻ ዜና ፣ ከሚች ሰው ሕሊና ሠምሮ
ሥጋና ደም በለበሱ ፣ ገብቶ በቋሚዎች ጀሮ
አይገታም ፣ ይፈነዳል ፣ ሕልውናቸውን ሰብሮ . . . .
ስማኝ ኀምሌት ፣ ስማኝ ልጄ ፣ ትወደኝ እንደሁ አባትክን
ተፈጥረህ እንደሁ በኔ አምሳል ፣ አምርተህ ከወዜ ወዝክን
አምርተህ ከደሜ ደምክን . . . .
ትመስለኝ እንደሁ አባትክን . . . .
ስማኝ ልጄ ፣ ስማኝ ኀምሌት ፤

ኀምሌት
እግዚአ አቤት . . . እግዚአ አቤት !

ጣዕረ መንፈስ
ደሜን ተበቀላት ኀምሌት
ፈሳ እንዳትቀር መሬት ።

ኀምሌት
የደም በቀል ! የማን በቀል ? የምን በቀል ተፈጠረ !

ጣዕረ መንፈስ
ከኮሶ የዘገነነ ፣ ከሞት ከሬት የመረረ ።
ኀምሌት ደሜ እንደፈሰሰ
አይቅር ትቢያ እንደነከሰ ።


ኀምሌት
ቶሎ ንገረኝ ልወቀው !
ያነቀኝ ሲቃ ሳይቀብረኝ ፣ ልወቀውና ልነቀው !
ልወቀውና ልወጣው !
የጠጣህን ጉድ ልጠጣው !

ጣዕረ መንፈስ
ያሰኛል ልጄ ያሰኛል ፣ ከኔም ጉድ ወዲያ ጉድ የለ
በምንም ሳቢያ ተግ አይል ፣ ወኔህ ቤህ ካልተቃጠለ ፤
እንደኔ የተቸገረ



ኀምሌት ፣ ከቶም አልነበረ ።
በቤተ መንግሥቴ ቅጥር ፣ በአትክልቱ የዕረፍት ሥፍራ
ተኝቼ እባብ ነድፎኝ ነው ፣ ተብሎ ነው እሚወራ ፤
ምድረ-ዴንም በዚህ ታፍኖ ፣ ተንበርክኮ ዓሜን ብሎ
የሐሰት ሁከት በጆሮው ፣ ታምቆበት ፣ ተቀብሎ
መወናበዱን አውቃለሁ ፣ ሐዘኔን ባንደበቱ አዝሎ ፤
አንተ ግን እውነቷን ስማ ፣ የተከተብኳትን ክታብ
እወቃት እንዳትሎግም ፣ አገሬን በለገማት ዛብ ፤
ዘውዴን የደፋት እባብ ነው ፣ እኔን የነደፈኝ እባብ ።

ኀምሌት
መንፈሴን የዘገነናት . . . .
ለካስ እሱ ኖሯል ነፍሴን ፣ ዓይነ ጥላ የጣለባት !
ይኸ ነበር የቀፈፋት
ነፍሴን የተጠናወታት ።



የደም በቀል ! የማን በቀል ! የምን በቀል ተፈጠረ !

ጣዕረ መንፈስ
እሱው ነው ኀምሌት እሱው ነው ፣ በርኩስ ተሰጥዎ ታድሎ
በትረ መንግሥቴን ነቃቅሎ
ክብሬን ፣ አልጋዬን በክሎ ፣
የሜራና የመሠሪ ፣ ወጥመድ በተንኮል አንቅቶ
መማክርቴን አሳስቶ
ሚስቴን በፍትወት አብክቶ . . . .
እንዲያ የማምናት እናትክን ፣ ያቺን ያለኝታዬን ሲሣይ
ፍቃድዋን ስለባት ስታይ . . . .
የምድረ-ዴንን ልቦና ፣ የሕዝቤን የክብሩን አዋይ
ስለባት ያ ንፉግ አባይ
እምነትን ከሕሊናዋ ፣ እውነትን ካንደበቷ ላይ ፤
የቅዱስ ጋብቻችንን ፣ ሥርዓተ ተክሊል አቃልላ
ከዚያ ከከይሲ ወደቀች ፣ በፍትወት ተበክላ ፤
ግና ይኸ የሥጋ ወረት ፣ ምን ቢጠገን ፣ ምን ቢታደስ
የብሩሕ መውደድን ሸማ ፣ ቢከናነብ ፣ ምን ቢወደስ
ከጥምብ እንሳ መሠረቱ ፣ ምሱን ሊሻ ከመልከስከስ
ከቶ አይወጣም ምን ቢላበስ ።
እንግዲህ ኀሕ ሊቀድ ነው . . . የብርሃን ኮከብ ሳትል ተግ
እንዳመጣብኝ ልሸሽግ ። . . . .
በብልቃጥ መርገዘ ይዞ አድፍጦ ፣ አንዳች ሳይጠረጥር ቀልቤ
በዕረፍቴ ጊዜ አትክልቴ ውስጥ ፣ ተጫጭኖኝ አሸልቤ
በጆሮዬ አንቆርቁሮ ፣ ደሜን ጠብሶኝ ተርገብግቤ
እንደ ሞት ጥላ ተስቦ ፣ ነደፈኝ በእንቅልፍ ልቤ ፤
የገዛ ወንድሜ እጁ ፣ እባብ መሆኑን አላሰብኩ
ሕይወቴን ፣ መንግሥቴን ፣ ሚስቴን ፣ ባንዲት ቀን ጀምበር ተገፈፍኩ ፤
ዓምላኬን እንኳ በጸሎት ፣ ለንስሃ ሞት አልለመንኩ
በቁም ገነዘኝ ወንድሜ ፣ ኃጢአቴን እንደለበስኩ ።
ኀምሌት ፣ ይኽንን የግፍ ግፍ ፣ ይኽንን የመዘዘ መዘዝ
ሃሞት ካለህ የወንድ ወዝ
ሳትበቀል እንዳትተኛ ፣ ያባትክን በቁም መገነዝ ፤
የፍትወትና የርኩሰት ፣ የዘበት አጥቢያ ተደርጋ
እንዳትቀር ተፈንግላ ፣ ያባቶችህ የክብር አልጋ ፤
ሆኖም በቀልክን ስታቅድ ፣ ፍቃድህ ከሕግ አይውጣ
የሙት ድምፄ ይገዝትህ ፣ እጅህ በናትህ አይቃጣ ፣
የመንግሥተ ሰማይ ጥብቅ ፣ የኔ ቁራኛ ናት እስዋ
ይፍረዳት የገዛ ቃልዋ
ሕሊናዋ ነው ሲአልዋ ፤



ልሂድ እንግዲህ ኀሕ ሳይቀድ ፣ የሌሊት ትል ዓይኑን ዘጋ
በምልክት ሊያስጠነቅቅ ፣ ጀመበር መንቃትዋን ልትነጋ
ሟችን በብርሃን ልትወጋ . . . .
ልሂድ እመቃብሬ ቤት
ቀኔ ተለውጧል በሌት ፤
እንግዲህ አትርሳኝ ኀምሌት ፣ . . . አስታውሰኝ ፣ አስታውሰኝ ኀምሌት ።
—ይወጣል—

ኀምሌት
እናንተም አትርሱኝ እግዚኦ ፣ አትርሱኝ እናንት ሰማዕታት
አትርሺኝ መንግሥተ ሰማያት
ዋስ ሁኚኝ እንድፈጽማት ፤
ያባቴ የመለኮት ቃል
ከሞት አዘቅት ኡኡ ! ብሏል ።
ነፍሴም ባንነሽ አትለቂ
ግዴታሽን ሳታጸድቂ ። . . . .
ግዞተኛው ረቂቅ መንፈስ ፣ መሀላዬን ተቀበላት
ከእንግዲህ ወዲያ ሃሳቤን ፣ ያንተ ፈቃድ ብቻ ይምራት
ሕይወቴ ያላማህ መዝገብ ፣ ሕልሜ የቂምህ ማኅደር ናት
ልቤም የበቀልህ ጽላት ። . . . .
ያለኝታ አርማዬ የነበርሽ ፣ ወዮ እማማ ፣ እናት ዓለም
ዛሬስ ካንቺ ወዲያ ከንቱ ፣ የውድቀት ምሳሌ የለም ።
ወዮ አንተ የሥራይ ጠቢብ ፣ ወዮ እንግዲህ እኔና አንተ
የተተበተብክበት ውል ፣ ሤራህ ቁልፉ ተከፈተ ፤
እሾህ ላጣሪው ነው አሉ ፣ ካንተው ተምሬ እንዳልበልጥህ
ለካስ ስትስቅ መንከስህ ነው ፣ ስትመክርም መርዝ መማስህ
ከሰይጣን ወዲያ ሰይጥኜ ፣ በቆፈርከው ነው እምቀብርህ ፤
አባባ አትርሳኝ ብሎኛል ፣ አንተም አትርሳኝ አጎቴ
መቃብርህ ላይ ነው ሞቴ ።

—እነሆራትዮስ ተሯሩጠው ይገባሉ—

ሆራትዮስ
ምነው ልዑል ጉድ አረከን !
አዬ ፣ በደልከን ፣ በደልከን ።
ምን አረግንህና ጠፋህ ? . . .
ኧረ እንኳን በለስ የተፋህ ።

መርቆሬዎስ
ኧረ እንኳን የተፋዎ ጃል !

ኀምሌት
መትፋት አልከኝ ፣ ውጦ መትፋት ? . . . እውነት ነው እኮ ያሰኛል . . . .

ሆራትዮስ
ጉዳህ እንዴ ? ነካህ እንዴ ? ሰውነትህ ደኅና አደለም ?

ኀምሌት
ኧረ ደኅና ነኝ ፣ አታዩም ? አንድ አጥንት አልተሰበረም . . . .

ሆራትዮስ
እኮ ምን አርግ ነው እሚልህ ? . . . በ- በጤና አልተለያየህም ?

ኀምሌት
ገና አልተለያየንም ፤ ገና አልተሰነባበትንም ፤ . . . .
ውስጤ ገብቶ ተዋህዶኛል ። ውጬዋለሁ አይለየኝም ። . . . .
ሆራትዮስ ፣ የሰው ልጅ መተት ፣ ከዕድሜው ጋራ ሲመጣጠን
ለካስ መተቱ በዝቶ ነው ፣ ዕድሜው ባጭር የሚወሰን ።

ሆራትዮስ
ታድያ ይኸ አዲስ ነገር አደል ። የዚህን ምሥጢር አላጣን
ሌህ ሲባል መቸም ከሲኦል ፣ ረቂቅ መንፈስ አላስጠራን ፤ . . . .
ይልቅ ምንድነው መዓቱ ! ጉዱን አሰማን ፣ አሰማን . . . .
ወይስ በዚች ደቂቃ ውስጥ ፣ ላለመተማመን በቃን ?

ኀምሌት
አለመተማመን አልከኝ ? . . .
የሱ ጥም ነው እኔን የያዘኝ . . . .
ግን ደሞ እውነትክን ይሆናል ፣ አዲስ ነገር የለም ያልከኝ . . . .
ስመ እግዚአብሔርን ጥሩና ፣ ሰይፋችሁን ተራምዳችሁ
ማሉና ትሰማላችሁ ። . . . .
መጀመሪያ መሃላችሁ ፣ አንዳች እንዳልተፈጠረ
አንዳች ነገር እንዳላየን ፣ ምንም ጉድ እንዳልነበረ
በኔና በናንተ መሃል ፣ ሊቀር እንደተሠወረ
በወንድ ልጅ በጀግና ስም ፣ ሰይፍ ተራምደን መማማል
ካፋችን ላይወጣ ይህ ቃል ፤
ሁለተኛው መሃላችን . . . ይኸ አሁን የምትሰሙት
እንኳንስ በሕይወታችሁ ፣ ስትሞቱም አብሯችሁ ይሙት ፤ . . . .
ወይ አፍኖ ይገድላችኋል ፣ ገና ሰምታችሁ ሳትዘልቁት ፤ . . . .

—ሲናገር ሲቃጣ የጣዕረ መንፈሱ ጩኸት ከምድር ውስጥ ይሰማል—



አለሀና ገና አልሄድክም ! ይኸዋ ! አላልኳችሁም ፤
ገና አልተሰነባበትንም ።

ጣዕረ መንፈስ
ይማሉ ፣ ኀምሌት ፣ ይማሉ ።

ኀምሌት
ሰምታችሁት የለ ጉበዝ ፣ ማሉ እኮ ነው እሚለው ቃሉ ።

ጣዕረ መንፈስ
ማሉ ።

ሆራትዮስ
እንምላልን ፣ እንምላለን
ልዑል መሃላውን ስጠን ።

ኀምሌት
የሰይፉን ስለት ንከሱ ፣
አንዳች ብትተነፍሱ
በሞትም ፣ ከሞትም ወዲያ ፣ ይከተላችኋል ክሱ ።

ጣዕረ መንፈስ
ማሉ እንዳትሸጧት ቃሌን ።

ኀምሌት
ካሁን ጀምሮ እስከ መቸም ፣ ለዘለዓለም ዓለም ዓሜን ።

ሆራትዮስ
እግዚኦ ! ምን ቁጣ ነው እሱ ?

ኀምሌት
የሰይፉን ስለት ንከሱ ።
ገና ምኑን አወቅህና ፣ . . . ብቻ አንዳች አትናገሩ
ውሀ ከምንጩ ነውና ፣ የበቀል ውርስም ከዘሩ ።

ጣዕረ መንፈስ
ማሉ እንዳትሸጧት ቃሌን

ኀምሌት
ዓሜን ፣ ለዘለዓለም ዓሜን ። . . . .

ሆራትዮስ
እግዚኦ የሰው ልጅ ዕድር !

ኀምሌት

በቋሚና በሙት መሀል ፡ ያልተደረሰ ምርምር
ሥጋ ለለበሰ ፍጡር ፡ ያልተገለጠ ተአምር
ፍልስፍናችን ያልፈታው ፡ አለ ብዙ ረቂቅ ምሥጢር . . . .
የሰው ልጅ ዕድርም ካልከው
ሃሳብክን ለግልህ ቋጥረው ፤
ቃሉን ብቻ ተቀበለው . . . .
እኔ እንደሁ ከእንግዲህ ወሰንኩ ፡ ላልመራመር ተፈጥሮን
ዕብደት ጤንነት እንዳልሆን ፡ ጤንነት ዕብደት እንዳልሆን ፤
ብቻ ይኸንን አድምጡኝ
አድምጣችሁ ተቀበሉኝ ።
ከእንግዲህ ወዲያ ብቻዬን ፡ ሳነበንብ ብታገኙኝ
ቤተ መንግሥት ፡ አደባባይ ፡ እንዳይሆን ስሆን ብታዩኝ
አታናግሩኝ ፡ አትጠይቁኝ ፤
አትዘኑልኝ ፡ አትሙኝ ፤
ምንም እንዳልተፈጠረ ፡ እንዲያው በደፈናው ተዉኝ ፡
ቢያስፈልጋችሁም እርሱኝ ።
እንዳልነበረ ቁጠሩት ፡ ከናንተ መወዳጀቴን
ብቻዬን እወጣዋለሁ ፡ ለብቻ የሰጠኝ ቁም ስቅሌን ።

ጣዕረ መንፈስ

ይማሉ ፡ ኀምሌት ይማሉ !

ኀምሌት

መሃላውን ተቀበሉ ፤
ተቀበሉት ቃሉን ፡ ቃሌን
ለዘለዓለም ዓለም ዓሜን ።
የሰይፉን ስለት ንከሱ . . . .
አንዳች ብትነፍሱ
በሞትም ፡ ከሞትም ወዲያ ፡ ይከተላችኋል ክሱ ።

—ይወጣሉ—



# ገቢር ሁለት

## ት ፡ ፩

—ጶሎኔዎስና ምዕመኑ ይገባሉ—

ጶሎኔዎስ

በል ይኸን ማስታወሻና ፡ ይህቺን ገንዘብ ስጥልኝ . . . .
ታድያን ሳታገኘው በፊት ፡ ጠባዩን አጠያይቅልኝ ፤

ምእመኑ

ኧረ እኔም ይህንን ብዬ ፡ ወስኛለሁ ፡ ቀድሞ አቅጄ ፤

ጶሎኔዎስ

ደግ አቅደሃል ። ጎሽ ልጄ . . . .
እንዲያውም ከሱ አስቀድመህ ፡ ፓሪ የሚኖር የኛን ሰው
የሁሉን ገቢና ወጪ ፡ አኳኋኑንም መርምረው
ጠቅላላ ዝንባሌና ፡ አስተያየቱን ፈትነው ፤
በነሱ ሳቢያም የልጄን ፡ አዲስ ያፈራውን ጠባይ
ከሱ ሳይሆን ፡ አጠያይቀህ ፡ ጥያቄህ ጎልቶ ሳይታይ
ጥብቅም ሳይል ላይ በላይ
ለይተህ ፡ ጠንቅቀህ አጥናው ፡ ሰውን ከሩቅ ነው የሚያውቁት
በወዳጅ ጠላት መስተዋት ፡ ባሕርዩን ተንትነው ሲያዩት
ከሚያቀርቡት በሚርቁት ፡ ከሚያወድሱት በሚያሙት
አማካይ ነው የሚያጠኑት ።
ገብቶህ የለ ምእመኑዬ ?

ምእመኑ

አዎን ገብቶኛል ጌታዬ ።

ጶሎኔዎስ

ታዲያን ከርመህ ስታገኘው ፡ ከሱው ምሥጢር ፡ ከሰማሃት
አንድዋን ከጨዋታ አስታምመህ ፡ ዝግ ብለህ አከክ አርጋት ፤ . . . .
በለዘብታ ካልታለለ
አብሿም አጋንንታም ነው ፡ ዘሎ ግሥላ ነኝ ካለ ፤


ክብሩም ደሞ እንዳይዋረድ ፣ ሰው ፊት እንዳይገባ ግምት
እንዲያው በጐልማሶቹ ወግ ፣ ዋዛን ባዘለ ውይይት . . . .

ምእመኑ
በተረት ፣ በእንካ ስላንትያ ፣ በሽኩቻ ወግ ማለት ነው ?

ጶሎኔዎስ
አዎን ፣ መጠጥ ፣ ክርክር ፣ ፉከራን ፣ ጉራን ጨምረው ፤

ምእመኑ
ጌታ ፣ ያማ ዘለፋ ነው ።

ጶሎኔዎስ
የለም ፣ ካቀራረቡ ነው ፤
ባደባባይ ወጥቷል ጉድህ
ወዮ ላንተ ምን ይዋጥህ
በለው ማለቴ አይምሰልህ ፤
ግን ስህተቱን ዝግ ብለህ ፣ የመቆጠብንም ጥቅሙን
በብልጭታ የፈጸመው ፣ የቤተ ሰብ ስም ማጉደፉን



ገብቶህ የለ ምእመኑዬ ?



አጉል ውጤት ማስከተሉን
ሽፈን አርገህ ነው ላይ ላዩን ።

ምእመኑ
ብቻ ጌታዬን አንዲት ቃል . . . .

ጶሎኔዎስ
እንዴት ነው የማውጣጣቸው ፣ ልትለኝ እኮ ይሆናል ፤
ዘመን አመጣሽ ዘዴ አለ . . . ካንዱ የሰማሃትን ጫፍ
ቀመም ፣ ጣፈጥ አድርገህ ፣ ስታጐርሰው ለሌላው አፍ
እሱም ደሞ በበኩሉ ፣ ያመጣዋል አያድርሱን
ዕዳ እንዳለበት ሁሉ ፣ ይከፍል ይመስል ብድሩን
የቀበራትን ይተፋል ፣ ዝርግፍ አድርጐ ምሥጢሩን ፤
ትልቅ ፣ ትንሽ ፣ ዘመድ ፣ ባዕድ ፣ ለመለየትም አይቻል
የወሬ አስተናጋጅ መሆን ፣ ምሥጢር ማፏጨት ወግ ሆኗል
የቋጠራት ፋይዳም ባትሆን ፣ እስዋኑ ወዲያው ሽው ይላል ፤

ምእመኑ
እሺ ጌታዬ ፣ ገብቶኛል ፤

ጶሎኔዎስ
በል መንገድክን ጨርቅ ያርግልህ ፣ አይርፈድብህ ደኅና ዋል ።
—ምእመኑ ይወጣል ። ወፌ-ይላ ትገባለች ።—

ጶሎኔዎስ
ምነው ደኅና ወፌ-ይላ ?

ወፌ-ይላ
እንጃ አባባ ፈርቻለሁ ፣ ደንግጬ ርቆኛል ጥላ ፤

ጶሎኔዎስ
ምን አገኘሽና ልጄ ?

ወፌ-ይላ
እልፍኝ ውስጥ ተቀምጬ ፣ ፈትል ሥራ ይዤ በጄ
ልዑል ኀምሌት ድንገት ገባ ፣ ልብሱ ሁሉ ተዝረክርኮ
የግር ሹራቡ እንኳ ሳይቀር ፣ ቅልጥሙ ላይ ተበሳስኮ
ሙቆም እንዳቃተው ሁላ ፣ እግሩን እያብረከረከ
የበለዘ ቅጠል መስሎ ፣ መንፈሱን እንደታወከ ፣
ዓይኑ በስቃይ ታፍኖ ፣ አንደበቱ እንደታሰረ
ከሲኦል እንደሸሸች ነፍስ ፣ ደርሶ እንደተንደረደረ
ከየት መጣ ብዬ ሳልል ፣ ፊት ለፊቴ ተዘረረ . . . .

ጶሎኔዎስ

ምናልባት በስሜት ጭንቀት ፣ እንደሆን ቀልቡ ተሰልባ ፣

ወፌ - ይላ

ኧረ እኔ እንጃ ፣ ኧረ እኔ እንጃ ፣ . . . ፈርቻለሁ እንጃ አባባ ፤

ጶሎኔዎስ

እኮ ምን ለከፈኝ አለሽ ?

ወፌ - ይላ

. . . እጄን ክርር አርጎ ይዞ ፣ ባክኖ ፣ ትክ ብሎ እያየኝ
በክንዱ አርቆ ጨብጦኝ ፣ በትእዝብት እየገመተኝ ፤ . . . .
ሳይናገር ፣ ሳይተነፍስ ፣ በሌላ እጁ ፊቱን ጋርዶ
አንገቱን የኋሊት ሰብሮ ፣ ካባው ከትከሻው ወርዶ
አይለቀኝ ፣ አያናግረኝ
ባይኑ ነበልባል ሲገርፈኝ ፤
ነፍሱን በመንጠቆ ይገፎ ፣ ያራቆትኳት አስመሰለኝ . . . .
እንደዚያ ቆይቶ ውሎ
ድንገት ለቆኝ ፈንገጥ ብሎ
ጭንቅላቱ እንደተለየው ፣ አንገቱን ቀልሶ ጥሎ
ታፍኖ እንደተለቀቀ ፣ አንደዜ ብቻ 'ሕቅ' አለ ፤
ነፍሱ ከትከሻው በርራ ፣ ባዶው የቀረ መሰለ ፤
ዓይኑን ወደኔ ቀልሶ ፣ እያደር እየገረጣ
እንደሚራመድ አስከሬን ፣ ቁሙን ተጐትቶ ወጣ . . . .

ጶሎኔዎስ

የለም ነይ ጌቶች ጋ እንድረስ ፣ ኋላ ሳያስከትል ቁጣ . . . .
ፍቅር የምትሉት ጣጣ ።
ክልሉን ድሶ ፣ ገንፍሎ ፣ በገዛ እልሁ ታፍኖ
ፍቅር የምትሉት መተት ፣ እስከዚህ ያሳጣል መቅኖ ? . . .
እንዲህ የሚያስደርግ ነገር ፣ አስታውሺ እስቲ ይኸን ሰሞን
ተናግረሽውስ እንደሆን ?

ወፌ - ይላ

የለም ፤ ብቻ አንተ አስቀድመህ ፣ ያዘዝከኝን ነው ያረኩት
ከጻፈልኝ ደብዳቤዎች ፣ አንዱንም ሳላይ መለስኩት
አይድረስብሽ እንዳልከኝ ፣ እንዳይደርስብኝ ነገርኩት ፤ . . . .
ሌላስ የወጣኝም የለ ፣ አልተነፈስኩም አንዲት ቃል

ጶሎኔዎስ

ታድያ ይኸ ቀልብ ይሰልባል ? በኔ ሞት ፣ በይ ቀልብ ይሰልባል ? . . .



ወይ እኮ ይሰልብ ይሆናል ፤ . . . .
እኔን የመሰለኝ ሌላ ፣ ይኸንን መቸ ጠረጠርኩ
ከቶ ይኸንን የት አሰብኩ ?
እንደኔ የጠና ሁሉ ፣ ወጣትን ከስህተት ማገድ
መጠበቅ ብቻ እንዳለብን ፣ ስናወጣና ስናወርድ
ሳንቆጠብ እየፈረድን
የጠቀምናቸው ሲመስለን ፣
በድለን እንገኛለን ፤ . . . .
ሆኖም ጉዳዩን ካወቅነው ፣ ኋላ እንዳይመስል ማላበስ
ይሻላል ጌቶች ጋ ማድረስ ።
መውደድ የምትሉትን ጉድ ፣ በጀ መስሎኝ በመደበቅ
የኋላ ቀን ፣ ባለማወቅ
እንዳላስከትል ሌላ ጠንቅ ።

—ይወጣሉ—

## ት ፡ ፪

—ንጉሡ ፣ ንግሥቲቱ ፣ ገድለ ስምዖንና ሮዘንቅሮስ ካጃቢዎች ጋር ይታያሉ—

ንጉሥ

ገድለ ስምዖን ፣ ሮዘንቅሮስ ፣ በሉ እንጂ ወዴት ሸሻችሁ !
ሰነበተ ሳናያችሁ ፤
በግር ፈረስ ስንሻችሁ ፤
እንግዳ እምትሆኑ አይመስልም ፣ ሌህ ላስጠራናችሁ ነገር . . . .
የኀምሌትን ድንገት መቀየር
ልብ ሳትሉትም አይቀር ። . . . .
መቀየር እንጂ ምን ይባላል ፣ ያደረሰበትን ዕድል
የላዩም ሆነ የውስጡ ፣ ድሮ እማውቀውን ሳይመስል
ከርሞ ፣ ሰንብቶ እያገረሸ ፣ ያባት ሐዘን ነው እንዳንል . . . .
እና የለከፈውን ጉድ ፣ ካፉ አምልጦ እንኳ ውሎ አድሮ
ከናንተ ከወዳጆቹ ፣ አይደብቅምና ቀብሮ
ካብሮ አደግ ባለሟሎቹ ፣ ከትምህርት ቤት ጀምሮ . . . .
በርትታችሁ ብታዋጡት ፣ በውይይት አግባብታችሁ
ሰሞኑን በቅርብ ሆናችሁ
እቤተ መንግሥቱ ግቢ ፣ ማረፊያ እልፍኝ ተሰጥቷችሁ . . . .

ንግሥት
እሰይ ፤ ልጄንም ፤ እኛንም ፤ ጀግኖቼ አውጡን ከዚህ እክል . . . .
ከልጅነቱ ጀምሮ ፡ ስማችሁ ካፉ ዝር አይል
ከናንተ በስተቀር ሌላ ፤ የሚያምነው ያለም አይመስል ፤ . . . .
ታድያን እዚህ ቆይታችሁ ፤ ብታጠኑልን ሕመሙን ፤
ብትረዱት ጓደኛችሁን ፤
እኛ አቅቶን ተስፋ አጥተናል ፤ እናንተ ተስፋ ብትሆኑን
ቤተ መንግሥቱም በፈንታው ፤ ይከፍላል ወሮታችሁን . . . .

ንጉሥ
አዎን ፤ ካስደሰታችሁን ።

ገድለ ስምዖን
ፈቃድዎን እንፈጽማለን ፤ ካዘዘን ግርማዊነትዎ . . . .

ሮዘንቅሮስ
ጃንሆይ ፤ አገልግሎታችን ፤ መቸም ቢሆን ካስፈለገዎ
ከመስጠት አንቆጠብም ፤ ግዴታችን ነው ትእዛዝዎ ።

—እጅ ሲነሱ ንግሥቲቱ ይዛቸው ትወጣለች ። ጶሎኒዎስ ይገባል ።—

ጶሎኒዎስ
ወደ ኖርዌይ የተላኩት ፤ መልእክተኞች ደጅ ቆመዋል ፤
ቸር ወሬ ይዘው መጥተዋል ።

ንጉሥ
መቸም በቸር ጸጋ ዜና ፤ እሚስተካከልህ ጠፍቷል ፤

ጶሎኒዎስ
ነው ጃንሆይ ? . . . ከሆነማ ፤ ተግባሬን እንደሕይወቴ
ላምላኬና ለንጉሤ ፤ በታማኝነት መስጠቴ
የማይዛባ እምነቴ ነው ፤ . . . እና ፤ አሁንም ያመጣኝ
የጥንት አእምሮዬ ዛሬ ፤ ዕድሜ አድክሞት ባያሳጣኝ
በእርስዎ ያለኝን መታመን ፤ ኋላ ባያስጠረጥረኝ
የኀምሌትን ወፈፍታ ሳቢያ ፤ የገለጠልኝ መሰለኝ ።

ንጉሥ
ያማ ተአምር መግለጥ ነው ፤ ትንቢት ፈታሁልህ በለኝ ፤
እኮ ንገረኝ ፤ ንገረኝ ።

ጶሎኒዎስ
ግርማዊነትዎ ቢፈቅዱ ፤ መልእክተኞቹን በቅድሚያ



ተቀብለው ፤ አሰናብተው ፤ የኀምሌትን ጉዳይ መዝጊያ
ብናደርግ ይሻል ይመስላል ፤ ነገሩ እንዳይሆን የጥድፊያ . . . .

ንጉሥ
ደግ እንግዲያስ ፤ አስገባቸው ።

—ጶሎኒዎስ ሲወጣ ንግሥቲቱ ትገባለች—

የነገረኝን ሰምተሻል ! . . .
የልጅሽ ወፈፍታ ሰበብ ፤ ተገለጠልኝ ይለኛል ።

ንግሥት
ያው ያባቱን ሃዘንና ፤ የኛን መጋባት ይሆናል ፤
ሌላ ሰበብ ከየት ይፈጥራል ? . . .

ንጉሥ
ቆዩ እኮ አትሽቀዳደሚ
የሚያመጣውን ሳትሰሚ ፤

—ጶሎኒዎስ ፤ ፍኖቴዎስና ቆርኔሌዎስ ይገባሉ—

እንኳን በደኅና መጣችሁ ፤
ታድያስ ፤ ምን መልስ አገኛችሁ ?

ፎኖቴዎስ
ልዑል ኖርዌይ ፤ አስቀድመው ፤ ሰፊ ሰላምታ ልከዋል
ለግርማዊ ፤ ለግርማዊት ፤ ዕድሜ ይስጥልኝ ብለዋል ፤
መጀመሪያ እንደደረስን ፤ የወንድማቸው ልጅ ጉዳይ
ጦር መከተቱ በኛ ሳይሆን ፤ በፖላንድ ገዥዎች ላይ
መሆኑን እንደተረዱት ፤
ጉዳዩንም ችላ በሉት
ብለው ፤ ኋላ በጎን ፤ ምሥጢሩን ቢያስመረምሩት
በግርማዊነትዎ መንግሥት ፤ ሊዘምት እንደሆነ አወቁት ፤
ወዲያው በሕመማቸው ማጤን ፤ ምክንያት እንደቀበጠ
ተረድተው ፤ ተበሳጩና ፤ . . . ዘንግቶ እንደተቀመጠ
እጁን እንዲሰጥ አዘዙት ፤ እሱም አምኖ እጁን ሰጠ ፤
ከሰፊ ተግሣፅ በኋላ ፤ ወዲያው እጅግ ተጸጸተ
ዳግመኛ እጁን በርስዎ መንግሥት ፤ ላያነሳ ተገዘተ ፤
ኖርዌይ በዚህ ተደስተው ፤ የገንዘብ ሽልማት ሰጥተው
ቢሻም በፖላንድ እንዲዘምት ፤ ወታደር መቅጠሪያም ፈቅደው ፤
በተጨማሪም ግርማዊ ፤ መልካም ፈቃድዎን ቢሰጡ
የፎርጠንብሮስ ዘማቾች ፤ ወደ ወረራው ሲወጡ

በምድረ-ዴን ግዛት ላይ ፣ ቢያቋርጡ ይመቻልና
የይለፍ ፈቃድ እንዲያዙ ፣ ለምነዋል በትሕትና ።

ንጉሥ
ደግ ፣ እንግዲህ እናይና ፣ ጉዳዩን መክረን ፣ አጥንተን
መልስ እንልካለን ወስነን ። . . . .
የደከማችሁ ይመስላል ፣ ሌት ተቀን ስትገሠግሡ
ሂዱ ፣ አረፍ በሉና ፣ ለራት ሰዓት ተመለሱ ።
—መልእክተኞች እጅ ነስተው ይወጣሉ—

ጰሎኔዎስ
የድካማቸው ውጤቱ
አይመስልም የሆነ ከንቱ ። . . . .
ግርማዊ ፣ ግርማዊት ፣ መቸም ፣ የነጋሢነት ፍቺው ቃል
የሥራ ግዴታን ትርጉም ፣ . . . ቀን ለምን ቀን እንደሚባል
ሌሊትም ሌት ፣ ጊዜም ጊዜ ፣ የተሰኘበትን ምክንያት
ተመራምሮ ለማጣራት
ያው ቀንን ፣ ሌትን ፣ ጊዜንም ፣ መፍጀት እንጂ የለም ብልሃት ፤ . . . .
ነገር ማራዘም ፣ ማዳከም ፣ ነገር ማሣጠር ፣ ማሳመር
እንደሚባል ሁሉ እኔም ፣ ቶሎ ልቁረጥ ይኸን ነገር ፤
ልዑል ኀምሌት በርግጥ ዐብዷል ፣ አዎን ዐብዷል ያለ ስህተት
ለእውነት ዕብደት ፣ ዕብደት እንጂ ፣ ሌላ ትርጉም አይወጣለት ። . . . .

ንግሥት
ይልቅ አምጣ ፍሬ ነገር ፣
ጥበብህ ለነገ ይደር ።

ጰሎኔዎስ
ጥበብ አይደለም ግርማዊት ፣ ልስጥዎት የመሐላዬን ቃል
ማበዱ ይፋ እውነት ነው ፣ . . . እውነት መሆኑ ያሳዝናል . . . .
ማሳዘኑም ያው እውነት ነው ፣ . . . ለኀምሌት ግን አልቆለታል ፣
ጥበቡስ ምን ይጠቅመዋል ? . . .
ስለዚህ አውጥተን እርሙን
በሉ እንወያይ ምክንያቱን ። . . . .
ምክንያቱን ሳይሆን ሰበቡን
ሰበብ ነውና ኀምሌትን ፣ ለክፎ የሰለበው ቀልቡን ። . . . .
እንግዲህ እግዜር ያሳያችሁ ፣ . . . እኔም አንዲት ልጅ አለቺኝ
በተግባርዋ ታዛዥነት ፣ ይኸን ደብዳቤ የሰጠቺኝ . . . .
እና ላንብበው ፣ አድምጡኝ ፣
አድምጡኝና ፍረዱኝ ።



—ያነባል—

'ይድረስ ለንግሥት ጽዮን ፣ ለቁንጅና ድንበር ፣ ለናት
ለተዋብሽው ወፌ-ይላ ፣ ለነፍሴ ማኅደረ ጽላት ፤'
የተዋብሽው ? . . . የምን ውብት ? . . . ይኽ ቅሌት ነው በርግጡ . . . .
ኧረ ገና ምኑ ቅጡ ! . . .

—ያነባል—

' ደም ግባትሽ እንደ ብርሃን ፣ ሲያንጸባርቅ ውጋጋኑን . . . .

ንግሥት
ኀምሌት ይኽንን ጻፈላት ፣ ልትሉኝ ነው እውነት አሁን ?

ጰሎኔዎስ
እባክዎን ንግሥት ፣ ይለመኑኝ ፣
ታማኝነቴን ለማመን ፣ አስቀድመው ያስጨርሱኝ ።

—ያነባል—

'የከዋክብት እቶንነት ፣ እውነት እንዳልሆን መርምሪ
የጀምበርን መንጋት ፣ መምሸት ፣ ለመጠራጠር ድፈሪ
እውነት ውሸት እንዳይደለች ፣ ነቅተሽ ጠይቂያት አትፍሪ
ብቻ ፍቅርን ፣ አትጠርጥሪ ። . . . .
እዚያች ላይ ነው የኔ ሕመም ፣ ሌላው አይጐዳም ቢያቆስልም ፣
አየሽ ፣ አንቺ ወፌ-ይላ ፣ ፍቅር አትጠረጠርም ፤
ከኀምሌት ።'
ከቀረው ሐተታ ሌላ ፣ በቃልዋ ከነገረቺኝ
ይኽንም በታዛዥነት ፣ ልጄ አምጥታ ሰጠቺኝ ።

ንጉሥ
እኮ ስለፍቅሩስ ጉዳይ ፣ እንዴት ነው የስዋስ ሁናቴ ?

ጰሎኔዎስ
. . . ግርማዊነትዎ ስለኔ ፣ ምን ግምት አለዎ ፣ በሞቴ ?

ንጉሥ
ክብርህን የምትጠብቅ ፣ ታማኝ መሆንክን አልስትም ፤

ጰሎኔዎስ
ይኽንኑ እሚያረጋግጥ ፣ ማስረጃ ልስጥዎ ፣ አሁንም ። . . . .
የኒህ የሁለቱን ፍቅር ፣ ገና ሥር እንደነከሰ
እንደዚህ ሳያቆጠቁጥ ፣ አረሙን እንደለበሰ
ልጄ እንኳ ሳትነግረኝ በፊት ፣ ነገሩ ሸቶኝ ዝም ብል
እንዳልሰማሁ ፣ እንዳላየሁ ፣ የምሥጢራቸውን ብቅል

ባጽናናት በከንፈር ንክሻ
በርቺ ብላት ባይኔ ጥቅሻ ፡
ችላ ብዬ ባስተውለው ፡ ሲያብብ ባየው እያደረ
ግርማዊትና ግርማዊ ፡ ኋላ ምን ትሉኝ ነበረ ? . . .
የለም ገና ሸው ሲለኝ
ሕሊናዬን ቀነቀነኝ ፡
ታማኝነቴ ንቃ አለኝ ፤
ልጄ ፡ ልዑል ኀምሌት ላንቺ ፡ ኮከብሽ አደለም አልኳት ፥
ደረጃዋን አሳስብኳት ፤
ዳግመኛ ዓይኑን እንዳታይ ፡ ከቤት እንዳትወጣ አዘዝኳት ።
ደብዳቤና መልክተኛ
እንዳትቀበል ዳግመኛ
አስጠንቅቄ ዘጋሁባት ፡
ልጄም ምክሬን ተቀበለች ፡ ትእዛዜንም ፡ እንደአባት ፤ . . . .
ስታስወግደው አዘነ ፡ ሐዘን ብስጭት ፈጠረ ፤
ከብስጭት ፡ እልህ ፡ ንዴት ፡ ከዚያም ወፈፍታ ፡ እያደረ
የቀልብ መስለብና ፡ የቁም ቅዠት እየባሰ . . . .
እየጫረ እየባሰ
ይኸዋ ፡ እንዲህ ከሚያንጫጫን ፡ ከዕብደት ፍጻሜ ደረሰ ።

ንጉሥ

. . . ሰበቡ ይኸ ይመስልሻል ?

ንግሥት

. . . ይመስላል ፡ ሊሆን ይችላል ።

ጶሎኔዎስ

አዲስ ነገር እኮ አይደለም ፡ አልፎ አልፎ ይፈጠራል ።
ፈልፍዬ ደርሼበት ነው ፤ ሥሩን ስይዝ ያዋየሁዎት
ሌላ ምንም ሳብያ የለው ፡ ጃንሆይ በኔ ይሁንብዎት ።

ንጉሥ

እንጃ እስቲ እናብላላዋለን ፡ ይህ ብቻ ነው ብለን ሳንውጥ . . . .

ጶሎኔዎስ

ከዚህ ሌላ ሰበብ ቢገኝ ፡ ይኸው እኔ አንገቴን ልስጥ . . . .
ያይን ማስረጃም ቢያስፈልግ፡ ለሰበቡ ግልጥ ፍሬ
ከቀበረበት አንደበት ፡ አዋጣዋለሁ ቆፍሬ ።

ንጉሥ

እኮ እንዴት አርገህ ? ንገረን ።



ጶሎኔዎስ

ኀምሌት በእልፍኙ አዛኘር መግቢያ ፡ በቀን አራት ሰዓት ያህል
መመላለሱን ያውቃሉ ፡ ሲወጣ ሲወርድ እንደሚውል ፤

ንግሥት

አዎን ፡ አየዋለሁ ሁል ቀን ።

ጶሎኔዎስ

በዚህ ሰዓት እኛ አድፍጠን
ልጄን እንልክለታለን ፤
ያኔ የሚላትን ሰምተን
ከአንደበቱ የሚያዘንበው ፡ ባይሆን የፍቅር ሰመመን
ኋላም ያበቃው ለማበድ
ባለሟልነቴ ቀርቶ ፡ ከብት እረኝነት ልሰደድ ።

ንጉሥ

ይሞከር ፡ ምሥጢሩ በዚህ ፡ ምናልባት ከተገለጠ

ንግሥት

እንዲያውም ያውና መጣ ፡ መጽሐፍ እያገላበጠ ፤

ጶሎኔዎስ

ፍቀዱልኝ ፤ ፍቀዱልኝ ፥
እኔ ላናግረው ፡ ውጡልኝ ፤
ለብቻዬ ልቀቁልኝ ።

—ንጉሡና ንግሥቲቱ ሲወጡ ኀምሌት ይገባል—

ጤና ይስጥልኝ ልዑል ኀምሌት . . . ሰንብቷል ከተገናኘን . . . .

ኀምሌት

ደኅና ፡ ይመስገን ፡ ይመስገን ።

ጶሎኔዎስ

ምነው ልዑል ፡ . . . አታውቀኝም ?

ኀምሌት

እንዴት . . . እንዴት አላውቅህም ?
ዓሣ ዓጥማጁ አደለህም ?

ጶሎኔዎስ

ተሳስተሃል ፡ . . . ተሳስተሃል ፤
እኔን ከዓሣ አጥማጅ አትለይም ?

ኀምሌት
እስከዚህም ድረስ እኮ ፣ አይመስለኝም አሣፋሪ
ታማኝ ቀጥተኛ ሰው ነው ፣ ዓሣ አጥማጅ ዓሣ ጐርጓሪ ።

ጶሎኔዎስ
ልዑል ፣ ቀጥተኛ አልከኝ ?

ኀምሌት
አዎን ቀጥተኛ ታማኝ ፣ . . . በመቶ ሺህ አንድ አይገኝ ፤

ጶሎኔዎስ
ጌታዬ እውነት ነገርከኝ ።

ኀምሌት
ፀሐይ ፣ ከንፈረ ብርሃንዋ ፣ ስትስም በእንፋሎቷ ኃይል
እሞተ ውሻ ጥንብ ውስጥ ፣ ትላ ትል ብታስፈለፍል ፣ . . . .
ሴት ልጅ ወልደሃል አንተ ሰው ?

ጶሎኔዎስ
አዎን አድርሻለሁ ፣ ምነው ?

ኀምሌት
ፀሐይ እንዳትወጋት ጠብቅ ፣ ከስዋ የምትፀነሰው ትፍስሕት
ላይሆን እንደልጅህ ግምት
ደብቃት ወዳጄ እንዳትስት ።

ጶሎኔዎስ
አልገባኝም አሁን ያልከው ፤–ልጅ ሆኜ በፍቅር ነገር
እኔም ቀባጥሬ ነበር ፤—
ምንድነው እሱ እምታነበው ?

ኀምሌት
ቃላት ፣ ቃላት ፣ ቃላትን ነው ።

ጶሎኔዎስ
ታድያሳ ምን ነገር ይዝዋል ?

ኀምሌት
ነገር ? . . . በነማን መሐከል ?

ጶሎኔዎስ
. . . እምታነበውን ነው ያልኩት ፤ . . . ምን ምን ፍሬ ነገር ይዝዋል ?



ኀምሌት
ድፍረት ብቻ ፣ ድፍረት አዝሏል ።
የሸመገለ ሰው ሁሉ ፣ ሪዙ ይገረጫል ይላል
ገጹም ይኮሰትርና ፣ ዓይኑ ጥሬ ፍም ይመስላል
ወይ እንደቁልቋል ይዘንባል
ሃሳቡ ላሽቆ እየከዳው ፣ ወሰድ መለስ እያለ
ልሣኑም ወዙ ተመጥጦ ፣ ሲናገር 'ሲጥ' ይላል አለ ፤ . . . .
ታድያን ወዳጄ ፣ አሁንም
ምንም እኔም በትችቱ ፣ ሙሉ በሙሉ እንኳ ባምንም
የዘረዘረው ሀተታ ፣ ቀጥተኛ ነው ቢባልም
ድፍረቱን አልቀበልም ፤ . . . .
ምክንያቱም ያንተ የወዳጄም ፣ ዕድሜህ ያብባል ከኔ እኩል
ዘመንህን እንደ ግርሻ ፣ የኋሊት መጐተት ብትችል ።

ጶሎኔዎስ
—ኸረ ነገሩስ ቅጥ አለው ፣ አልዘላበደም ቢንጣጣ ፣
ቅጥ ያለው ዕብደት ከየት መጣ ?—
ከሱ ከነፋስ ሽውታ ፣ ብርድ ያማታል ፣ ወዲህ ውጣ ፤

ኀምሌት
ከነፋስ ተወጥቶ ወዴት ?
አልተዘጋጀሁ ለምድር ቤት ።

ጶሎኔዎስ
ያልወጣኝን ? በየት በየት . . . .
—በልጄ ካልተጠመደ ፣ አልተፈታም የሱስ ወጥመድ ፣—
ቀጠሮ ብጤ ነበረኝ
ልዑል ፣ ስንብትክን ስጠኝ ።

ኀምሌት
እኔ እምሰጥህም የለኝ ፣ . . . ልሰጥህ ግን የምፈቅደው
እኔም ከቶ እማልፈልገው
ወዳጄ ፣ ሕይወቴን ብቻ ነው ፤
አዎን ሕይወቴን ብቻ ነው ።

ጶሎኔዎስ
በል ደኅና ዋል ልዑል ኀምሌት ፤

—ዞር ይላል—

ኀምሌት
—. . . ምን የዋህ ! መንቻካ ባልቴት ።—

—ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ይገባሉ—

ጶሎኔዎስ
ልዑልን ነው እምትፈልጉት ?
ያውላችሁ ፤ ሂዱ አጫውቱት ።

—ይወጣል—

ሮዘንቅሮስ
እንኳን እግዜር ለዚህ ያበቃህ ፤

ገድለ ስምዖን
ኧረ እንኳን ያቆየህ ፤ አዎን ፤

ኀምሌት
ሮዘንቅሮስ ! ገድለ ስምዖን ! . . .
ጉበዝ ምን እግር ጣላችሁ ?
ከየት መጣችሁ ? ደኅና ናችሁ ?

ሮዘንቅሮስ
አለን ፤
እየተንከላወስን ፤

ገድለ ስምዖን
አዎን ፤ ይመስገነው አለን ፤ ደኅና ነን ምንም አንልም
ዕድል እንደባርኔጣዋ ፤ አናቷ ላይ ባትጭነንም ፤

ኀምሌት
ጥላስ አልረገጠችህም ?

ገድለ ስምዖን
እዚያ ታችስ አልወረድንም ፤

ኀምሌት
ሽንጧ መሐል ፤ ወገቧ ጋ ፤ ከደረስክ እሱ ነው ግቧ ፤
ታቅፋሃለች ማለት ነው ፤ አስጠግታ ወደ ልቧ ።

ሮዘንቅሮስ
አዎን ፤ አላራቀችንም ፤

ኀምሌት
የቆሎ ጓደኞችዋ ነን ፤ ምሥጢረኞች ነን አትልም ፤ . . . .



ሆነም ፤ ዳሩ ምን ይረባል ፤ ወናፍነትዋን አትተውም ፤ . . . .
በሉ ጉበዝ ፤ ወሬ አምጡ እንጂ ፤ ምን አዲስ ነገር ይወራል ?

ሮዘንቅሮስ
ዓለም ፤ የእውነት ደብር ሆነች ፤ የሚሉ ወሬ ይሰማል ።

ኀምሌት
ምፅዓት ደረሰ በለኛ ! . . . ወይ ወሬው አሉ ቧልታ ይሆናል ።
ቆይ በዝርዝር እንወያይ . . . ለዕድል ቅርብ ነን ካላችሁ
ወደዚህ ወደ ወህኒ ቤት ፤ በምን በደል ላከቻችሁ ?

ገድለ ስምዖን
የምን ወህኒ ቤት አመጣህ ? የለም ልዑል አትሳሳት ፤

ኀምሌት
ተወው ፤ ለወሬው እንግዳ ነህ ፤ . . . . ምድረ-ዴን እኮ ወህኒ ቤት ናት ።

ገድለ ስምዖን
ይኸን ካልክማ መላ ዓለም ፤ ወህኒ ቤት ነው ቤህ መሠረት ፤

ኀምሌት
ያለቀለት ፤ የወጣለት
አንዳች እንከን የሌለበት ፤
ግዞት ፤ ሽረት ፤ እሥር ፤ ስደት ፤ ዱላ ፤ ግርፊያ ፤ ስቃይ ፤ ግዳይ ፤
ምድረ-ዴን ግን ምንጩ ናት ፤ ለዚህ ሁሉ አደባባይ ።

ሮዘንቅሮስ
ልዑል ፤ በዚህ አንስማማም . . . .

ኀምሌት
ደንታ የላችሁምና ፤ ለናንተ እንደኔ አይሰማም ፤ . . . .
ያማ ፤ ክፉም በጐም የለ ፤ ልቦናችን ካልፀነሰው
ሃሳባችን ካልፈጠረው ። . . . .
ምድረ-ዴን ለኔ ወህኒ ነው ።

ሮዘንቅሮስ
ምናልባት ዕቡይ ዓላማህ ፤ የማደግ መንፈስ አንቅቶህ
ዴን ቢያንስህ ፤ ወህኒ መስሎህ
ጠልተኸው ይሆናል ፤ ጠቦህ ።

ኀምሌት
እንግዲያውስ ረስተኸኛል ፤ . . . የሽምብራ ሽፋን ታህል
መከናንቢያ ሥር ኖሬ ፤ ጠበበኝ ጨነቀኝ ሳልል ፤

ከዓለመ - ዓለማት ንጉሥ ፥ ከምድርና ከጠፈር
ከከዋክብት ባለቤት ፥ ይበልጥ ፥ ደስ ባለኝ ነበር ፤
ምድረ-ዴንን የጠላኋት ፥ ወህኒ የሆነብኝ ቤቴ
ጠባኝ ሳይሆን ፈርቻት ነው . . . ክፉ ሕልም በማየቴ ።

ሮዘንቅሮስ
ያው የታብዮ መንፈስ ነው ፥ በእንቅልፍ እየተጠለለ
እያደር ዘር እሚዘራው ፥ የሕልም ጥላ እየመሰለ . . . .

ጎምሌት
ሕልም ራሱስ ጥላ አደለ ?

ሮዘንቅሮስ
ያውም ከንቱ ከፊፍ ነገር ፥ ከአየር ክብደት ያላየለ
ትልቅ ከመምሰል ታብዮ ፥ ያነሰ ምን ቅሌት አለ ?
የጥላ ሁሉ ጥላ ነው ፥ ከቅሌትም የቀለለ ።

ጎምሌት
ለእግዚአብሔር ምን ይሳነዋል ? ለጥላም ጥላ ያበቅላል
ለልክስክስም ልክስክስ ፥ ለለማኝም ለማኝ ፈጥሯል ። . . . .
በሉ ችሎት መሄዴ ነው ፥ ከሰው ጋር ቀጠሮ አለኝ ፤

ገድለ ስምዖን
. . . እዚሁ እንጠብቅሃለን ።

ጎምሌት
አትጠብቁኝ እባካችሁ ! . . .
ካሽከሮቼ እኮ አልቆጥራችሁ
እናንት ወዳጆቼ ናችሁ ። . . . .
ይመስገን የሰማይ አባት
የሚጠብቀኝ ሰው ብዛት
በጓደኝነት ጥላ ሥር ፥ በወዳጅነት መስተዋት . . . .
የመጣችሁበት ጉዳይ
ምንድነው እኮ ሳንወያይ . . . .

ሮዘንቅሮስ
ልዑል ጌታዬን ልንጠይቅ ፥ በሰላም መሆንክን ልናይ ፤

ጎምሌት
አዬ የኔ ነገር ፥ ባለኩ
እግዜር ይስጥልኝ ማለትን ፥ እንኳን ነፍጌያችሁ ዝም አልኩ ፤ . . . .



አልተላከባችሁማ ? በፍቃዳችሁ ነው ያልከኝ ?
ነፃ ጉብኝት ነውና ? ልትጠይቁኝ ? በል ንገረኝ ?

ገድለ ስምዖን
እምንነግርህ ምኑን ነው ? እምትፈልገው ለማወቅ ?

ጎምሌት
ምን መቸም ያሻህን ነዋ ! . . . ፍሬ ነገሩን ሳትለቅ ! . . .
ፈቅዳችሁ መምጣታችሁን ፥ በግል እኔን ለመጠየቅ ። . . . .
ምነው ግንባርክን አላበህ ? አይዞህ ኮስተር አርገህ እየኝ
ተልኮብህ መምጣትህን ፥ እያፈርክ ፥ አታስጠርጥረኝ !

ሮዘንቅሮስ
ለምን ጉዳይ ጠሩን ብለህ ፥ ነው እስከዚህ ያስጠረጠረህ ?

ጎምሌት
የሱን መልስ አንተ ታውቃለህ ። . . . . 'ሕፃን በነበርኩ ጊዜ እንደ ሕፃን እጫወት ነበርኩ ፤ ' ማን ነበረ እንዲህ ያለው ? . . .
ምን ይረባል ! 'ሁሉ ያልፋል ፥ ሁሉ ያልቃል ፤' ይኸንነስ ማነው ያለው ? ምን ያረጋል ! ምን ይረባል ! . . . ስሙኝ ምሥጢር ላጫውታችሁ ፤ ምሥጢሬን አሳልፋችሁ ፥ ለንጉሡም ለንግሥቲቱም ፥ መዘርገፍም ካለባችሁ ፥ ዘክዝኩት ይሁን ግድ የለም ፥ በኔ ሳቢያ እንዳይነክሷችሁ ፤ . . . . መታሰቢያ በረከት ነው ፥ በነጻ የምሰጣችሁ ፤ . . . 'ሕፃን በነበርኩ ጊዜ ፤እንደ ሕፃን እጫወት ነበርኩ ፤' ማን ነበረ እንዲህ ያለው ? . . . ሰማችሁኝ ወዳጆቼ ፥ ከቀን በኋላ የመጣ ፥ ስም የሌለው አዲስ ሕመም ፥ አስተያየቴን ዘርፎኛል ፤ ባሕሪዬን ባሕር ከቶታል ፤ ፍቃዴ እንኳ ተሳክሮብኝ ፥ ይቺ ፍሬያማ እናት ምድር ፥ ይቺ ማጎፀነ ዝጉርጉር ፥ መካን ምድረ በዳ ሆና ፥ ይህ የሕይወት እስትንፋስ ዓየር ፥ ይህ የመብራት ማሾ ጥበብ ፥ የዚች ያዳራሽ ሠገነት ፥ የጣራው ጌጣ ጌጥ ንድፍ ፥ አንዳች ትርጉም አይሰጡኝም ፥ በእንፋሎት ውስጥ የሚማስን ፥ ሠራዊት ነው የሚመስለኝ ፤ . . . ሰው ፥ የትንግርት እጅ ሥራ ፥ የአስተያየቱ ተአምር ፥ ተሰጥዎው ወሰን የሌለው ፥ ቁመናውና ሁናቴው ፥ የሚደነቅ ትርጉም ያለው ፥ ግብሩ የአማልክት የሚመስል ፥ ጥልቀቱ ለእግዜር የሚቀርብ ፥ የዓለም ውበት መጨረሻ ፥ የፍጡራን ሁሉ በላይ ፤ ግና ለኔ ወዳጆቼ ፥ ብኩን የዐመድ ረመጥ ነው ፤ . . . የሰው ዘር ጣዕም አልቆልኛል ፤ አንዳችም ትርጉም አይሰጠኝ ፤ . . . ባጉል ፈገግታህ ነገሬን ፥ እንደናቅህ እንኳ ባውቅም ፥ ለኔ አልቆልኛል የሰው ጣዕም ።

ሮዘንቅሮስ
ኧረ ምን ቆርጠኝ ጌታዬ ፥ ከቶ የንቀት አደለም

ኀምሌት
ለሰው ጣዕም የለኝም ስልህ
ምነው ታድያን መገልፈጥህ ?

ሮዘንቅሮስ
ዛሬ የጋበዝካቸውን ፥ ተዋንያን እመንገድ ላይ ፥ ወዲህ ሲጓዙ አይተናቸው ፤ ለሰው ጣዕም የለኝም ስትል ፥ ለምን እንደጋበዝካቸው ፥ ማወቁ ስላቃተኝ ነው ፤ ምክንያቱም የተዋንያን ፥ የሞያቸው ፍሬ ነገር ፥ የሰውን ዘር ጣዕም ጥልቀት ፥ ማድነቅ ፥ ማነጻጸር ፥ መንቀፍ ፥ ሕይወትንም ማንጸባረቅ ፥ ነው ፥ ስለሚባል ገርሞኝ ነው ፤ . . . .

ኀምሌት
መጥተዋላ ! ጥሩ ወሬ ! . . .
ሳቅህ መስሎኝ በነገሬ . . . እንደ ንጉሥ ተመስሎ ፥ የሚጫወተው ነው ድንቁ ፤ እጅ መንሻ አዘጋጃለሁ ፥ ለግርማዊነቱ ብቁ ። መጥተዋላ ! ጥሩ ወሬ ! . . . ሜረኛው ባለሚል ደሞ ፥ ያመፅ ልብሱን ያጠልቅና ፥ . . . አፍቃሪው ጐልማሳ ይልቅ ፥ ብቻ አሁን ለኔ ሲጫወት ፥ ‘ ውዳሴ ላንቺ ’ እንዳይል ! ያ ደሞ የቀልዱን ክፍል ፥ የሚጫወተው ልጅ እግር ፥ መጨረሻውን ያሳምር ፥ . . . ድንክየው ይምጣብኝ ይልቅ ፥ ብቅ ሲል ጦሽ እሚሉትን ፥ እነሱ እነሱን ያሳስቅ ! . . . . ቆንጆይቱ ወይዘሪት ግን ፥ ትናገር ያፈቀዳትን ፥ አለዚያ ውርድ ንባቧ ፥ ተቀርቅሮ ይቀራል ልቧ ፤ . . . ቶሎ ይደርሱ ይሆን ሰዎች !

ገድለ ስምዖን
የት ይቀራሉ ብለህ ነው ? የከተማው አዝማሪዎች !

ኀምሌት
ያንተም ሞያ ይሻል ብለህ ፥ ይሆናል እኮ ከነሱ ?

ሮዘንቅሮስ
እንዲያውም ይኸው ደረሱ ፤

ኀምሌት
እንግዲያስ ትቻችሁ ልሂድ ፥ በሉ ከቀናችሁ በርቱ ፥ እኔም እንግዶች አሉብኝ ፥ ታዝዘው የመጡብኝ ሳይሆን ፥ ጋብገርቸው የመጡልኝ ፤ . . . ግን ንጉሡም ፥ ንግሥቲቱም ፥ ሞኝነታቸው አይሰማ ፤

ገድለ ስምዖን
ማን እንዲህ አለኝ ልትል ነው ? ሞኝ ሆኑ ብሎ ማን አማ !



ኀምሌት
ከዕብድም ዓይነት አለው ፥ ያማ . . . .
ዕብድ ሁሉ ዝፍጥ አደለማ ።
—ጶሎኔዎስ በሩቅ ይታያል—
እዩልኝ ያን አሮጌ ልጅ ።

ሮዘንቅሮስ
መታደል ነበር እሱማ ፤ መንሰልጀጅ ዳግመኛ ሕጻን ፥ መሆን ነው ሲሉም አልሰማህ ?

ኀምሌት
እውነት እኮ ይመሳሰላል ፥ ቀራብ ነው በብዙ ነገር . . . .
በቅዘን መበስበስ ቀርቶ ፥ በሃሳብ መበስበስ በስተቀር ፤ . . . .
ለወሬ ምክንያት አገኘ ፥
መጣ እንግዲህ ሊሠትረኝ
—ጶሎኔዎስ ይገባል—

ጶሎኔዎስ
ጌታዬ እምነግርህ አለኝ ፤

ኀምሌት
‘ ጌታዬ እምነግርህ አለኝ ! ’ . . . ሮዜዎስ የሮም ተዋናይ . . . .

ጶሎኔዎስ
አዝማሪዎቹ መጥተዋል ።

ኀምሌት
ፑፍ - ፑፍ - ፑፍ - ፑፍ . . . .

ጶሎኔዎስ
ኸረ እውነቴን ነው ልዑል ፤ ለአሳዛኝ ሆነ ለአስቂኝ ትርኢት ፥ ለታሪካዊ ፥ ለሕብረ ሰብአዊ ፥ ለሃይማኖታዊ ፥ ለአሳዛኝ ታሪካዊ ፥ ለአሳዛኝና-አስቂኝ ምስቅልቅል-በታሪክ-አቀፍ-ሃይማኖታዊ-ትርኢት ፥ በክራር ፥ በመሰንቆ ፥ በዋሽንት ፥ በእምቢልታ ፥ በዘፈን ፥ በሆያ ሆዬ ፥ ማን አህሎዋቸው ! ሲኔካም እንደነሱ አላሳዘነ ፥ ጵላጥዮስም እንደነሱ አላሳቀ ።
የሞያን ጸጋ የተካኑ ናቸው ።

ኀምሌት
ዮፍታሔስ የእሥራኤል አፈ ንጉሥ ፥ ምን ጸጋ እንደነበረው ታውቃለህ ?

ጶሎኔዎስ
ምን ጸጋ ነበረው ጌታዬ ?

ኀምሌት
ከበቂ በላይ የሚወዳት አንዲት ሴት ልጅ ብቻ ነበረችው ።

ጰሎኔዎስ
አሁንም እዚያው ?

ኀምሌት
ተሳሳትኩ እንዴ አፈ ንጉሥ ዮፍታሔ ?

ጰሎኔዎስ
ዮፍታሔ ካልከኝ ልዑል ፥ እኔም ከመጠን በላይ የምወዳት አንዲት ሴት ልጅ አለቺኝ ።

ኀምሌት
ኤጭ ! የነገሩ አመጣጥ እንዲህ አደለም ።

ጰሎኔዎስ
ታድያን እንዴት ነው አመጣጡ ልዑል ?

ኀምሌት
ሲመጣ ታገኘዋለህ ።

—ተዋንያኑ ይገባሉ—

ጰሎኔዎስ
እንዲያውም ያው አንዱ መጣ ።

ኀምሌት
የመጣው ነገር አደለም ፤ ምነው ሞያ ነው ብለሽኝ ። . . . .
ጐበዛዝ እንኳን መጣችሁ ፥ እንኳን መጣችሁ ጌቶች ፤ . . . አለህ እንዴ አንተ መሆኑን ? ምን በደልኩህና ሸሸኸኝ ! . . . . ምነው ገጽህን ጢም ዋጠው ? መርዶ አለ እንዴ ምድረ-ዴን ውስጥ ? . . . አንቺም ሰላም እመቤት ፥ ብቻ አደራ ያ ድምፅሽ ፥ ዙሪያ ጥምጥሙን ሲዋትት ፥ እንደ ንክር ወርቅ እንዳይነክት ፤ . . . ብቻ እንኳን መጣችሁልኝ ፤ . . . ያን የጭንቀት ንግግርክን ፥ ግለኛ መነባንብክን ፥ እስቲ አንደዜ ውረድልኝ ፤

መሪ ተዋናይ
የትኛውን ይሆን ልዑል ?

ኀምሌት
ምነው ያኔ ወጥተህልኝ ፤ ትርኢቱ እንኳ አልታየም ። አንደዜ ታየ መሰ ለኝ ? . . . አዳሚን አላስደሰተም ፤ ለአህያ ማር አይጥመውም ፤ . . . . ግን ድንቅ ነበረች ታድያን ፥ ትዕይንቱን አመንኝርከው ፥ ሆያ ሆዬም ሳያ ደርጉት ፥ የምሥጢሩን መንፈስ ብቻ ፥ ለይተው እያበሰሩ ፥ እንደሷ ከቶም



አልሠሩ ፤ . . . አንድ ወዳጄ እንኳ ምን አለ ? . . . አዎን ፥ ጣዕሙ እስ ኪጐመዝዝ ፥ ቅመም አላበዙበትም ፤ ደራሲውም ለመራቀቅ ፥ ከፍሬ ሃሳቡ ሸሽቷል ፥ የሚያሰኝ ቃል አልነበረም ፥ . . . ነበረ መሰለኝ ያለው ። በተ ለይ አንድ እማልረሳት . . . ኢናዮስ ለዲዮዶስ ፥ ስለፒሪያም መታረድ ፥ በምታዋይበት ምንባብ . . . እንዴት ነበር የጀመርከው ? ቆየኝ ቆየኝ . . . አዎን . . . ‘ ደልጋ አንበሳ መሰል ፖይሩስ ፥ አይበገሬው ሻካራ ’ . . . የለም ቆየኝ-ቆየኝ-ቆየኝ . . . .



. . . ትርኢቱ እንኳ አልታየም ። አንደዜ ታየ መሰለኝ ?

‘አይበገሬው ሻካራ ፥ እንደ ቂሙ ጥቁረት አንጻር
ድፍን ጥቁር ጥሩር ለብሶ ፥ መስሎ የመልአከ ሌት ጣር
ፖይሩስ ልበ መራራው ፥ ቀልሞት የገጹን ገላ
አድፍጦ እንደ ዳልጋ አንበሳ ፥ በእንጨት ፈረስ ሠረገላ
ጥሩሩ ልቡና ልብሱ
ፊቱም ጨልሞ እንደነፍሱ
ቂም አርግዞ በቀል ሲያምጥ ፥ ሊገላገል ጣር ከማለም
አእምሮው ላይ ከዘመተው ፥ ካባት ከናት ከወገን ደም ፥
መልክና ትዝታቸውን ፥ በልቦናው እያብላላ
በጥርሱ ሞት ነክሶ ሲበር ፥ ተመርቶ በበቀል ጥላ

በወገኖቹ የደም ድምፅ ፡ በታፈኑበት የግፍ ግፍ
ዓይኑ እንደ እባብ መርዝ አብቅሎ ፡ ዘርግቶ የጣዕረ ሞት ክንፍ
የደምን በደም መጠታብ ፡ ፒሪያም እናቱ ላይ ሊጽፍ
መርዙን ነቅሎ እንዲያገኝ እንቅልፍ’ . . . .

ጶሎኔዎስ
ሠናይ ፡ ሠናይ ፡ ይበል ፡ ይበል ፡ . . . እንዲህ አርጐም የለ ልዑል
ቃሉም ፡ ድምፁም ፡ አሰካኩም ፡ ሲስማማ እንደ ጨዋ ልጅ ውል ፤

መሪ ተዋናይ
. . . ‘ መርዙን ነቅሎ እንዲያገኝ እንቅልፍ . . . .
አተኩሮ እንዳደፈጠ ፡ የጦር አምላክ ምሱን ሲልፍ ፡
አየው ፒሪያም ግሪኮችን ፡ ወገኖቹን ሲጨፈጭፍ ፤
አንቲካ ሳንጃው ለክንዱ ፡ እንዳሻ አልታዘዝ ብሎት
እተነከረበት ደም ውስጥ ፡ አቦዝኖ አዝለፍልፎት ፡
ምንም ፒሪያም ቢሸመግል ፡ አቻ አትመርጥምና በቀል
አሽቆልቁሎ አጥለቀለቀው ፡ እንደ ድንገተኛ ደለል
አጣቅሶም እንደደረሰ ፡ ሳንጃውን እንዳንጣለለ
ምድሩ በሞገድ ተናጋ ፡ ክንዱ በነጐድጓድ ዛለ
ፒሪያም መብረቁ አስደንግጦት ፡ ሳይቀጥፈው ተፈነገለ ፤
የፒሪያም ጋሻ ጃግሬም ፡ ቀትረ ገታራው ኢሊያም
አሾልቆ ፡ ተጐትቶ ፡ እንደ ወረርሺኝ አሲዳም
ፓይሩስ ከቶ ሳያየው
ቀኝ ጆሮውን በጠሰው ፤
ፓይሩስ በፒሪያም አናት ላይ ፡ የቃጣበት የቂም መብረቅ
ሳይወርድበት ዘንጠፍ አለ ፡ በሕመም ትንፋሹን ቢነጠቅ ፡ . . . .
ሰቀቀን ገርገብ እንደሚል ፡ በሁለት ነጐድጓድ ማህል
ነፋስ ሽውታው ተሰልቦ ፡ ምድር እርጭ እንደምትል
የሱም ስሜት እንደሞተ ፡ እንደተዳፈነ ያህል
ፍቃዱ እንኳ ባይዘነብል
ላንድ አፍታ ተነብዞ ቀረ
ቆሌው እንደተሰተረ ፤
ሆኖም በቀል የፀነሰ ፡ እንደሚያገረሽ ውሎ አድሮ
መርዙን በሃሞቱ ቀብሮ
የፓይሩስም ማንጐላጀት ፡ እንደዘበት መሽቶ ነጋ
ጠፈር ያዘለው ነጐድጓድ ፡ መብረቁ ምድር እንዲወጋ
እንደቀጠቀጧት እባብ ፡ አፈር ልሳ ትቢያ ምጋ
ከሞት ነቅታ ሞት ልትተፋ
ልታደፍጥ እንደምትጠፋ



ፖይሩስም እንደ ዛር ልክፍት ፡ ነዝሮ ፡ በርግጐ ፡ ተግ አለ
ክንዱ ከመልአከ ሞት ፡ መቅሰፍት እንደተቀበለ
ተውዘግዝጐ ፒሪያምን ፡ ደም አስክሮ እንዳበረረው
አስገምግሞ ተረከከው ።
የብረት ጥሩሩን ጐርዳ ፡ ሰይፉ ከእጁ ተለግታ
ሲያል እንደሆነች እንጂ ፡ ምድር የመጣች ተፈትታ
ፍላፃም እንደዚህ አይወርድ ፡ መብረቅም እንዲህ አይመታ ፤ . . . .
እናንት ነዋሪ አማልክት ፡ ምነው ዕድል አትዳኙም ?
ሥልጣኗና ሕግጋቷ ፡ ማፍረስ እንጂ ምነው አይፈርስም ?
ፈተና መስደድ ነው እንጂ ፡ ፈተና አትሰደድም ? . . .

ጶሎኔዎስ
አዬ ፡ ዝብዝቡ በዛ ! አይ አ—አይሆንም ፡ የለ አይሆንም !

ኀምሌት
የበዛውስ ሪዝህ ነበር . . . .

—ተዋናዩን—

አንተን ባይሰማህ ይሆናል ፡ ትዝ ብሎት ተረብ ነገር
መቸስ ሰው አፉ እንኳ እንዳይሸት ፡ አልፎ አልፎ መናገሩ አይቀር ፤
ዕቁባ ጋ ድረስ ቀጥል
ትርኢቱም እንዲኖረው ውል ።

መሪ ተዋናይ
. . . ‘ ማን አየ ! እግዚኦ ማን አየ ! የንግሥት ዕቁባን ሲቃ
ነበልባሉን ለመቀነስ ፡ በባዶ እግርዋ እስኪነቃ
ስትወጣ ፡ ስትወርድ ፡ ስትከንፍ ፡ ጦር እሳት ላይ ስትንቃቃ
ዘውድ የደፋችበት ራሷን ፡ በመቀነቷ ጠቅልላ
ጋቢ ብጤ አሸርጣ ፡ ድንጋጤ ጭምር ዝላ
እንኳን የንግሥት ግርማ ፡ ርቋት ያልባሌ ጥላ
ይኸን አይቶ ያላዘነ ፡ ለመከራ ወድቃ ተድላ
የዕድልን አለመዳኘት ፡ በልቦናው ያላብላላ
አንገቱን ያልደፋ ጀግና ፡ ማን አለ ፡ እግዚኦ ማን አለ !
ዕድል ትፈተን ያላለ !
ወዲያው ፖይሩስ በጥሩሩ ፡ እንደ ቁጡ መንፈስ ሲከንፍ
ሰቀቀን ያዘለ ዓይኗ ፡ ተርገብግቦ አብሮት ሲሰፍ
የባልዋ የፒሪያም አካል ፡ እንደ ወርካ ሲዘነጠፍ ፤
ማን ነበረ ! ሕቅ ! ያላለ ፡ አብሯት ያልሞተ መንፈሱ
የሰማይ መላእክት አብረው ፡ እንኳንስ ሥጋ ለበሱ

በሐፍረት ልቦናቸውን ፣ ምንኛ እንደቀለሱ
ከዳኝነት ወምበራቸው ፣ ወርደው እንዳላለቀሱ
ሁሉ በረቂቅ ምግባሩ ፣ ምሥጢር እንዳልተወያየ
ዕድል ትፈተን እያለ ፣ ወደ ላይ እንዳልጸለየ
ማን አየ ! እግዚኦ ማን አየ ! . . .

ጳሎኔዎስ
የምርህን እንባ አነቀህ ? እኔም አዘንኩ ረስቼ
ቧልት መሆኑን ዘንግቼ ፤

ጎምሌት
አዎን ፣ ቧልቱን ዘንጋውና ፣ ተገቢ መቆያ ሥፍራ
እንድትሰጥልኝ አደራ ፤

ጳሎኔዎስ
እሺ ልዑል ፣ . . . እሺ ልዑል ፤

ጎምሌት
እግዚአብሔር ይስጥልኝ ጉበዝ ፤ በሉ ተለማመዱና
ንጉሡ እንዲያዩላችሁ ፣ እለምናለሁ ይጠናና ፤
መስተንግዶውን አደራ ፣ ጳሎኔዎስ እወቅበት . . . .
ረቂቅ መናፍስት ናቸው ፣ ነዋሪ የጊዜ መዛግብት
ከሞትህ በኋላ ስምህ ፣ ይሻላል ዕድፉ ቢታተት
በቁም ከሚጫወቱበት
ተርጉመው 'በቧልት' አንደበት ።

ጳሎኔዎስ
እሺ ልዑል ፣ . . . ኑ ጌቶቼ
ተከተሉኝ ወዳጆቼ ።

—መሪው ተዋናይ ሲቀር የቀሩት ተዋንያን ከጳሎኔዎስ ጋር ይወጣሉ—

ጎምሌት
ሰማኸኝ ወይ አንተ ጉበዝ ፣ . . . ስለ ጎንዛጎ አገዳደል . . . .
ነገ አንተ ብትጫወተው ፣ ደኅና ታዋጣለህ ልበል ?

መሪ ተዋናይ
ልዑልነትዎ ካዘዙኝ
እሞክራለሁ ደስ እያለኝ ፤

ጎምሌት
አሥር መሥመር ታህል እኔ ፣ ጽፌ አክልበትና
አጥንተህ እናያለና ፤ . . . .



በል ቶሎ እኒያን አዛውንት ፣ ተከተል ሳይሠወሩ
ምናልባት ባሕሪያቸውን ፣ ተመስላችሁ ብትሠሩ
መመሰሉ ላይ ደግ እንጂ ፣ ለመሆን ግን እንዳትጥሩ ፤ . . . .
በሉ እናንተም ወዳጆቼ ፣ እስቲ በሰላም እደሩ ።

—መሪ ተዋናይ ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ይወጣሉ—

. . . . ምንድነኝ ? ምን ጉድ ነኝ እኔ ? ምን የእርግማን ቋት ነኝ እኔ ?
መከራ ለሰፈነባት ፣ ለዕድሌ ይብላኝላት ፣ መጥኔ . . . .
አሁን ይህ ተአምር አደል ? . . . አንድ አልባሌ ተጫዋች ፣
ልቡ በተረት ተጠቅቶ ፣ ሲሰቀቅ ፣ ሲያዝን እንደ አንዳች ፣
በሥነ ጽሑፍ የሕልም ዓለም ፣ መላ መንፈሱን አዝፍቆ
ቀልቡ በስሜት ተሰርቆ
ዓይኑ በእንባ እንክብል ታንቆ
ጭብጥ ኩርምት እያለ ፣ ድምፁን በሲቃ ተነጥቆ ፤ . . . .
ለምንድነው ? ለምን ፋይዳ ? ለዕቁባ ነው እንዲህ የባባ ?
ዕቁባ ለሱ ምኑ ናት ? ወይንስ እሱ ለዕቁባ ?
እንዲህ የሚጨበጥ በእንባ . . . .
ጉዴን ቢያያትስ እንግዲያ
የኔ እርግማን ቢሰፍንበት ፣ ቀምሶ ከዕድሌ መለኪያ
ለሷ እስከዚህ የደረሰ ፣ በኔስ እንዴት ይሆን አያ ?
መድረኩን በእንባ ባጠበው ፤
የተመልካቹን ሕሊና ፣ ጣጣዬ እስኪዘገንነው ፤
በደለኛውን አብሽቆ
ደገኛውን አስጨንቆ
አላዋቂውን አስቆ
ያይንና የጆሮን ምግባር ፣ በጥበቡ አስደንቆ ፤ . . . .
ዳሩ የኔን ጉድ የት አውቆ ! . . .
ኧረ በበለስ ምንድነኝ ፣ አቅል የሌለኝ እንዝህላል
እንኳንስ ሸባ ጫንቃዬ ፣ ነፍሴ የማትችለውን ቃል
ለመለኮት ውል ገብቼ ፣ የደሙን በቀል ለፍፌ
ያለ አንድ እቅድ እርጭ ስል ፣ እንደረኸጥ ተዘፍዝፌ
ኧረ በበለስ ምንድነኝ ! . . . ያልጫ ይሆን ሃሞቴ ?
አጉል ፍጡር ነህ የሚለኝ ፣ የልቤን ብኋል በሞቴ ?
ሞራ ገላጭ ነህ ልበለው ? . . . አፌስ ላይ አክ እትፍ ቢል !
ቢዘልፈኝስ ? ቢጠፋኝስ ? እኮ ምን አባቴ እንዳልል ! . . .
አባቴ ? የምን አባቴ ? . . . ምን ከፋኝ እርሙን ካጣጣምኩ
እንደ ወንዶች ሱሪ አጥልቄ ፣ አብሬአቸው ከተሰለፍኩ
ሃሞተ ዝቃጭ መሆኔን ፣ ከሸፈንኳት እያሸቃበጥኩ ፤

ልምሰል እንጂ ከሰው እኩል
እጣቢ መሆኔ ቀርቶ ፣ የሰው አጉል ፣ የወንድ አጉል . . . .
ደሞ እኔን ብሎ ደም መላሽ ! ደሞ እኔን ብሎ ልዑል . . . .
በቀሉ ቀርቶ አፌን ላሹል . . . .
በቀል ? አዬ በቀል !
ጀግና ጠፍቶ ፣ ወንድ ጠፍቶ ፣ እኔ ጫንቃ ላይ ይተከል ? . . .
እሱን ጊዜ ይፍታውና ፣ ይልቅ የተውኔቱ ጉዳይ
ያስገኝ ይሆን ዘዴ መሳይ ?
ከተመልካች ጋር ሲያስተውል ፣ የዓመፅ ግብር ተካፋይ
ጉዳዩ ሲቀነቅነው ፣ ፊቱ ሲታየው በደሉ
የጎነተሉት ይመስል ፣ በርግጎ ቱግ ይላል አሉ ፤
ቱግም ባይል መቁነጥነጡ ፣ አይቀር ይሆናል ለዓመሉ ።
የገዘተኝ ጽኑ መንፈስ ፣ በጤና እስከዚያ ቢያደርሰኝ
ወይም ያጂያቆነኝ ሰይጣን ፣ መቸም ሳያቀስ አይለቀኝ
ገፋፍቶ ለዚያ አብቅቶኝ ፣ መሳለቂያ ባያደርገኝ ፤ . . . .
ደካማነቴ አያዘልቅም ፣ መንፈሰ ርኅሩኅነቱ
አላዋጣም መባባቱ ፣ . . . .
ለነገ ያብቃን ፣ ለማተቱ ፣
ፍሬ ነገሩ ፣ ተውኔቱ ፤
የነፍስ ገዳዩ ወጥመድ ፣ የሌባ ያሽ መድኃኒቱ ።

—ይወጣል—



# ገቢር ሦስት

## ት ፡ ፩

—ንጉሡ ፤ ጰሎኒየስና ወፌ-ይላ ይገባሉ—

ጰሎኒየስ
አንቺ ይህን መጽሐፍ ገልጠሽ ፣ ዞር ፣ መለስ ፣ ገልመጥ እያልሽ ፣ የተመሰ ጥሽ አስመስለሽ ፣ ብቸኝነት የተሜነሽ ፣ እያስመሰልሽ ድገሚ ፤ እንግዲህ ግርማዊነትዎ ፣ እኛ ሸሸግ ብለን እንጠብቅ ። ተብሎ ያለተለት ነው ። የታማኝን ገጽ ለብሶ ፣ ልበ ቀና ጭምት መስሎ ፣ እንኳንና የሰውን ልጅ ፣ ሰይጣንን ያስቷል አሉ ።

—ጰሎኒየስ ይሸሸጋል—

ንጉሥ
ምንኛ እውነት ነገረኝ !
ንግግሩ ሽምጥጥ አርጎ ፣ ሕሊናዬ ላይ ገረፈኝ ።
የጋለሞታ ደም ግባት ፣ በቅባት ፣ በክርቢ ታጥኖ
የኔን አድራጎት ይመስላል ፣ በቃላት ሽታ ታፍኖ ።
ምንኛ ከባድ ጭነት ነው
ጫንቃዬ ላይ የሠፈረው !

—ንጉሡ ይሸሸጋል ። ኀምሌት ከፋቅ ይገባል—

ኀምሌት
መሆን ፣ ወይም አለመሆን ፣ እዚሁ ላይ ነው ችግሩ ፤
የዕድል የፈተና አለንጋ ፣ ሲወናጨፍ ወስፈንጥሩ
በሃሳብ ግርፊያ መሰቅየቱን ፣ ችሎ ታፍኖ ማደሩ ?
ወይስ ፣ የመከራን ማዕበል ፣ ተጋፍጠ ፣ ጦርን ከጦሩ
ተጋትሮ ፣ ወግቶ ድል መምታት ፣ እስኪነቅል ከነሥሩ ፣
የቱ ነው ለሰው ልጅ ክብሩ ? . . .
መሞት ፣ መኛት ፣ ማንቀላፋት ፣ እስከ መቼም ባለመንቃት
ከስንቱ ቆሸት መቃጠል ፣ ማምለጥ ፣ ሰው ከመሆን ሥጋት
ያሚጸለይለት ሲሣይ ነው ፣ የምኞት ሁሉ አናት ፤
ለእንቅልፍ ሲባል መሞቱ ፣
በሞት እፎይታን ማግኘቱ ፣

የሰላም ሕልም ማየቱ . . . .
ሕልም አልኩ እንዴ ? እሱ ነው ጉዱ ፣
በሞት የእንቅልፍ ዓለም ደሞ ፣ የሕልም ወግና ሽጉዱ ፣
ቢኖር ፣ የሰላምን ድባብ ፣ የጸጥታን እሽሩሩ
የሚያውክ ዓይነት አይሆንም ፣ ይታገዳል መጣረሩ ፤
ይኸ ሟች ፣ ጉፋያ ሥጋ ፣ ሲደመደም መቃብሩ
እዚያ ላይ ይገታል ክብሩ ፤
ኑሮ የሚሉት ውጥንቅጥ ፣ እንቅልፍ ላይ ነው ድንበሩ ? . . .
የጊዜን ግልምጫ አለንጋ ፣ ለምን ይዘልቋል ተገርፎ
ያጥቂን ጥቃት ተሸክሞ ፣ በትዕቢተኛ ተዘልፎ
በዳኝነት እጦትና ፣ በቀጠሮ ተለማምጦ
በተናቀች ፍቅር ቁርጠት ፣ በሕልውና አምጦ
በሥጋ ግብር ተዋርዶ ፣ በአንደበት እልፊት ተዘልፎ
በደጅ ጥናት ወግና ፣ በመተያያ ተገፎ
በአስተሳሰብ ተቆልፎ
የጊዜን ግልምጫ አለንጋ ፣ ለምን ይዘልቋል ተገርፎ ?
ወደ እንቅልፍ ዓለም አምልጦ ፣ ከዚህ ጣጣ ለመገንጠል
በገዛ እጅ ፣ ባንዲት ጩቤ ፣ ሲቻለን ለመገላገል ? . . .
ግና ፣ ከሞትስ ቀጥሎ ፣ ከእንቅልፍስ ዓለም ባሻገር
ምን አለ ? የሚሉ ስጋት ፣ የተፈጥሮ መጠራጠር ፣
ከዚያች ካልታወቀች አገር ፣ ዓይነ ሥጋችን ካላያት
የሄደባት መንገደኛ ፣ ከቶ ካልተመለሰባት
ፍቃዳችን እያቅማማ ፣ እንቅልፍ ዓለም ከመሰደድ
ያዘወተርናትን ፍርጃ ፣ እያስታመምን መለማመድ
መርጠን መሆኑ አይሳትም ፣
ያልታየ አገር አይናፍቅም ፣ ቢያስኝም አይታወቅም ፤ . . . .
በምናውቀው ስንሰቃይ ፣ የማናውቀውንም ፈርተን
በሕሊናችን ማቅማማት ፣ ወኔአችንንም ተሰልበን
ከዕለት ወደ ዕለት ተስበን ፣ ከአባቶች በወረስነው ጋድ
እያደቀቅን ፣ እየደቀቅን ፣ መጓተት በጥንቱ ልማድ
በሃሳብ ጭጋግ ስንዋኝ ፣ መንፈስ ንቁነት ጥቅሙ
የአድራጐት ምግባር አምሃ ፣ የመንቀሳወስ አቅሙ
እያደር ከሕሊናችን ፣ ይደመሰሳል ትርጉሙ ።
ሰው የመሆን ሕመም ሥሩ
የመኖር ወይ ያለመኖር ፣ እዚሁ ላይ ነው ችግሩ ። . . . .
ወፌ-ይላ ፤ . . . ወፌ-ይላ . . . .
ሰዎች እስዋው ናት ? ወይንስ ፣ የስዋ ተመሳሳይ ሌላ ? . . .
ጣዖት እስዋን ተመስላ ? . . .



በጣዖቷስ መቅደስ መዝገብ . . . .
ኃጢአቴ ሁሉ ይታሰብ

ወፌ-ይላ
እንደምን . . . ሰነበትክ ልዑል ? . . . ደኅና ?

ኀምሌት
ደኅና ፣ ደኅና ፣ ደኅና ፤

ወፌ-ይላ
ልዑል ፣ . . . ብዙ ጊዜ ስፈልግህ ፣ ነበር ለብቻህ ላገኝህ . . . .
የላክልኝን ስጦታ ፣ አስቤ ልመልስልህ . . . .
ተቀበለኝ እንካ ባክህ . . . .

ኀምሌት
ስጦታ ? . . . ምን ስጦታ ነው ?

ወፌ-ይላ
እንዴ ! ምነው እያወቅኸው ? . . .
ያውም የሰላምታ ቃላት ፣ ሊዘነጉ የማይችሉ
ከስጦታህ ጋራ አብረው ፣ . . . እስካሁንም ድረስ አሉ ፤ . . . .
ሰጪው ጭካኔ ካበዛ ፣ . . . መንፈስ ጨዋ ነኝ ለሚል
በተለይ የሃብታም ስጦታ ፣ መደለያ ነው እሚመስል ፤ . . . .
ባክህ ተቀበለኝ ልዑል ።

ኀምሌት
ሃ - ሃ - ! . . . ታማኝ ሴት ነሽ ?

ወፌ-ይላ
አቤት ?

ኀምሌት
ቀና ሰው ነሽ ?

ወፌ-ይላ
ምን ማለትህ ነው ፣ . . . ጌታዬ ?

ኀምሌት
ታማኝ ከሆንሽ ፣ ቀና ከሆንሽ ፣ ታማኝነትሽ ለቁንጅናሽ ከቶ ምሥጢር እንዳታካፍላት ።

ወፌ-ይላ
ከማን ጋር ትወያይ ብለህ ? ቁንጅና እኮ ፣ እንደታማኝነት የልብ ወዳጅ የላትም ።

**ኀምሌት**
ነው ፤ አዎን ፤ ምክንያቱም ፣ የታማኝነት ፍልስፍና ቁንጅናን አግባብቶ በእምነት መንገድ ከሚያራምዳት ይልቅ ፣ የቁንጅና ሥልጣን ታማኝነትን አሞካሽታ ወደ ጅልነት ትለውጣታለች ብንል ይቀላል ። ይኸ ፣ ጥንት ተረት ነበር ። ዛሬ ግን ቋሚ የየዕለት ታሪክ ነው ። እኔም ፣ ቀድሞ ፣ አንደዜ ፣ ወድጄሽ ነበር ።

**ወፌ–ይላ**
እኔም አምኜበት ነበር ።

**ኀምሌት**
ባላመንሽ ይበጅሽ ነበር ። ማለት ፣ ዘጠኝ ጊዜ መታደል የቀድሞ ትግዛታችንን አግማ አዲስ ልታደርጋት አትችልምና ፤ በትግዛታዋ ናፍቆት ብቻ በሰመመን እንታደስ ይሆናል እንጂ ፤ . . . . ወይም እንዲያውም አልወደድኩሽ ነበር ይሆናል ።

**ወፌ–ይላ**
ስታብለኝ ኖሯላ ኀምሌት ?

**ኀምሌት**
ቆብሽን ጭንሽ ገዳም ግቢ ! ምን በወጣሽ የኃጢአት ፣ ፈልፋይ ሆነሽ ትቀሪያለሽ ። እኔም ቀና ነኝ እንኳ ብል ፣ ለይስሙላ ባደረግሁት ፣ ለዓምላክ ጉቦ ቅንነት ፣ በግብዝ መንፈሴ ድፍረት ፣ ምነው ከቶ ባልተፈጠርኩ ፣ በሚያሰኝ ሕገ ወጥነት ፣ ሕሊናዬ ይከሰኛል ። . . . . አየሽ ፣ ኩሩ ነኝ ፣ ቂመኛ ፣ ዕቡይ ፣ ያፈነኝ እልህ ብዛቱ ፣ ከማከማችበት ሃሳብ ፣ ከማቅድበት አእምሮ ፣ ከምፈጽምበት ጊዜ ፣ አይሎ እየገነፈለ ፣ ቅጥ አሳጥቶኛል ይኸው ። የኔ ብጤዎቹ ምግባር ፣ በመንግሥተ ሰማይና ፣ በምድር መሃል ስንገላተት ፣ ስንት ውጥንቅጥ አለበት ፣ ሕይወት የሚፈተንበት ። የሤራ ፈላስፎች ብቻ ነን ፣ አንዳችንን አትመኝን ። ቆብሽን ጭንሽ ገዳም ግቢ ። . . . አባትሽ የት ነው ያለ ?

**ወፌ–ይላ**
እቤት ነው ።

**ኀምሌት**
ደጃፍህን ቆልፍ በዬው ፤ እንቆቅልሽ ለጨዋ ልጅ ፣ ደጁን ዘግቶ እቤቱ ያምራል ፤ የውጩውስ እንቆቅልሽ ፣ የኋላ ቀን ደግ አደለም ።
ደኅና ዋይ ።

**ወፌ–ይላ**
. . . ምን ኢባቴን ላርግለት እመ ብርሃን !





. . . ቆብሽን ጭንሽ ገዳም ግቢ !

**ኀምሌት**
ባል ልታገቢ እንደሆነ ፣ የሚቀጥለውን ቸነፈር ፣ በረከት እሰጥሻለሁ ። ጥብቅ ብትሆኚ እንደ ሰማይ ፣ ወይ እንደበረዶ ንጹህ ፣ ካሉ ቧልታ አታመልጪም ፤ ቆብሽን ጭንሽ ገዳም ግቢ ። ሂጂ በዪ ደኅና ዋዪ ። ግድ ማግባት ከኖረብሽ ፣ ጅል ብጤ ፈልገሽ አግቢ ፤ ግምት ያለው የሆነ እንደሁ ፣ ከቀን በኋላ ጅል ጋኔል ፣ እንደምታደርጊው ያውቃል ። ፈጠን ብለሽ ገዳም ግቢ ። ደኅና ዋዪ ።

**ወፌ–ይላ**
ባክህ ኢየሱስ ንገረው ።

**ኀምሌት**
ቀለም የመቀባባት ወግ ፣ መማርሽንም ሰምቼአለሁ ፤ እግዚአብሔር የሰጠሽን መልክ ፣ መስተዋት ፊት ፣ ወረቀት ላይ ፣ አለዋውጠሽ እየቀባሽ ፣ ትቀያየሪአለሽ አሉ ። በዳንስማ የዳንኪራ ፣ ጥበብ ፣ ተጠበሻል አሉ ። ስትፈነጪ ፣ ስትጋልቢ ፣ ሰበር ሰካ ስትዪ ፣ ያዝ ለቀቅ ስትዪ ፣ እጥፍ ዘርጋ እንዳለንጋ ! . . . በርቺ ፣ በርቺ ፣ በርቺ ፤ . . . እኔን ግን ያሳከረኛል ፤ . . . ጋብቻ ከምትሉትም ፣ እኔና አንቺ ብቻ እንጂም ፤ እስካሁንም የተጋቡት ፣ በራሳቸው ይወቁበት ። . . . ቶሎ ብለሽ ገዳም ግቢ ።
—ይወጣል—

ወፈ-ይላ
አዩ ኀምሌት ፣ አዩ ጀግና ፣
ቀረህ እንዳይሆን ሆንክና !
የመኳንንት ፣ የወታደር ፣ የሊቅ እንደበትና ጦር
የምድረ-ዴን ዘውድ እጩ ፣ . . . ስንቱን ታሳያለች መኖር !
የኅበዛዝ አርአያ ፣ የመልክ ቀናዎች ድንበር
ያድናቂዎች ተደናቂ ፣ ኀምሌት እንዲህ ሆነህ ትቀር !
እኔስ ? ቃልክን እንደመንፈስ ፣ በነፍሴ ሕይወት ናኝቼ
ከሴት ዘር በታች ረክሼ ፣ በስመመንህ ምጥ ሞቼ . . . .
ባከንክ ኀምሌት እንደቅገሮት ?
ስልቱ እንዳልሠመረ ልቅሶ ፣ ሆድ ውስጥ እንደጮሁት ጩኸት ?
እንደወረት ? እንደዘበት ?
ባከንክ ኀምሌት እንደተረት ?

—ንጉሡና ጶሎኒዎስ ይገባሉ—

ንጉሥ
ፍቅር ይመስላል ነው እምትል ? . . . ኸረ እኔ እንጃ ፣ . . . አዩ እንጃ . . . .
ስም የሌለው አጉል ፍርጃ ።
ንግግሩ አቅድም ቢያጣ
ለኔ ዕብደትም አልመሰለኝ ፣ ወይ ፍቅር የሚሉት ጣጣ ፤
መንፈሱ ግን ከነአካቴው ፣ የሃሳብ ጸጥታ ተነፍጓል
ሁናቴው ሁሉ ቅጥ አጥቷል
ያም ሆነ ማስጋቱ አልቀረም ፣ ይህ ሽሽግ ድፍን እንቁላል ፤ . . . .
ከእንግሊዝ ጋር ባደረግነው ፣ የስምምነት መሠረት
ንጉሣቸው ያልከፈለን ፣ ያመት ዳረጐት አለበት ፣
በፍጥነት ተደርጐ እንግዲያ
ኀምሌት ይላክ በዚያ ሳቢያ ። . . . .
የመርከብ ላይ ባሕር ጉዞው ፣ ሥፍራው ያዲስ አገር አየር
ያሸረው ይሆናል እልቡ ፣ የቀረቀረውን ነገር ፤
ወይ የራስ ምታቱም በዚያው ፣ መንኮራኩሩ ዝግ ይላል
ወይ አንድያውን ይፈርጣል ። . . . .
አንተንስ ምን ይመስልሃል ?

ጶሎኒዎስ
ቴህ ወዲያ ምን ዘዴ ይገኛል ! . . .
ይሁንና አሁንም ሳቢያው
የፍቅሩ ጉዳይ ነው ብዬ ፣ እንደቀነቀነኝ ነው ያው ፤ . . . .
በይ እንግዲህ ወፈ-ይላ ፣ ሰምተነዋል አታስቢ
ቢቃሽ ፣ ወደ ቤትሽ ግቢ ፣ . . . .



እና ከትርኢቱ በኋላ ፣ ግርማዊነትዎም ፈቅደው
ንግሥት እናቱ ለብቻው ፣ ኀምሌትን ቤት አስጠርተው
በእናት አንደበት አባብለው ፣ እንዲያዋያቸው ሰበቡን
እኔም ቅርብ ተሸሽጌ ፣ ባዳምጠው ንግግሩን
አገኝ ይሆናል ምሥጢሩን ፤
እምቢ ካለም እንደበቱ ፣ ከዚያ ወዲያ እርስዎ እንዳሉት
ወዲያ ወደ እንግሊዝ አገር ፣ መሻሉ አይቀርም ቢልኩት ።

ንጉሥ
ጥሩ አስተሳሰብ ነው በእውነት ፤
የታላላቆች ላይ ዕብደት ፣ ጠርቶ መታወቅ አለበት ።
ፈርጦ ፣ ከተሸሸገበት ።

—ይወጣሉ—

# ት ፡ ፪

—ኀምሌት ፣ መሪው ተዋናይና ሌላ ባልደረባ ተዋናይ ይገባሉ—

ኀምሌት
ቃላቱን እኔ እንዳነበብኩላችሁ ፣ ከምላሳችሁ ላይ እያጠናቀራችሁ እንድትናገሩት ፣ በምታምኑባቸው አማልክት ሁሉ እማልዳችሁአለሁ ። ግን ብዙዎቻችሁ እንደምታደርጉት ፣ ቃላቱን እምትጐርሱት ከሆነ ፣ ለተዋንያን ቀርቶ ለመንደር ዕድር ለፋፊ ብሰጠውም ያው ነው ፤ እጆቻችሁንም እንደአክናፍ እያራገባችሁ ደርሶ ዓየሩን አትፈሱት ፤ ግርማ ጭምር በዝግታ ይበጃል ። ማለት ፣ በመጨረሻው የስሜት ሲቃ አውሎ ነፋስ መጥቃችሁ ፣ ወይም በማዕበሉ አዘቅት ውስጥ ሰጥማችሁም ሳለ ፣ ለአስካኩ ሚዛንና ስልት የሚሰጥ ዝግታና ግርማ የግድ ልታስገኙለት ይሻል ፤ . . . የምሬን ነው የምላችሁ ፣ አንዳንድ በየመጐናጸፊያው ዓይነት የተጠቀለለ ደንደሳም ፣ የቃላትን ደመ ሕይወት ጐርሶ ይዞ እየተረተረ ፣ በጣጥቆ ዳባ ሲያለብሳትና ፣ የምድር - አቀፎቹን አልባሌዎች ጆሮ ሲሰነጥረው ሳዳምጥ ፣ ምንም እንኳ እነሱም ትርጉም ከሌለው ድፍን መወራጨትና መንጫጫት ሌላ የሚጨበጥ ትርፍ ባያተርፉም ፣ እኔን ነፍሴን ነው እሚለክፈኝ ። እንደኔ ቢሆን ፣ የዚህ ብጤውን ፣ የጋጋኖን አቴቴ ዛር አምላክ እንኳ አጋኖ ቢጫወታት ፣ አጋድሜ ነበር እማስገርፈው ። ከሄሮድስም አልፎ የሄሮድስ ሄሮድስ ልምሰል እኮ ነው እሚል ። . . . በፈጠራችሁ ፣ አስወግዱት ።

ተዋናይ
በተቻለን አንቦዝንም ልዑል ሆይ ።

ኀምሌት
አለልክም ደሞ አትጨመቱ ፤ የገዛ አስተያየታችሁ ይምከራችሁ ። እን ቅስቃሴአችሁን ከቃሉ ፣ ቃሉን ከእንቅስቃሴአችሁ ስታዋህዱት ፣ የፋ ታን ምዕራፎችም ከለመዘንጋት ጋር ነው ፤ ግብዝነትን ሳይሆን የሕይወትን የግብረ ገብነት ሥርዓትም ከቶ አለመጋፋት ነው ፤ ማለት ፣ ከተውኔት ኪነ ጥበብ ቀደምት ዓላማ አንዱ የተፈጥሮ መስተዋትነት ሲሆን ፣ ከበቂ በላይ ማጋነኑ ዝብዝብ እንዳይሆን መቆጣጠርና መመጠን ነው ፤ ተፈጥሮ የገዛ መልኳን እንድታስተውል ፣ አስተውላም በራሷ እንድታሾፍ ፣ በየጊ ዜው ዕድሜዋና በእርቃን ገላዋ ፣ በሁናቴዋና በሥልጣኗ ማሾፍ እንድት ችል ማለት ነው ። ታድያን የዚህ አሰካክ ከመጠኑ ባነሰ ወይም በተረፈ ቁጥር ፣ አላዋቂውን እንኳ ቢያስቅ ተመራማሪውን ቅር ያሰኛል ፤ እናንተ ከመንፈሳችሁ የምታዋህዱት የትርጓሜ መስተዋት ከሌሎች ትርጉም ይከብዳልና ፣ ፍሬ ሃሳቡን በጥንቃቄ ተገንዘቡት ።

አንዳንድ ፣ በብዙዎች አፍ የሚደነቁ ተዋንያንን ሞያ ፣ አይቻለሁም ሰም ቻለሁም ፤ የክርስቲያን ወግ አይሉት ወይ ክርስቲያን መሰል ባሕርይ ፣ የእስላም አይሉት የይሁዲ ፣ ጥንተ ዛር ውላጅ አይሉት ወይ የዘመናዊ ዛር ውላጅነት ፣ ሲያስገመግሙ ሲያጓሩ ሳያቸው ፣ ፈጣሪ ሳይሆን አንዳ ንድ ጊዜ ወለድ ሃሳዊ መሲሆች አጉል አፈጣጠር ፈጥረዋቸው የሰውን ልጅ ባሕርይ እንዳይመሰሉ አርገው ሲተረጉሙት ፣ ያሳዝኑኛል ።

መሪ-ተዋናይ
ይኸን ይኸን መቸም እኛ በመጠኑ አሻሽለናል ብለን ነው ተስፋችን ፣ ልዑል ።

ኀምሌት
እረ በጠቅላላው አሻሽሉት ። ያስቂኝ ድንክዮቹን ባሕርይ ተመስ ለው የሚጨወቱትን ደሞ ፣ ከተጻፋላቸው ቃላት ሌላ አታክሉበት በሉ አቸው ። ከተመልካቹ መሃከል አንዳንድ ከንቱነቱን ሲኮረኩሩት እሚጌ ፈቀፈቀውን ለማስገልፈጥ ሲሉ እነሱው ራሳቸው ተሽቀዳድመው እኻ ይላሉ ፤ የተውኔቱ ፍሬ ሃሳብ ይኸኔ ባከነ ማለት ነው ። ይኸ ወንጀል ነው ፤ ለጭብጨባ ቅልውጥ የተደረገ ርካሽ መጫወቻነትን ብቻ ነው እሚመ ሰክር ። ሂዱ ተዘጋጁ ።

—ተዋንያኑ ይወጣሉ ። ጶሎኔዎስ ፣ ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ይገባሉ—

እህ ወዳጆቼ ፣ ጌቶቹ ይመጣሉ ?



ጶሎኔዎስ
ያውም ንግሥቲቱም አብረው ፤ እንዲያውም ተነስተዋል ፣

ኀምሌት
እንግዲያውማ ተዋንያኑን ቶሎ በሉ በልልኝ ።

—ጶሎኔዎስ ይወጣል—

እናንተም እርዱ እንጂ ጉበዝ ።

ገድለ ስምዖን
ደስ እያለን እንጂ ልዑል ።

—ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ይወጣሉ ። ሆራትዮስ ይገባል—

ኀምሌት
ሆራትዮስ ፣ እንኳንም መጣህ ፤ መቸም ጨዋ ሰው ነህና . . . .

ሆራትዮስ
ኧረ ጌታዬ . . . ምኔ . . . .

ኀምሌት
እምቀባባህ መስሎህ ነው ? ጠባይህ ያልቀባህን ስም
እኔ ብቀባህ አይጠቅምም ፤
ካልታመነ ደሞ ደህን ፣ ማንም አይለማመጥም ።
ጅላ ጅል ምላስ ብቻ ናት
ማሞካሸት የማይደክማት ፤
ከጆርባ አጠፍ ፣ ካንገት ደፋ ፣ ቀን አዝላ ማታ እምታወርድ
አሽቃባጭ ምላስ ብቻ ናት ፣ ንፉግን ልመና እምትሰድ ።
ይልቅስ ዋናውን ጉዳይ ፣ እንዳንዘል ዘንግተነው ፣
ይኸ የሚታየው ትርኢት ፣ ምሥጢር ብጤ ያዘለ ነው
ለዚያ ለገጠመኝ ጣጣ ፣ እኔና አንተ ለምናውቀው ፤
እና ንጉሡና እናቴ ፣ ተውኔቱን ሲያዩ ፣ ገጻቸው
የተጻፈበት ሁናቴ ፣ ምን እንዳሳደረባቸው
ቀረብ ብለህ አጥናቸው ፤
መጡ መሰለኝ እንዲያውም ፣ ነቅተህ አጥናልኝ ልብ አድርግ
በል እሚመች ቦታ ፈልግ ።

—ንጉሡ ፣ ንግሥቲቱ ፣ ጶሎኔዎስ ፣ ወፌ-ይላ ፣ ሮዘንቅሮስ ፣ ገድለ ስምዖን ፣ ባለሟሎችና አጃቢዎች ይገባሉ—

ንጉሥ
ኀምሌት ፣ እንዴት ከረምክ ልጄ ?

ኀምሌት
ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ድንቅ ። እንዲህ አርጉም መከረም የለ ፤ በድፎ ዳቦ ምጣድ
ላይ ፡ የተስፋ ዓየር እየበላሁ ፡ እንዲህ አርጉስ መከረም አለ ?

ንጉሥ
ምንድነው እምትለው ልጄ ? አማርኛህ አልገባኝም ። . . . .
ይኸን መቾም እኔም ሆነ ፡ ወይም ደሞ እናትህም
ከቶ አላስተማርንህም ።

ኀምሌት
እኔም ለኔ አልገባኝም ።
ድሮ ፡ ዩኒቨርሲቲ ሳሉ
ግርማዊነትዎ ቴአትር ፡ ተጫውቼ ነበር አሉ ?

ንጉሥ
እንዴታ ! ያውም ያማረ !
ድንቅ ተጫዋች ነው ብለው ፡ ያሞጋግሱኝ ነበረ ።

ኀምሌት
ማንን ተመስለው ነበር ፡ የተጫወቱት ? ግር አለኝ ፤

ንጉሥ
ዩልዮስ ቄሣርን ሆኜ ፡ ብሩቶስ ወግቶ ገደለኝ ።

ኀምሌት
እንደኔ አስተያየት ቢሆን ፡ በብሩቶስ ነበር ፍርዱ
እስቲ እንግዲህ ያንን ታላቅ ፡ ገራገር ጥጃ ማረዱ !
ተዋንያኑ ይቅረቡ ?

ንጉሥ
ይቅረቡ እንጂ እንግዲያማ ፡ ላይቀርቡ ነበረ ድሮስ ?

ኀምሌት
አቅርባቸው ሮዘንቅሮስ ።

ንግሥት
ኀምሌት ፡ ና እስቲ እኔ ጋ ቁጭ በል ፡ ይኸው ምቹ ወምበር አለች ።

ኀምሌት
ደረቋ ትሻለኛለች ። . . . .
እመቤቴ ብትፈቅጂልኝ ፡ እስቲ ጉንሽ ሻጥ ልበል ፤

ወፌ-ይላ
እ ? . . . እ ?



ኀምሌት
አጠገብሽ ልቀመጥ ወይ ?

ወፌ-ይላ
አ — አዎን . . . አዎን ፤

ኀምሌት
ምን ያልኩሽ መስሎሽ ነበረ ?

ወፌ-ይላ
የለም ምንም አልመሰለኝ ፤ . . . እውነት ፡ ምንም አልመሰለኝ ፤

ኀምሌት
ሽምጥጥ . . . ነው ተደግፌሽ ፡ እንቅልፍ አሁን በወሰደኝ ።

ወፌ-ይላ
እንቅልፍ አልከኝ ?

ኀምሌት
ምንም አላልኩ . . . እየሽ ተራዬን ሸመጠጥኩ ። . . . .

ወፌ-ይላ
ደስ ደስ ያለህ ትመስላለህ ።

ኀምሌት
ማ እኔ ?

ወፌ-ይላ
አዎን ።

ኀምሌት
እኮ እኔ ?

ወፌ-ይላ
አዎን ።

ኀምሌት
ሃ ሃ ! በይ ጥበብሽን ተጠበቢ ፤ መደሰት ፡ መፈንጨት እንጂ ፡ ሌላ ምን
መውጫ አለኝ ብለሽ ? እናቴን እንኳ አታዪአትም ፡ አባባ በተቀበረ ፡
ይኸው በሁለት ሰዓት ውስጥ ፡ ሳቅ ፡ ጨዋታ ፡ ዓለም ሆነ ።

ወፌ-ይላ
ሁለት ሰዓት እኮ አደለም ፤ ኧረ ሁለት ወር ነው ልዑል ።

ኀምሌት
ኧረ ? ለካ ሁለት ወር ነው ! . . . ምን በወጣኝ ይህ ጥቁር ልብስ ፡ ኧረ ሰይጣን ጥቁር ይልበስ ፡ እንደ ጨዋ ላጊጥ እኔስ ። እግዚኦ ! እግዚኦ ! ድፍን ሁለት ወር ሙሉ ፡ እንዴት አይረሳም በሉ ? እንግዲህ በዚህ አያ ያገ ፡ አንዳንድ ታላቅ ሰው ሲሞት ፡ እስከ መንፈቅ ድረስ ያህል ፡ ትገ ታው ከቶ ላይሞት ነው ፤ ሐልማችን ላይ ደብር ሊተክል ! ደብሩን ካልተ ከለማ ፡ እንደጠቋር የዛር ፈረስ ፡ ሰው ሲሠለጥን ነው እሚፈርስ ! . . .

—ለትርኢቱ መክፈቻ ‘የማይም’ ወይም የዳንስ እንቅስቃሴ ድራማ መቅድም ለማቅ ረብ ሁለት ተዋንያን ይገባሉ ። በፍቅር በተሣሡሩ ንጉሥና ንግሥት ይመሰላሉ ። ንግሥ ቲቱ በተራብ ስሜት ትጠመጠምበታለች ፤ ያቅፋታል ። ሲያንቀላፉ ትታው ፊንጠር ብላ ትወጣለች ። ሌላ ተዋናይ አድፍጦ ፡ አሾልቆ ይገባል ፤ ዘውዱን ከንጉሡ ጭንቅላት አወ ልቆ እቅፍቅፍ ያረገዋል ፤ ወዲያው በንጉሡ ጆሮ የመርዝ ጠብታዎች አንቆርቁሮ ውልቅ ይላል ። ንጉሡ በርግጎ ተንጨፍርሮ ይሞታል ። ንግሥቲቱ ትገባለች ፤ ንጉሡ ሞቶ ታገኘ ዋለች ፤ መደረቢያዋን ቀድዳ ፡ ደረቷን ገልጣ ታዝናለች ፤ መርዝ ያንቆረቆረው ተዋናይ ሁለት ቀትረ-ደናቁርት ባልደረቦች ይዞ ይገባና ያስተዛዝኑአታል ። ሬሣውን ያወጡታል ። መራገፉ ተዋናይ ለንግሥቲቱ ገጸ በረከት ይዞ ያግባባታል ። ለጊዜው በተግሣጽ ያልተቀበ ለችው ትመስላለች ፤ ታንገራገረች በኋላ ልቧ ወዲያው ይከፈልላታል ። ተግባብተው በኅብረት ይወጣሉ—

ወፌ-ይላ

ምን ማለት ነው እንግዲህ ይኸ ልውል ?

ኀምሌት

ይኸ መቅድሙ ነው ፤ ሲፈጸም ትጠይቂኛለሽ ።
—ሐተታ አንባቢው ይገባል—

ሐተታ አንባቢ

—ያነባል—

‘ ይህቺን አጭር ተውኔታችንን
ፈቃድዎ ሆኖ እንዲያዳምጡልን
እዙፋንዎ ሥር በአክብሮት ወድቀን
ግርማዊነትዎን እንለምናለን ።’

—ይወጣል—

ወፌ-ይላ
ምነዋ እንዲህ አሳጠራት ?

ኀምሌት
እንደሴት ፍቅር ?

—ተዋናይ ንጉሥና ተዋናይት ንግሥት ይገባሉ—




ተዋናይ ንጉሥ
ታሪክ አልፎ ሌላ ታሪክ ፡ ዘመን አልፎ ሌላ ዘመን
ሲመጣ ሲሄድ ፡ ሲተካ ፡ በጊዜ ጉዞ ሲመጠን
በእግዚአብሔር ጸጋ ተሳስረን
አብረን ስቀን ፡ አብረን አዝነን
ይኸው ሠላሳ ዓመት ሞላን ፡ ክፉና ደግ አብረን አይተን ።

ተዋናይት ንግሥት
ገና ብዙ እናይ ይሆናል ፡ የእግዜር ጸጋው አይጓደል
እንደ ዕድሜ ምን ሲሳይ አለ ፡ እንደ አብሮ መኖር መታደል ፤
ግን እንጃልኝ የኋላ ቀን ፡ ዓይንህ ዓይኔ ላይ አታርፍም
ብርሃንዋን ሸሽጋኛለች ፡ ሳትሰለቸኝ አልቀረችም ፤
ግን ሴት ልጅ ፈሪ ናትና ፡ እስከዚህ ድረስ ብሰጋም
ልብህ ዓይንህን ገስፃ ፡ እንደምትመክራት አላጣም ፤
በመስጋቴም ፡ እንዳትሰጋ ፡
መጨነቅና መጠበብ ፡ ነውና የመውደድ ዋጋ ፤
ፍቅር ትልቅ የሆነ እንደሁ ፡ ሥጋቱም ፍርሃት ይሆናል
ፍርሃቱም እያደር ሲያድግ ፡ ፍቅሩም ተራራ ያህላል ።

ተዋናይ ንጉሥ
በቃ እንደሱ አትበይ ፡ አይሆንም ፡
ጉልበቴ እየተዳከመ ፡ ቀኔም መቅረቡን አታዩም ?
አንቺ ልጅ ነሽ ፡ ዕድሜ አለሽ
ገና ብዙ ትኖሪያለሽ ፤
ስለዚህ መላ ፍቅርሽን ፡ ለኔ ባትሰዊ ይሻላል
ለኋላ ያስቸግርሻል
አይዞሽ ፡ እንደኔ እሚወድሽ ፡ የሚያከብርሽ ይገጥምሻል ።

ተዋናይት ንግሥት
ተው እንደዚህ አትበድለኝ ፡
በጡቶቼ የሤራ ግት ፡ ያጠመቅኩ አታስመስለኝ ፤
ዳግመኛ ባል አያሰየኝ ፤ ፍቅር የመጀመሪያ ነው ፡
ሁለተኛው እርግማን ነው ።
የመጀመሪያውን ገፍቶ ፡ ማቀድ ለሁለተኛ ባል
በደስታችን ማሾፍ ነው ፡ በፍቅር አምላክ ግፍ መዋል ።

ተዋናይ ንጉሥ
ቆይ አንድ ተረት ልንገርሽ ፡ ወይም ሳታውቂው አይቀርም
‘ ኧረ ተይ ፡ ኧረ ተይ ፡ ኧረ ተይ አይሆንም
ተኝቶ ሰው መግደል ፡ አያስመሰግንም ። . . . ’



ተኛ ፤ ተኛ ፤
እግዚአብሔር ይከልክልልን ፣ በመሃላችን ምቀኛ

ተዋናይት ንግሥት
ተኛ ፤ ተኛ፤
እግዚአብሔር ይከልክልልን ፣ በመሃላችን ምቀኛ

—ትወጣለች—

ጎምሌት
ታድያስ ምን ይመስልሻል እናት ዓለም ?

ንግሥት
ሴቲቱ ክርክር አላበዛችም ?

ጎምሌት
በቃልዋ ብትተማመን ይሆናላ ።

ንጉሥ
ጽሑፉን ተከትለሽዋል ? ዘለፋ ያዘለ አይመስልህም ?

ጎምሌት
አይ አይመስለኝም ። ቢናገሩም የቀልድ ነው ፣ ቢመርዙም የቀልድ ፣
ቢሞቱም የቀልድ ነው ፤ . . . ዘለፋ የሚሉም የለ ።



ንጉሥ
አርዕስቱ ምን ይባላል ?

ጎምሌት
ያይጥ ወጥመድ ፤ ያይጥ ወጥመድ ይሉታል ። ቬኒሲያ በሆነ ታሪክ ላይ የተንተራሰ ትርኢት ነው አሉ ፤ ጎንዛጎ ስለሚባል መስፍንና ባብቲስታ ስለምትባል ሚስቱ ነው ይባላል ፤ መጨረሻውን ያዩት የለ ፤ . . . ትን ግርተኛ ትርኢት ናት ፣ . . . እኛ ምን ጨነቀን ብለው ነው ጃንሆይ ፣ ንጹህ መንፈሳችንን አያውከው ፣ . . . ደንታ የለን ፣ እኒህ መንቻኮች ቢያቃስቱ ፤

—ሉቅያኖስ ይገባል—

. . . መጣ ደሞ አንዱ ፤ ሉቅያኖስ የሚሉት የመስፍኑ የሥጋ ዘመድ ነው ። . . . መጣ ፣ መጣ ፣ ይኸ ቀንድ አውጣ ።
መተቱን እያተተ መጣ እየተጐተተ ፣ . . . .
መጣ ይኸ ቀንድ አውጣ ።

ሉቅያኖስ
ቀኑ ፣ ሥፍራው ፣ መድኃኒቱ ፣ ሠምሮ ፣ ተስማምቶ ሲጣጣም
የወደቀ አይነሳም
የተኛ ከእንቅልፍ አይነቃም ፤
ውጋ ፣ ውጋ ፣ መርዝ ፣ ንከስ
ዕጣ ክፍሉና ኮከቡ ፣ አድሚልና እንዳትረክስ
ያሸተተህ እንዲማቅቅ ፤ የቀመስህ ገላው ሊፈርስ
ውጋ ፣ ውጋ ፣ ንከስ ፤
በቀትር ንዳድ ተምስህ ፣ በደረቅ ሌት ተቀምመህ
ያሸተተህ ሲጥመለመል ፣ እንኳን በሥጋ ደም ዘልቀህ
ውጋ ፣ ቅጠፍ
የተነፈስህ ይዘንጠፍ ፤
ንከስ
የቀመስህ ገላው ይፍረስ ።
—መድኃኒቱን በጆሮው ያንቆረቁራል—

ወፌ-ይላ
ግ — ግርማዊ ተነሱ !

ንጉሥ
መብራት ብርሃን ብጤ ምነው !

ሁሉም
ብርሃን ! መብራት ! ብርሃን ! መብራት !
—ከጎምሌትና ከሆራትዮስ በቀር ሁሉም ተደናብረው ይወጣሉ—



ንከስ ፤
ዕጣ ክፍሉና ኮከቡ አድሚልና፣ እንዳትረክስ ።

ኀምሌት
እኮ ምን ሊባል ነው ? . . . ሆራትዮስ ጉድ ልንገርህ ፣ ለሰው ስሜት ይብ ላኝለት ፤ . . . ስንቱን ችሎ ፣ ስንቱን አዝሎ ፣ በስንቱ እልህ ተቀቅሎ ፣ ስንቱን ዝብዝብ ሲያሰላ ፣ በበራድ ነገር ሲቦዝን ፣ በትኩስ ነገር ሲፈላ ፣ በራስ ምታት ተነትርኮ ፣ በሆድ ቁርጠት ተቦጭቆ ፣ ነገር አኮ ፤ ቁርጠት አኮ ፡ . . . አሁን ምን ነካኝ ሊባል ነው ?

—ሮዘንቅሮስና ገደለ ስምዖን በጥድፊያ ይገባሉ—

. . . መብራት ብርሃን ! . . . እኔስ ሙዚቃ ይሻለኛል ። ሙዚቃ ! ሙዚቃ ! ጌቶች በቀልድ ካመረሩ ! የጤና አልሆነሙ ነገሩ ፤ ሙዚቃ ! መለከት ! ጡሩ ምባ !

ገድለ ስምዖን
ልዑል ብትፈቅድልንና ፣ አንዷት ቃል ብናናግርህ . . .

ኀምሌት
አናግሩኝ ፣ አናግሩኝ !

ገድለ ስምዖን
ኧረ ልዑል ፣ . . . ንጉሡ መንፈሳቸው ክፉኛ ተቆጥቶ . . . .



ኀምሌት
መጠጥ ነው ?

ገድለ ስምዖን
ኧረ የለም ፣ በብስጭት ምክንያት . . . .

ኀምሌት
ታድያ እኔ ምን ላርግላችሁ ? ኀምሌት ሐኪም ነው አሏችሁ ?

ገድለ ስምዖን
አንዴ እኮ ብታናግረኝ . . . .

ኀምሌት
እኮ ተናገር ፣ ለማድመጥ ገርታችሁኝ የለ ።

ገድለ ስምዖን
ንግሥት እናትህ ልዑል ፣ በታላቅ ጸጸት ተጨንቀው ፣ አንተ ጋ ስለላኩኝ ነው የመጣሁት ።

ኀምሌት
እንኳን ደኅና መጣህ ።

ገድለ ስምዖን
እንዲህ እኮ አደለም ነገሩ ልዑል ። ፍቃድህ ሆኖ ለተላክሁበት ጉዳይ ቀጥተኛ መልስ ትሰጠኝ እንደሆነ ፣ በጄ ፤ አለበለዚያ ግን ነገሩ በዚሁ ተቆረጠ ማለት ነውና ጌታዬ ብታሰናብተኝ ይሻላል ።

ኀምሌት
አልችልም ።

ገድለ ስምዖን
ምኑን ልዑል ?

ኀምሌት
ቀጥተኛ መልስ ልሰጥህ አልችልም ። ከተረሳሳን የቆየነውን ቀጥተኛ ጤንነት አታስታውሰኝ ። ግን የምሰጥህን ማናቸውንም መልስ ተቀብለህ ማሳለፍ ብቻ ነው ። ቀጥተኛ ሆነ ስንኩል ፣ ዱልድም ሆነ ሹል ፣ ድፍን ሆነ ቀዳዳ ፣ ተግባርህ ማመላለስ ብቻ ነው ። እና ንግሥት እናቴ . . . .

ሮዘንቅሮስ
እንግዲያውስ ንግሥት እናትህ ፣ ልዑል ፣ ባሕርይህ እጅግ አሳዝኖኛል ብለውሀል ።

ጎምሌት
ጉድ አትልም ! የጉድ ዕድል !
እንዲህ በድንገት ዱብ ሲል
ተወልዶ እኔን የሚያክል
እናቱን አግፍር ጉብል ! . . .
ታድያን በዚህ የተነሳ ምን ይሁን አለች በል ?

ሮዘንቅሮስ
አሁኑኑ እልፍኝ ድረስ መጥተህ ሳታነጋግረኝ መኝታ ቤትህ እንዳትሄድ ብለውሃል ።

ጎምሌት
እሰየው ! እሺ ንግሥት—ዓለም—እናት—ዓለም እመጣለሁ ብኋል በል ። ሌላስ ፤ ጉዳይ አለን ?

ሮዘንቅሮስ
አይ የለንም ፤ . . . ብቻ ልዑል ፥ ከቀድሞ ወዳጅነታችን ለምን እንዲህ እንዳራቅኸን . . . .

ጎምሌት
እንዴት ተደርጐ ! እኔ ? እናንተን ?
ምን ቆርጦኝ ? በምን አንጀቴ ! ? . . . . አምጣ እጅህን ! ቀኙን የማይከዳውን

ሮዘንቅሮስ
ታድያን ምነው እንደድሮአችን ፥ ችግርህን ችግራችን ፥ ሕመምህን ሕመማችን እንዳናደርገው ምሥጢሩን ነፈግኸን ? ደበቅኸን !

ጎምሌት
‘ወዳጅዎ ጆሮ ስንቁ ፤ አለልቡ ፤
ዳኛዎ ትእዛዙ ብቁ ፤ አለማተቡ ፤
መቸስ ከገቡ ጨፍነው ይግቡ ፥ ሳያማትቡ’ ማለትህ ነው ?

ሮዘንቅሮስ
ልዑል ለካ አንተም እንደኛው ቡቡ ነህና ? እስከዚህ ምን ያጠራጥርሃል አልጋ ወራሽነትክን እንደሁ ንጉሡ ራሳቸው አሳምረው ባደባባይ ባዋጅ ነግረውልሃል ።

ጎምሌት
ነግረዋል እንዴ ? ነግረዋላ ! . . . እስቲ እጄን ምታ ! ቀኙን የማይከዳውን ! . . .



ወተትሽ ይደር ፥ ቅቤ እንዲወጣው — ቢሳት አሉ ደላላ
እስኪያድር ድረስ ፥ ምጥማጥ ሊያሳው – አለች አሉ [redacted] ።
ተረቱ ይቀጥላል ፤ ግን ቷህ ወዲያ ይሸታል ! . . .

—ከተጥንያን አንዱ እየተጫወተ ዋሽንት ይገባል—

ታድያን ፍቅራችን ፥ አጉል ሲበዛ ፤ እንዳይጠነዛ ፤ አልበቃም ዋዛ ?

ገድለ ስምዖን
ልዑል ጌታዬ ፥ የጸኑ ወዳጅነታችን ጥናትና ጥራት ብቻ ነው ፥ ከተግባራችን ብዛት ጋር ሲጋጭ አግባብ ያጣ ያስመሰለብን እንጂ . . . .

ጎምሌት
በለው ! ይኸ ይኸ አልገብቶኝም ፥ አያ ተግባር—ብዛት ወዳጅነት—ጥናት ፤ . . . .

—ዋሽንቱን ከተዋናዩ ተቀብሎ—

ዋሽንት መንፋት ትችል የለ ?

ገድለ ስምዖን
እኔ የት አባቴ አውቅበታለሁ ብለህ ልዑል ።

ጎምሌት
ተው ባክህ ጃል እንካ ።

ገድለ ስምዖን
ልዑል ይሙት አላውቅበትም ።

ጎምሌት
ምነው ስለምንህ !

ገድለ ስምዖን
እንዴ ፥ ምነው ጐበዝ ! ነክቼውም አላውቅ ስልህ !

ጎምሌት
ቀላል ነው ፤ ከውሸት እንኳ የቀለለ ነው ። ይኸውልህ ፤ ቀዳዳ ቀዳዳውን በቀኝ እጅህ ጣት ፥ በማይከዳው ፥ አፍነው ፤ ወዲያው አፍክን አሹለህ ንፋ ፤ ከዚያ በኋላ ሰምተህ የማታውቀውን የዋሽንት ጡሩምባ ታሰማለህ ። ያው በል ፥ ተቀዳጅበት ።

ገድለ ስምዖን
የማላውቅበትን እንዴት አርጌ ! . . . ኧረ ፍረዱኝ ሰዎች !

ጎምሌት
እኔን ግን አንተው ፍረደኝ ! በል እንደገመትከኝ ፍረደኝ ። በኔ ላይ ለመ
ጫወቱ ጊዜ ታውቅበታለህ ። ግምቴን አቅሜን ለክተህ ትተነፍስብኛለህ።
የልቤን ምሥጢር ስልት እያነፈነፍክ ትቃኘኛለህ ። . . . ከዚች ከትንሿ
የዋሽንት መሣሪያ ግን ውብ ዜማ ቢፈልቅም ፤ ከቶውኑ ልትጫወትባት
አልቻልክም ። ታድያስ ፤ ከዚች ከቀርከሃ አንጓ ይልቅ በኔ ላይ ለመጫ
ወት መቻልክን ማን አስተማረህ ? ስታነፈንፍ ትታክታታለህ እንጂ በኔ
ለመጫወት አትችልም ። ከኔ አንዳች ስልት ጠብ አይልልህም ። በል እግ
ዚአብሔር ያጥናህ ወዳጄ ።

—ይወጣል—

## ት፡፫

—ንጉሡ ፤ ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ይገባሉ—

ንጉሥ
ይበቃል ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ፤ ምንም አይጠበቅ ከሱ
ወዲያ ወደ እንግሊዝ አገር ፤ አድርሳችሁት ተመለሱ ፤
ለሀገሪቱም ሆነ ለኛ ፤ ቀና አይመስልም መንፈሱ ።

ገድለ-ስምዖን
ነው ፤ ይኸው ነው የሚሻለው ፤ እኛማ አቃተን ጨርሶ
እንኳንስ ሊጠመድልን ፤ ያጠምደን ጀመር መልሶ ፤ . . . .
የኛ እንኳ ባልከፋ ነበር ፤ ለሀገሪቱም ክብር አልሳሳ ፤
የእርስዎንም ጸጥታ ነሳ ።

ሮዘንቅሮስ
ያንድን ቤተ ሰብ ሃላፊ ፤ ማወክ ፤ ሰላሙ እንዳያምር
ጸጥታውን ብቻ ሳይሆን ፤ ማፍረስ ነው ትዳሩን ጭምር ፤
አልጋን በያዘም ፤ መታበይ ፤ መጣረር ፤ ዘውድን በደፋ ፤
የሱን ሰላም ብቻ ሳይሆን ፤ ሀገሪቱን ጭምር ገፋ ፤
ውሀ ሙላት ፤ ዓውሎ ነፋስ ፤ አሰሱን ሳያግበሰብስ
ስንቁን ሳይይዝ እንደማይነፍስ ፤
ኃይልም ብቻዋን አትወድቅም
አጥሯን ፤ ማገሯን ሳትለቅም ፤
ጫካና ቁጥቋጦው አቅፏት
ጠጠርና ኮረት አዝሏት
ተራራ ጫፍ ላይ እንዳለች ፤ እንደ ጠብ የአለት ጉልላት ፤



የናዳ መሠሪ እንደ ምንጭ ፤ ተፈትልኮ ከሥር ሲፈልቅ
ግሣንግስዋም ተያይዟት ፤ አብሯት ተንኮትኩቶ እንደሚያልቅ
የኃይልም ጓዟ ብዙ ነው ፤ ብቻዋን መሄድ አታውቅም
ያዘላትን ሳታስቀድም ፤
ስለዚህ ገገርም ብቻውን ፤ 'እህህ' አይልም ከቶ
አብሮ ያምጣታል እንጂ ፤ ሠራዊት ጥርሱን አፋጭቶ ።
ስለዚህ ተግባራችንም ፤ የሚያስገኘው ፍሬ ነገር
ሃላፊነቱን ስናቅ ነው ፤ እንዳትታወክ ነው ሀገር ፤

ንጉሥ
ሃላፊነትን መካፈል ፤ ነውና ችግርን ሲያቁ
እንግዲህ እናንተም በርቱ ፤ እንዳይሾልክ ፤ ተጠንቀቁ ።

—ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ይወጣሉ—

እግዜር ይፍታህ ለማይሉት ፤ ሥራይ ፤ የእንቆቅልሽ ቃሉ
'እሾህ ላጣሪው' ነው አሉ ።
በመንግሥተ ሰማይ ስሜን ፤ አየኋት ፤ ተጥላ ፤ ገምታ
የወንድሜን ደም ተቀብታ ፤
ልቤ እንኳ ባይል ፤ እንዳለ ፤ ራሴን አግባብቼ ባምንም
ጸሎት ከቶ ካንደበቴ ፤ አልወጣ አለኝ ፤ ብፈልግም ፤
ሕሊናዬ ቃሌን አንቆት
አይበገር ታብዮዬን ፤ አይበገር ግፌ ውጦት ፤
በሁለት እጁ እንደበላ ፤ ለሁለት ጌታ እንዳደረ
ባንዱ ሳይሠምር ፤ አንዱን ሳይይዝ ፤ ነፍሴ እንደቃተተ ቀረ ፤
በወንድሜ ደም ተዘፍቃ ፤ በግፍ ድርብ ብትቆሸሽም
ለእጇ ማጥሪያ ያህል ዝናብ ፤ መንግሥተ ሰማይ የላትም?
የት አል የይቅርታዋ በር
ያመፅን ግንባር ፊትለፊት ፤ አፋጥጣ መፈተን በቀር?
ምንድነው የጸሎት ጥቅሙስ ፤ ኃጢአታችን ከቀበረን?
ስንጠመዘዝ ካልቀናን ፤ ስንሰበር ካልተጠገንን ?
እኔም መንግሥተ ሰማይን ፤ እማያት ፤ ሲሞት ነው ግፌ
ከሕሊናዬና ከእጄ ፤ ቀድሞ ሲታጠብ ነው እድፌ ፤
ታድያስ ምንድነው ጸሎቱ ፤ ለእንደኔው ብጤው ኃጢአት
በምድር ላይ አጥቦ እሚያነጣ ፡ አስታራቂ የቂም ፍትሃት !
በደሌን ይቅር በል ልበል? . . . በደሌን መች ተላቀኳት !
የዕቡይ መንፈሴን መች ተውኳት ?
ንግሥቲቱንም አልራቅኳት ፤
ዘውዷንም እንደደፋኋት . . . .
ዕቡይነቴን ሳልተዋት

ከየት መጥቶ ይውጣኝ ጸሎት? . . . በእግዜር ወይ በኔ ላሾፍ ነው ?
በደሌን ይቅር በል እንጂ ፣ በደሌን አጽድቅ አልለው ፤
የመንግሥተ ሰማይ ችሎት ፣ ይግባኝ የለው አያካክድ
ገበናችን እንደቆዳ ፣ ተሸልታ በነፍስ ፍርድ
እርቃኗን መፋጠጥ እንጂ ፣ ዘጠኝ ጊዜ ብትዘላብድ ፤ . . . .
መች ይቸግር ነበር ያማ ፣ ብትጠመድ እንደኛ ልምድ ፣
እንደዚች ዓለም ዳኝነት ፣ በአገም ጠቀም ብትቀላምድ ፤
እኮ ምንድነው ብልሃቱ ? የእግዜር ዳኝነቱ ላይፈርስ
ዘጠኝ ሱባኤ ቢገባ ፣ ዘጠኝ መቶ ማቅ ቢለበስ
በዚህ ላይ የኔም ዛር ምሱ ፣ የዕቡይነቴ መንፈስ
ግቡን ካልያዘ ላይለቀኝ ፣ ከግብሩ አንዳች ላይቀነስ
ጸሎት ሱባዔ እማይፈታኝ ፣ እኔው ነኝ የራሴ መተት
በተበተብኩት መሠሪ ፣ እስካንገቴ ጠልቄበት ።
ተወኝ እንዳልልህ አምላክ
አልተውኳት የግፌን ተውሳክ ፤
ነፍሴም ለማምለጥ ብትጥር
ፍቃዴ ከብረት ግትር ፤
እግዚኦ መላእክተ ቅዱሳት
ጉልበቴን ታጠፊ በሷት
መንፈሴን ታጠፊ በሷት
ፍቃዴ የእግዜርን ፍቃድ ፣ እንድትቀበል ምከሯት
ያለዚያማ ተስፋም የላት ፤
እግዚኦ እናንተ ተስፋ ሁኗት . . . .

—ተንበርክኮ ንጉሡ በጸሎት ሲመሰጥ ኀምሌት ይገባል—

ኀምሌት
አሁን ? . . . ታድያስ አሁን
ላቅርባት የጽዋ ስንቋን? . . .
እግዚኦ ! . . . . እሱም ይጸልያል
ከአምላክ ጋር ውይይት ይዟል . . . .
እግዚአብሔር አብን ሲማለድ ፣ የሞቱን ጽዋ ብሰጠው
የመንግሥተ ሰማይን በር ፣ ከፍቼ እንዳስገባሁት ነው ፤
ታድያስ በቀሉስ በቀል ነው ?
ያባቴን ገዳይ ገድዬ ፣ መንግሥተ ጽዮን ባስሰጠው ?
ዕድሌ ይቺን ስንኩል ሰዓት
ምን ሲያረግ ለኔ መረጣት !
አልሰጠው የሞቱን ጽዋ ፣ ሕይወቱን በጄም ቢያስገባት
ለበቀል ውለታ አልከፍልም ፣ እጄን በገዛ እጄ ልብላት ?



እምላኩስ ፊት አልገለውም ፣ ሲጥር ሱባዔ ሊገባስ
ከኃጢአቱ አደል ያፈነው ? መች ንስሐ ገባ አባባስ ?
ዛሬ ትለፈው ግድ የለም ፣ ጽዋው ብታልፈው አይከፋም
ከመንግሥተ ጽዮን በቀር ፣ ማን ያውቃል ያባቴን አቅዋም ?
ከነግፉ ነው እማሰጥመው ፣ አሁን ግን ፀጉሩን አልነካም !
አለው ሰዓት ፣ አያመልጥም ፣ . . . በበደሉ ሲከረፋ
በግፍ ደንፍቶ ሲተፋ
በእግዜር ላይ ጀርባውን ሲያዞር ፣ ሲዶለት ፣ ሲያሤር ፣ ሲገፋ
ሲቦርቅና ሲሴስን ፣ ነፍሱ በኃጢአት ስትለፋ
የዚያን ጊዜ ነው ጽዋውን ፣ በጉረሮው እምደፋ ።
ይሞክራት ጥቂት ጊዜ ፣ ይጋተራት የኑሮን ምርቅ
እጄም ፣ ሰይፌም ይታገቱ ፣ በኃጢአቱ እስኪማቅቅ ።

—ይወጣል—

ንጉሥ
አፌ ብቻ ክንፍ አውጥቶ ፣ ባዶ ቃላት ሲያነበንብ
ልቤ መሬት አቅፎ ቀረ ፣ አብሮት አልወጣ አለ ሽቅብ ፣
ጸሎት ያለ ልብ ፍቃድ ፣ ፍሬ አይኖራት ፣ ከቶ አታብብ ። . . . .

—ይወጣል—

## ት ፡ ፬

—ንግሥቲቱና ጶሎኔዎስ ይታያሉ—

ጶሎኔዎስ
ንግሥት እንግዲህ ይበርቱ ፤ ተልኮበታል ፣ ይመጣል ፤
ባሕርይህ አቅል አጥቷል በሉት ፤ . . . እስካሁንም በርስዎ ብርታት
ጉዳዩ በርዶ ነው እንጂ ፣ ኋላ ጉድ ይፈላል በሉት ፤ . . . .
መጣ መሰለኝ ልሸሸግ . . . ልክፍትህ ምንድነው በሉት ።

—ጶሎኔዎስ ይሸሸጋል ። ኀምሌት ይገባል—

ኀምሌት
ለምንድነው ያስፈለግሺኝ ፣ እናት ዓለም ? ይኸው መጣሁ ።

ንግሥት
እቅጬን ልንገርህ ኀምሌት ፣ አባትክን በድለኸዋል !

ኀምሌት

እቅጩን ልንገርሽ እኔም ፤ አባቴን በድለሽዋል !

ንግሥት

ይኸንኑ እኮ ነው እምልህ ፤ ምንድነው ይኸ አጉል መልስ ?

ኀምሌት

ይኸንኑ እኮ ነው እምልሽ ! ምንድነው ይኸ አጉል ጥያቄ ?

ንግሥት

እንዴት ኀምሌት ? እንዴት ? እንዴት ?

ኀምሌት

የምን እንዴት - እንዴት ነው እሱ !

ንግሥት

እናትህ እኮ ነኝ እኔ ! እናትክን ረሳኸኝ እንዴ ?

ኀምሌት

እንዴት አባቴን አርጌ ? ምን ባረግ ነው እምረሳሽ ? ንግሥቲቱ አደለሽ
እንዴ ? የባልሽ-የወንድም-ሚስት ፤ . . . በዚህ ላይ ደሞ እናቴ ነሽ ፤
ምን ቆርጦኝ ነው እምረሳሽ ?

ንግሥት

. . . አይ ተወው እንግዲያስ ተወው ። እነኝያው የሚያፋጥጡህ ፤
ይምጡልህና ያስወትውቱህ ። . . . .

—ትነሣለች—

ኀምሌት

ነይ ! ጸጥ ብለሽ ተቀመጭ ። ከዚህ ውልፍጥ እንዳትዪ ፤
ጉድሽን በመስተዋት እፊትሽ ፤ አፋጥጬሽ እስክታዪ !

ንግሥት

እኮ ምን ልትሆን ? . . . ልትገድለኝ ! . . . ግደለኝ ፤ ግደለኝ ኧረ !

ጶሎኔዎስ

ኧረ ጐበዝ ኡ ! ኡ ! በሉ ፤ . . . ኡ ! ኡ ! ኡ ! ያገር ያለህ ! ኡ ! ኡ

ኀምሌት

. . . ውሻ ? ልክስክስ አሥረሻል ፤ ውሻ ? ልክስክስ አልወድም !
አልወድም !

—ጶሎኔዎስን መጋረጃ ውስጥ ይወጋዋል—



ንግሥት

. . . ምንድነው እሱ ያረከው !

ኀምሌት

አንቺ ንገሪኝ ምንድነው ? ንጉሡ ነው ?

ንግሥት

ኧረ ምንድነው ያረከው ! የምን ጥድፊያ ! የምን ኃጢአት !

ኀምሌት

መቸም አይብስ ካንቺ ኃጢአት
ባል ገድሎ ወንድሙን ከማግባት !

ንግሥት

ምን !

ኀምሌት

ቃሌ ነው ፤ አዎን የኔ እናት ! . . .
ምን ይኸ የዋህ ልክስክስ ፤ የተጣደፈ የቁም ሙት
ካንተ የተሻለው መስሎኝ ፤ ለካስ አንተን ነው የቀጠፍኩት ።
አንቺስ ሥራው ብዙ መስለሽ ፤ ሌህ ነው የተንቀለቀልሺው
ብዬው በይ እንቺ ምስሽን ፤ ሰበብ ላይ እንደተከልሺው !
እጅሽን አታርገብግቢ ፤ በቁም እንደተኮነነ
ይልቅስ ልብሽ ይርገብገብ ፤ እውነት በድን እንዳልሆነ
በሥራይሽ ተቆራምዶ ፤ በስሜት ሞት ካልመሰነ ።

ንግሥት

ዘጠኝ ወር በተሸከምኩህ፤ ጡት መግቤ ባሳደግሁህ
በወላጅ ፍቅር ባዘልኩህ
ምን በደልኩህ ! ምን በደልኩህ ?

ኀምሌት

በደል አልሺኝ ? በደል ? በደል ?
በደልሽ በደል እንዳይደል ! . . .
ቅንነት በሰው ልጅ ባሕርይ ፤ ተፈጥሮ እንዳልነበረ
መገበዝ እምነትን ገድላ ፤ ሕሊና እንዳልተፈጠረ
ኩብሩክ ፍቅር አክሊል ውስጥ ፤ የውል ቅብዐ ቅዱስ ደፍቶ
የጋብቻን ሥርዓተ ቃል ፤ ከነመቀነቱ ፈትቶ
በደል ከጐተራው ተርፎ ፤ እንደ በልግ ትል ሲፈላ
ምን በደልኩህ ይባላላ !
ሃይማኖትን እንቆቅልሽ ፤ ቧልት ያስደረጋት ያፍ እልፊት
በቁሙ ከሕያው ሰው ውስጥ ፤ ነፍስ የሚመነጥቅ ድርጊት ፤

የመንግሥተ ሰማይም ዓይን ፣ ከቶውኑ እንደታወረ
በድኩም ሥጋና ደም ውስጥ ፣ ግፍ ተሸሽጎ እንደቀረ ፣
ዳኝነት ፣ ፍርድና ምፅዓት ፣ በሕልም እንኳን እንዳልኖረ
ኃጢአት በሕሊና መሶብ ፣ በደም እርም እየተበላ
ምን በደልኩህ ይባላላ !

ንግሥት
ከመወትወት ይኸን ሁሉ
እቅጩን አትናገርም ፣ እኮ ምንድነው በደሉ ?

ጎምሌት
ይኸን ሥዕል ታውቂዋለሽ ? . . . ይኸንንስ ታውቂዋለሽ ? . . .
ይኸኛውን በቁም በልተሽ ፣ ይኸን በቁም ትልሺያለሽ ። . . . .
ንሺ ፣ ይኸን አስተውዪው ፣
በትዝታሽ ስዕል ሳዪው ፣
ቀረብ አድርገሽ አስታውሺው ፤
የሐር ሽልም ሽፋኑን ፣
የገጹን ፣ ግርማ ሞገሱን ፣
የጐፈሬ አወራረዱን ፣ የራስ ወርቅ አሥተሣሠሩን
የመንፈሰ ንቁነቱን ፣
የጸጋ አረጋዊነቱን ፣
ግንባረ መለኮት ዳኛ ፣ እውነት ካይኑ የሚነበብ
ቀና ገዢ ፣ ብቁ ጀግና ፣ የወንድ ወንድ ፣ የተርብ ተርብ ፣
መላእክት የተቀበሉት ፣ በሃሰት ፍርድ ያልተፈታ
የጥበብ ወዳጆች ወዳጅ ፣ ለዓለም የተሰጠ አለኝታ ፤
ያስታውስ እንደሆን ልብሽ
ንቂ ፣ እሱ ነበረ ባልሽ ። . . . .
ተመልከቺ ይኸን ደሞ . . . እንደ ባለጌ ቤት ድግስ
ቅጥ ያጣ አዲሱ ባልሽ ፣ መላ አካሉ ሲተነፍስ ፤ . . . .
እውነትስ ዓይን አለሽ ታድያን ፣ ይኸን አረጋዊ ገፍተሽ
ይኸንን ፈንጋይ ባል ብለሽ !
ታድያስ ! ዓይን አለኝ ትያለሽ ? . . . ፍቅር ገፍቶኝ ነው በይ እንጂ
ላዲስ ፍቅር ደክመሽ ፣ ጠንተሽ ፣ ለፍርድ ስትዘጋጂ ፤
ፍርድስ ቢሉሽ ምን ፍርድ ነው
ካልጋ ዐመድ የሚወድቀው ?
ፍቅር የሌለው ውድቀት ነው ፣ የሥጋ ውድቀት ነው ፣ ዓሜን ፣
ፍርዱ በልብ ዓይን ሳይሆን ፣ ታይቶ በፍትወት ብሌን
እንዲያ የታወረው ዓይንሽ ፣ ባይመለከት ነው ልብሽ
መውደቅ ፣ መርከስ ፣ መልከስከስሽ ።



ኧረ ሲያል የት አል ፍርድሽ !
ባንቺ ዕድሜ የሥጋ ፍቃድ ፣ ፍትወት ከጫነብሽ ዛሩን
ካሸጠሽ የባልሽ ፍቅሩን
በወጣቱስ ላይ ምን ይሁን ?
ግብረ ገብ አመዳይ ትሁን ? እኮ አሰሚና ፍርዱን !

ንግሥት
ኧረ በቃህ ! ኧረ ተወኝ !
አትፈትነኝ ! አትጥበሰኝ !

ጎምሌት
ምን በወጣሽ ! ምን በወጣሽ !
የሕሊና እንቅልፍ ይውሰድሽ ፣ ይኸው አልጋሽ ! ይኸው አልጋሽ ! . .
ርካሽ !

—ጣዕረ መንፈስ ይገባል—

ቆ . . . ቆይ . . . ቆይ ! . . .

ንግሥት

ምነው ? ምነው ምን ሆንክ ?

ጎምሌት

ቆይ !

ጣዕረ መንፈስ

ተው ልጄ ተው ጎምሌት ልጄ ፣ እናትህን አትዝለፋት . . . .
አሁንም ቢሆን ፍቅሬ ናት ፣
አሁንም ቢሆን ሚስቴ ናት ፣
ለኔና ለእግዚአብሔር ተዋት ፤ . . . .
ምነው በቀልክን ችላ አልካት ?
ምነው በቀልክን ችላ አልካት ? . . .
አሁን በል እሰዋን አዋያት . . . .
አየህ ፣ ምንም አልታያት . . . .
ቃሌ ከቶም አይሰማት
በደካሞች ላይ ይጠናል ፣ የመታበይ እኮ ግዛት . . . .
በል ዝግ ብለህ አዋያት ። . . . .

ጎምሌት
እ—እንዴት ዋልሽ እማማ ?

ንግሥት
ደኅና ፤ . . . ምን ሆነሃል ? ምን ነክቶሃል ? ምን ብኩን ያናግርሃል ?

ዓይንህን ምን አስፈጠጠህ ? ምን እንደዚህ አፈዘዘህ ? ምነው ከሰል
አስመሰለህ?ኧረ ወዝክን ምን መጠጠህ?ደኅና ነህ፣ ኀምሌት?ደኅና ነህ?

ኀምሌት
ም—ምነው ምንም አይታይሽ ? አሁን ምንም አልሰማሽም ?

ንግሥት
ምን አለና ነው እሚታየኝ ? ምን ሰማህና ነው እሚሰማኝ ?

ኀምሌት
ተ . . . ተዩው ፣ ለካ አይሰማሽም
ለካ አንቺ አይሰማሽም . . . .

ንግሥት
ምን ሆንክ ኀምሌት ? ምን ሆንክ ልጄ ? ምን ሆንክ ልጄ ?

ኀምሌት
ተይ ፣ ተይ ፣ ራርተሽ አታራሪኝ
ተይ ፣ ተይ ፣ ባብተሽ አታባቢኝ ፤
አየሽ እኔ ቃል አለብኝ ፣ እኔ መልእክት አለብኝ ፤
እምባ ሳይሆን ደም አለብኝ ፣ . . . .
ቆራጥ መሆን ነው ያለብኝ ፣ . . . .
መልእክት ፣ ቃል ፣ አለብኝ ። . . . ሄደ አባባ . . . ሄደ አባባ ፣
አየሽው ? ያው ሄደ አባባ . . . .
—ጣዕረ መንፈስ ይወጣል—

ንግሥት
ንግሥት
ኧረ ልጄ ምን ሆነሃል ?
ዓይንህ ምን ራዕይ ይስላል ?
ቀልብህ ምን ይተበትባል ?
የሌለ ነገር ያሳያል ? የሌለ ነገር ያሰማል ?
ልጄን የተጠናወተው
ምን የሚሰልብ ቅዠት ነው ? ምን አዙሪት ራዕይ ነው ?

ኀምሌት
ይልቅ ራስሽን አታታዪው ፣ የኔ ጤና ካንቺ ይሻላል
ገና እንዳንቺ አልደነዘዝም ፣ ዓይቶ ፣ ሰምቶ ፣ ይሰማዋል ፤ . . . .
እናት ዓለም ፣ ሎሌ አትሁኝ ፣ ለራዕይ አትቸገሪ
እኔን አብዷል ብለሽ አንቺ ፣ በግፍሽ ዘፍቀሽ ልትቀሪ ?
አይምሰልሽ የኔ አዙሪት
ግፍሽ ነው አልታይ ያለሽ ፣ ተገትሮልሽ ፊት ለፊት !



ሕሊናን ማታለል ዋዛ ! . . . . የጣቱ ጥፍር ቢሰበር
ዘጠና ቀንድ አብቅሎ ነው ፣ ሁለንተናሽን የሚወር
ውሉን ባላላሽ ቁጥር ነው ፣ እልቦናሽ ላይ የሚከር ፤
ይልቅስ ሱባዔ ግቢ ፣ አጉል ቅሌት አትነግጂ
ያለፈውን ይቅር ካለሽ ፣ በቁም ሲያል አትውረጂ ፤
የእውነት ጥርሱ ምላጭ ነው ፣ ከቁርጠት ይልቅ ይቆርጣል
ሆኖም ፍትወት ባንቺ ዕድሜ ፣ ይቀፋል ፣ ይዘገንናል
ይምርሽ እንደሁ ለምኚው ፣ መልከስከሱ ይበቃሻል ።

ንግሥት
ኧረ ተወኝ ! ኧረ ተወኝ !
የእግዜር ይቅርታ ይቆየኝ ፣ ቀድመህ አንተ ተለመነኝ ፤
ልጄ ፣ ነፍሴን አቆስልከኝ ።

ኀምሌት
ኧረ ገና ምኑን አይተሽ ፣ ለነፍስሽማ ይብላኝላት
የኔ ማቁሰል መቼ በቅቷት !
ነፍሴ ቆሰለ እምትይው ፣ በንግግሬ መቀየም
ስተውሽ አጎቴ አልጋ ላይ ፣ ወጥተሽ ለመሥፈር አደለም !
መታመንና አለኝታ ፣ ከሞት አይከፋም አትፍሪ
እውነት ነፍስሽ ቆስላ እንደሆን ፣ ማረኝ ለማለት ሞክሪ ፤
ልብሽ እንኳ ባይሰማው ፣ ለወግ ያህል ይምሰልብሽ
ዛሬ እንኳ ግብዝነትሽ ፣ ለቅን ፣ ለበጐ ይሁንልሽ ፣
የመገበዝ ተግባር እንደሁ
ለከፉም ለበጐም 'አለሁ '
'አቤት ፣ ወዴት ! ' እዚያም እዚያም ፣ ለእውነት ሐሰት ፣ ለሐሰት ሐቅ
ባሕርይዋ ማማረጥ አያቅ ፤
ታድያ ዛሬ እንኳ ለወጉ ፣ ማረኝ ብለሽ በግልጥ ቃል
ሌላ እልፍኝ ዘግተሽ እደሪ ፣ እግዜር ይምርሽ ይሆናል
ዛሬ ለወግ ያደረግሺው ፣ ወይ ለነገ ይለምድብሻል . . . .
ልማድ ፊት እንዳሳዩት ነው ፣ ወይ ይጠፋል ወይ ያጠፋል
ከርሞም የሠለጠነ እንደሁ ፣ ተፈጥሮ ይሆናል ይባላል ፤
እኔንም ይቅር ይበለኝ . . . ከኔ መች ጸሎት ፈልጎ
ባንድ እጅ እኔኑ እንዳለንጋ ፣ ባንድ እጅም ገራፊ አድርጎ
ለዚህ ለፈጠረው ጉዳይ ፣ እኔ መጫሪያው ነኝ ላዩ
ጉዳዩን በኔ እየቀጣ ፣ እኔን ደሞ በጉዳዩ ፤
አጥፊና ጠፊ አድርጎናል ፣ የተአምሩ መግለጫ
እኔን ለሱ መቀጣጫ ፣ እሱን ለኔ መቀጣጫ ፣ . . .
በይ ደኅና እደሪ እናት - ዓለም ፣ የራስሽን አይተሽ ፍረጂኝ

# ገቢር አራት

## ት ፡ ፩

—ንጉሡና ንግሥቲቱ ይታያሉ—

ንግሥት
አብዷል ! አብዷል !
ጨርቁን ጥሏል !
ውሻ ! ውሻ ! ብሎ ዘሎ
ጶሎኔዎስን ወግቶ ገድሎ !
እኔንም ደሞ ሊደግመኝ
ሲያስጨንቀኝ ! ሲያስጨንቀኝ !
አብዷል ጎምሌት ! አብዷል ! አብዷል !
ጨርቁን ጥሏል !

—ሮዘንቅርስና ገድለ ስምዖን ተሯሩጠው ይገባሉ—

ንጉሥ
ምን ይባላል ? ምን ይባላል ?
አብዷል ብቻ መቸ ይበቃል !
ቶሎ አምጡልኝ ! ፈልጉልኝ ! . . .
እጁን ይዛችሁ አምጡልኝ !

—ይወጣሉ—

## ት ፡ ፪

—ጎምሌት ይገባል ። የጶሎኔዎስን ሬሣ ይሸሽጋል—

ጎምሌት
ያው በል እንግዲህ ተዘፍዘፍ ፥ ምን ይኸ ልክስክስ ችኩል !

—ሮዘንቅርስና ገድለ ስምዖን ከሩቅ ይጣራሉ—



ሮዘንቅርስ
ልዑል ! ልዑል ! ልዑል !

ገድለ ስምዖን
ልዑል ጎምሌት ! ልዑል ! ልዑል !

ጎምሌት
ልዑል ! ልዑል ! . . . አቤት ጣጣ
ከመቸው ተተነፈሰ ፥ ከመቸውስ ክንፍ አወጣ ? . . .
ልዑል ! ልዑል !

—ሮዘንቆርስና ገድለ ስምዖን ይገባሉ—

ሮዘንቅርስ
ምነው ልዑል ? ምነው ? ምነው ! . . .
በል ሬሣውን የት አረከው ?

ጎምሌት
አታውቅም እንዴ ? አታውቅም ?
አ አዳም መሬት ነህና ፥ ወውስተ መሬት . . . ትሰጥም ፤

ሮዘንቅርስ
ኧረ ንገረን ጌታዬ ፥ እግዜር ምን ይበል ይኸን ሲያይ !
ቤተ መቅደስ አብረን ወስደን ፥ ባይሆን እንኳ እዚያ ይቆይ ፥

ጎምሌት
አይ ! የለም ፥ አይሆንም የለም ፤
ከማንም መንጠቆ አፍ ጋር ፥ ደሞ ሬሣ ልሸካከም !

ሮዘንቅርስ
ልዑል ጌታዬ እኔን ነው ፥
መንጠቆ አፍ እምትለው ?

ጎምሌት
አዎ አንተን ነው ! . . .
ያፍ እልፊት መስሎህ አታድንቅ
በመንጠቆ አፍ ሲታዘዝ ፥ የንጉሥ ልጅ ምን ይበል ይልቅ ? . . .
ከንጉሥ አፍ ነገር ስትነጥቅ
ከወዳጆችህ ስትነጥቅ
ዳረጎቱን ፥ ሽልማቱን ፥ እያሸቃበጥክ ስታጭቅ
ልብ ውልቅ ! ልብ ውልቅ ፥ ውልቅ ! . . .
ንጉሡ ያመነህ መስሎሃል ፤
እንደ ገመሬ ዝንጀሮ ፥ መንጋጋው መሃል ይዘሃል !

መጀመሪያ የነከሳትን ፣ መጨረሻ ይውጣታል ።
የሚፈለግብህን ጥቅም ፤ እስክታደርስለት ነው ግብ
በመንጠቆ አፍህ ጭነህ ፣ ስትጠልፍና ስትስብ
ኋላ ሲሞላለት የልብ ፣
ላንተም ቦታ ይሰጥሃል
ጨምቆ ፣ መጥጦ ይተፋሃል ።

ሮዘንሮቅስ
ኧረ አልገባኝም ጌታዬ . . . .

ኀምሌት
ነው ። አልገባም ማለቱ ይሻላል ።

ሮዘንቅሮስ
ሬሣውን እኮ አሳየን ፤ . . . ንጉሡም ይጠብቁሃል !

ኀምሌት
ይጠብቁኛል እንዴ ፣ . . . ወይድ ?
ባፈ-ሙዛችሁ አጅቡኝ ፣ በሉ እንሂድ ፣ በሉ እንሂድ ።



. . . . ላንተም ቦታ ይሰጥሃል
ጨምቆ ፣ መጥጦ ይተፋሃል ።



# ት ፡ ፫

—ንጉሡ ፣ ባለሟሎችና አጃቢዎች ይታያሉ—

ንጉሥ
የሕገ መንግሥቱ መዝገብ ፣ የሚደነግገውን ግድ
ከመወሰናችን በፊት ፣ ሕዝቡ ለሱ ያለው መውደድ
ሌላ መዘዝ ደሞ እንዳይስብ ፣ መገንዘብ በአስተያየት ፍርድ
የግድ ይጠይቅብናል ፣ መሻት ፣ ብልህ ዘዴና እቅድ ፤
ሠራዊት የሚያስተጋባው
የልቡን ሳይሆን ያይኑን ነው ፤
ሌህ ነው ፣ መገንዘብ የምለው ፤
ሕጉም የሚሻው መሸፈን ፣
የበደሉን ክብደት ሳይሆን ፣ የተበደለው ሰው መጠን
እንደ ወዳጁ ብዛት ነው ፣ እንደ ተቆርቋሪው ወገን ፤
ስለዚህ የጶሎኒዎስ ፣ የቀብሩ ሥርዓት ይደበቅ
ግፈኛውም በሚያስቸኩል ፣ በግዞት አገሩን ይልቀቅ
አዋጁም ቶሎ አይታወቅ ። . . . .
ይሻላል ፣ አንነታረክ፣
መደበቁ ይበጃልና ፣ ሕዝባችን እንዳይታወክ ።
ኀምሌት መቸም በጥጋቡ ፣ መከራውን እንዳመጣው
ይሂድና እንግሊዝ አገር ፣ የገዛ መከራው ይፍታው ። . . . .

—ኀምሌት ፣ ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ይገባሉ—

አስከሬኑ ተገኘ ወይ ?

ሮዘንቅሮስ
የለም አላሳየን አለን ።

ንጉሥ
እንዴት ! ጶሎኒዎስ የት አል ኀምሌት ?

ኀምሌት
ገበታ ላይ ።

ንጉሥ
ገበታ ላይ ? የት ገበታ ላይ ?

ኀምሌት
እሚበላበት ላይ ሳይሆን ፣ እሚበላበት መሶብ ነው
አድፍጠው ይመገቡታል ፣ የሤራ ትሎች አብረው ።

የእርድ ከብት አደልበን
ከዚያም ከዚያም አርደን በልተን
ቦርጭ አውጥተን ፡ ፋፍተን ፡ ሰብተን
የትል ቀለብ እንሆናለን ።
ወፍራም ንጉሥ ፡ በገበታ ፡ በአዳራሽ ሰልፍ በአሳላፊ
ጉፋያ ደሃም እንደአቅምዋ ፡ አግበስብሳ ትርፍራፊ
ሆድን ሞልቶ እንደስልቻ
በልቶ ለመበላት ብቻ ። . . . .
በንጉሥ ሥጋ የፋፋን ትል ፡ ዓሣ አገኘችና ጥልፍ
ዓሣ አጥማጅ ዓሣዋን ቅርጥፍ ፡ ትል መልሳ እሱን ቅርጥፍ . . . .

ንጉሥ
እኮ የምን ምሳሌ ነው ? አስረዳን እንጂ ትርጉሙን ።

ኀምሌት
ቅርብ ነው ኧረ ምሥጢሩ ፡ ተደብቋችሁ ነው አሁን ?
በአንድ ለማኝ ዓሣ አጥማጅ ከርስ ፡ ንጉሥ ሽርሽር መግባቱን ?

ንጉሥ
ይልቅ ጶሎኒዎስ የት ነው ?

ኀምሌት
ምናልባት መንግሥተ ጽዮን ፡ ወይ ከዚያ ብትጠፉፉም
ሌላው ሥፍራ አትጠጣጡም ።
ጠፍቶ ቢጠፋ ፡ እስካንድ ወር
ከወደ ሰገነት መውጫው ፡ መዓዛው ሳይመጣም አይቀር ።

ንጉሥ
በሉ ሂዱ እዚያ ፈልጉት ፤ ሰገነቱ ጋ ይላችኋል !

ኀምሌት
ግድ የለም አትጣደፉ ፡ እስክትደርሱ ይጠብቃል ።

ንጉሥ
. . . የፈጸምከው ታላቅ ነውር ፡ ያሠጋልና ሕይወትክን
በሚያስቸኩል ወስነናል ፡ በሥራህ እጅግ እያዘንን
ወደ እንግሊዝ እንድትሄድ ፡ ቶሎ ለቅቀህ ምድረ-ዴንን ፡

ኀምሌት
ወደ እንግሊዝ ?

ንጉሥ
ነው ፤ ኀምሌት ።



ኀምሌት
ደግ ።

ንጉሥ
ደግ መሆኑ እርግጥ ነው ፡ የኛን ችግር ብታውቅልን ፤

ኀምሌት
መናፍስትም አውቀውታል ። ብቻ አሁን ዋናው ነገር ፤
ረኸሮሙን ጉዞ መጀመር ፤ . . . .
አደለም ጎበዝ ፡ አደለም ?
ደኅና ይግጠመን እናት ዓለም ።

ንጉሥ
እኔ እኮ አባትህ ነኝ ኀምሌት ።

ኀምሌት
ያው እኮ አደል ! እንዴት ፡ እንዴት ?. . .
አባት እናት ፡ ባልና ሚስት ፡ አንድ ሥጋ ፡ ያው አንድ አካል
ያስኬዳል እኮ ይባላል ። . . . .

—ይወጣል—

## ት ፡ ፩

—ፎርጠንብሮስ ከነሠራዊቱ ይታያል ። ከነጋድራሱ ጋር ይነጋገራል—

ፎርጠንብሮስ
በል ነጋድራስ ፡ ወደ ምድረ-ዴን ንጉሥ ዘንድ በፍጥነት ደርሰህ ፡ የአክብሮት ሰላምታዬን አቅርበህ ፡ ድንበራቸው ላይ ማረፋችንን አስረድተህ ፡ ቀድሞ በተጻጻፍንበት ቃል መሠረት ፡ በምድረ-ዴን ግዛት ላይ አቋርጠን ፡ በፖላንድ ላይ እንድንዘምት ፡ የይለፍ ፍቃዱን ይዘን ፡ ጉዞ መጀመራችንንና ፡ ተግባራችንን እንጂ ከተግባራችን ሌላ ምንም ጉዳይ እንደሌለን ፡ ግርማዊነቱ ቢሻም ይህንኑ ዓላማዬን በቅርብ ላስረዳ ፍቃደኛ መሆኔን ጭምር አስታውቅልኝ ። ረኸሮም ዕድሜ ለግርማዊነትህ ብሏል የኖርዌይ ልዑል ፎርጠንብሮስ በልልኝ ። ፈጠን በል ።

ነጋድራስ
እሺ ልዑል ጌታዬ ።

—ፎርጠንብሮስና ሠራዊቱ ይወጣሉ ። ኀምሌት ፡ ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ከአጃቢዎች ጋር ይገባሉ—

ኀምሌት
ጌታ ፤ የማን ሠራዊት ነው ይሄ ?

ነጋድራስ
የኖርዌዩ የልዑል ፎርጠንብሮስ ነዋ ጌታ ።

ኀምሌት
ጠቅላላውን የፖላንድ ምድር ለመውረር ነው ፣ ወይስ ለጠረፍ ግፊያ ምክንያት ብቻ ነው ?

ነጋድራስ
በእርግጥ ከሆነ . . . ከስም በቀር ሌላ አንዳች ጥቅም የሌላት ፣ ኩርማን ታህል መሬት ፣ ያመት ግብሯ ካምስት አሞሌ ያልበለጠ—አምስት አሞሌ ነው እምልዎት—ለኖርዌይም ለፖላንድም ፋይዳ የሌላት ቦታ ለመያዝ ነው ጌታ ።

ኀምሌት
ያማ ከሆነ የፖላንድ ሠራዊት ለስዋ ሲል አይቋቋማችሁም ማለት ነዋ ።

ነጋድራስ
አይ አይደለም ጌታ ፤ ከብበው ፣ ሠፍረው ፣ መሽገው ይጠብቁናል ።

ኀምሌት
. . . ሁለት ሺህ የሚሆን ጀግና ፣ የያንዳንዱ ሕይወት እንኳን በቤሳና ባሞሌ በወርቅ ግምት የሌለው ፣ እንዴት ፋይዳ ለማትሞላ ኩርማን መሬት ይተላለቅ ? ሃብት ሲትረፈረፍ ፣ የሰላምም መደላድል ሲያመች ፣ ሃብቱም ሰላሙም አጥግቦ አስክሮ ከውስጥ ከገነፈለ ፣ ሟቹስ ለምን እንደሚሞት መች አመዛዝኖ ! እግዜር ያክብርልኝ ጌታ ።

ነጋድራስ
አሜን ፣ ጤና ይስጥልኝ ።

—ነጋድራስ ይወጣል ። ሮዘንቅሮስ ፣ ገድለ ስምዖንና አጃቢዎቹም ገንጠል ብለው ያርፋሉ—

ኀምሌት
. . . እሮይ እንኳ ብዬም ባላውቅ ፣ የቁስሌ ቀስቃሽ ብዛቱ ፣
ሰው በዕድሜው ፣ ሰው በዘመኑ ፣ ካልሠራበት በሕይወቱ
በልቶ ከተጋደመበት ፣ ኑሮው ምንድነው ምክንያቱ
ካውሬ ምንም አልተሻለ ። ምን ይላል የፈጠረንስ ?
የአእምሮ ልቦናን ብርሃን ፣ ሸልሞን ስናበሰብስ ? . . .
የኔስ ካውሬ በምን ሊሻል ፣ ቢነገር በይፋ አንደበት
ሃሳቤን ማግበስበስ እንጂ ፣ አንዳች ፍሬ ላልሠራበት ፤



የትዕግሥት ፣ የጥንቃቄ ፣ የፍርሃት ፣ የስንቱን ምክንያት
ማስታመም ማሰላሰሉ ፣ መሥጋት ፣ ማውረድና ማውጣት . . . .
አለሁ ይኸው ቅገሮት ይዞኝ
ጽኑ የበቀል ቃል ኖሮኝ ፣ ፍቃድ ፣ መሣሪያ ፣ አቅም ኖሮኝ
ከቅገሮት አላልፍ አልኩ እንጂ ፣ የሃሳብ ብዛት ሰንክሎኝ ፤ . . . .
አሁን የዚህ የሠራዊት ፣ የስንቱ ጀግና መሄጃ
ዓይን የሚወጋ አርአያ ነው ፣ ቁስሌን የሚያክ ማስረጃ ፤
መንፈሱ በትልቅ ዕቅድ ፣ በተጫረ ወጣት መስፍን
የጦርን ምዕዓት በናቀ ፣ ለልበ ንቁ ሃሳበ ጭፍን
ይኸ ሁሉ ጉልቤ መሣፍርት ፣ ሕይወቱን ፣ ትዳሬን ሳይል
ሞት አለ ፣ ደም አለ ሳይል
ቆርጦ ወደ ስቃይ ሲሄድ ፣ ከመሪው ጋር ተግተልትሎ
ስም እንጂ ፋይዳ ለሌላት ፣ ላንዷት ቁራጭ ምድር ብሎ ፤ . . . .
እውነተኛ ታላቅነት ፣ ከሃሳብ ርቀት ጋር ቢሆንም
የስም ጉዳይ ማሰላሰል ፣ ምርምር አትጠይቅም ፤
የወኔ ምሥጢር ነውና ፣ በጨዋ ዘንድ የታመነ
ለሰባራ ስንጥር መሞት ፣ የክብር ጉዳይ ከሆነ ፤
ታድያን እኔስ ፣ ክብር አለኝ ወይ ? . . . ያባቴን በቀል ጠጥቼ
የናቴን ውርደት እያየሁ ፣ በብስብስ ሆዴ ከትቼ
የደም ፣ የወኔ ፣ የአእምሮ ፣ የሕሊናን ሙግት ትቼ
እንዳይረቱኝ አግባብቼ
አባብዬ አስተኝቼ ፣
ቁስሌን የሚያመረቅዝ ጦር ፣ የሚያፌዝ ባልጫ ሃሞት
ለስም ሲል አንድ አገር ጀግና ፣ ለአንዲት እፍኝ መሬት ሲሞት ፣
አንዳች ጥቅም ለማትሰጠው ፣ እንኳን አርሷት ልታበላው
ለመቃብር ለማትበቃው ፤
ለዓይኔ ሥጋ ምስክሬ ፣ በቁሜ ለሞትኩት ለኔ
አሳየኝ ፣ አሳየኝ ባይኔ ። . . . .
ከእንግዲህ ወዲያስ ያለደም
ነፍሴን የሚያድናት የለም ።

—ሮዘንቅሮስ ይገባል—

ሮዘንቅሮስ
ኧረ እንሂድ እንጂ ልዑል ።

ኀምሌት
ነው ፣ እንሂድ ፣ አዎ ፣ እንሂድ ።


—ይወጣሉ—

# ት ፡ ፭

—ንግሥቲቱና ሆራትዮስ ይታያሉ—

ንግሥት
የለም ፡ አላነጋግራትም አልኩ ።

ሆራትዮስ
ኧረ ንግሥት ሆይ ፡ ጤናም ያላት አትመስል ። እንደኔስ ፡ ባያዩአት ነው እንጂ ምንኛ በራሩላት ነበር በሁኔታዋ ።



. . . . አገር ትለብለብ አሉ ፡ ጓዳ የተጫረች እሳት ፤ . . . .

ንግሥት
እኮ ምን አርጉኝ ነው እምትለው እስዋ ደሞ ?

ሆራትዮስ
አንብታ አንብታ ማቀቀች ፡ ስለአባቷ ሞት ብቻዋን ታነበንባለች ፤ ዓለም ምን የተንኮል ሲያል ናት እያለች ደረቷን ገልጣ ትደበድባለች ፤



ጣዕሙ የተመሳቀለ እንቆቅልሽ ታልጉመጉማለች ፡ . . . ኧረ እንጃላት እንዲህስ ሆና የምትዘልቅ አትመስልም ንግሥት ሆይ ።

ንግሥት
ወይ ጣጣ !
መቸም መከራ ዛብ የለው ፡ እንደዜ እግር ካወጣ ፤
በል እስቲ ሂድና ጥራት
የሆነችውን እንስማት ፤
አገር ትለበልብ አሉ ፡ ጓዳ የተጫረች እሳት ፤ . . .

—ወፌ-ይላ ቀልቧን ስታ ትገባለች—

ወፌ-ይላ
ሰላም ለከ ንጉሥ ፡ ንጉሥ ገላውዴዎስ ! . . .
የት አለ ዘንካታው ፡ ብፁዕ ፡ ብሩክ ፡ ቅዱስ ?

ንግሥት
ምን አልሽ ወፌ-ይላ ?

ወፌ-ይላ

—ትዘፍናለች—

‘ አጋግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ . . . . ’
ከግዞተኛ ፡ ስጫወት ውዬ ፡ ስጫወት ውዬ
የት ላይ ነው ባክህ ፡ የሰው ልክ ፡ የሰው ልክ
አባዬን ገድለህ ፡ አንተም ሄድክ ፡ አንተም ሄድክ
‘አጋግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ . . . . ’


—ንጉሡ ይገባል—

በልቤ መሃል ፡ ንሥር ሰፍሮ ፡ ንሥር ሰፍሮ
አባዬን ነጥቆኝ ፡ ትቶኝ በርሮ ፡ ትቶኝ በርሮ
እኔን ያብርረኝ ፡ ያክንፈኝ ፡ ያክንፈኝ
እግዞት አገር ይስደደኝ ፡ ይስደደኝ ፤
የባዕድ አገር ፡ መራራ ነው ፡ መራራ ነው
የጐበዝ ልቡ ፡ ተራራ ነው ፡ ተራራ ነው
የሴት ልጅ አንጀት ፡ ደካማ ነው ፡ ደካማ ነው ፤
የቀበርኩ እንደሁ ፡ ሁለት ባንዴ ፡ ሁለት ባንዴ
አባዬን መሬት ፡ እሱን ሆዴ ፡ እሱን ሆዴ
‘አጋግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ . . . . ’

ንጉሥ
ከመቼ ወዲህ ነው እንዲህ የሆነችው በሉ ?

ወፌ-ይላ
‘አጋግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ . . . .’
ከግዞተኛ ፡ ስጫወት ውዬ ፡ ስጫወት ውዬ
ጉዴ ይደበቅ ፡ ካፌ አይውጣ ፡ ካፌ አይውጣ
ጋሼ በፈረስ ፡ እስኪመጣ ፡ እስኪመጣ ፡
‘አጋግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ’
እኔን የጠፋኝ የሰው ልክ ፡ የሰው ልክ
አባዬን ገድለህ ፡ አንተም ሄድክ ፡ አንተም ሄድክ . . . .

—እያንጐራጐረች ትወጣለች—



‘ አጋግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ ፡ ግግም ብዬ . . . . ’
ከግዞተኛ ፡ ስጫወት ውዬ ፡ ስጫወት ውዬ

ንጉሥ

ተከተላት ፤ እባክህ ተከተላት ።

—ሆራትዮስ አብሯት ይወጣል—

. . . አልቆላት ። . . . በልጆች የእንቆቅልሽ ጨዋታ ፡ ጭራቅ አንዴ ራሱን ሲሉት ዘጠኝ ራስ ፡ ሁለተኛ ሲደግሙት ዘጠና ራስ ፡ ሲያሠልሱት ዘጠኝ መቶ ራስ ያበቅላል ይላሉ ። መጀመሪያ የልጅሽ ዕብደት ፡ ቀጥሎ የዚች የልጅ አባት ሞት ፡ ከዚያ የስዋ ዕብደት ፡ በዚህ ላይ የሕ



ዝቡ ማንሰራራትና መፍጨርጨር ፡ አሁን ደሞ የጶሎኔዎስ ወንድ ልጅ ላርቆስ ከፈረንሣይ አገር ሾልኮ መጥቶ ፡ በከተማውና ባባቱ ወገኖች ልብ ሤራ እያጫረ ፡ በነገር እየመረዘ አሸፍቶብን ሊወረን በጥድፊያ ይገሠግሳል አሉ !

—የሠራዊት ሁከትና ሽብር ከደጅ ይሰማል ። የእልፍኝ አስከልካይ ይገባል—

ም—ምንድነው እሱ ?

እልፍኝ አስከልካይ
ላ — ላርቆስ ! ላርቆስ ነው ግርማዊ ! — ኧረ ሕዝቡ ! ኧረ ጃንሆይ !
ኧ — ኧ — ኧረ — ለነፍስዎ ያምልጡ ! !

ንግሥት
እንዴት — እንዴት — ይኸ የምድረ-ዴን እከካም ሁሉ !

—በሩ ይፈነገላል ፤ ላርቆስና የሠራዊቱ ግንባር ቀደሞች ተንደርድረው ይገባሉ—

ላርቆስ
እኮ የት አለ ይኸ ንጉሥ ! ጐበዝ እናንተ በር ያዙ !
እኮ የት አለ ! ይኸ ርኩስ ! የት አል ! በሩን በሩን ያዙ ! . . .
ይስሙኝ ንጉሥ ! ይስሙኝ !
አባቴን ይስጡኝ !
አባቴን !
ወላጄን አሳዳጊዬን !
ይመልሱልኝ አባቴን !

ንግሥት
እ — እኮ ዝግ በል ልጅ ላርቆስ ፡ . . . .

ላርቆስ
ዝግ የሚል ደም
ውስጤ የለም !
ዝግ የሚል ደም ፡ የኔ አደለም !
ካባቴም አልተወረሰም
ያጥንቱ ፍላጭ አይደለም ! የሥጋው ቁራሽ አይደለም !

ንጉሥ
ምነው ላርቆስ ዐመፅህ ፡ እንዲህ ግሥላ መሰለ ?
. . . አትያገርው ተይ ገርትረድ ፡ ምንም እሚያረገኝ የለ ።
ንገረኝ ፡ ምነው ንዴትህ ፡ እሳተ ገሞራ አከለ . . . .
ልቀቂው እንጂ ገርትረድ ፡ ይንገረኝ እሚለው ካለ ።

ላርቆስ
አባቴ ፣ አባቴ የት አል !

ንጉሥ
ሞቷል ።

ንግሥት
ቢሞት ታድያን ባንተ እጅ አደል ።

ንጉሥ
ቆይ ፣ እሱው ይጠይቀኛል ።

ላርቆስ
እኮ በማን እጅ ሞተ ? . . . ኋላ ይህ ዋዛ አያዋጣም !
ይህ መዝናናት አያዋጣም !
ባለሟልነት ፣ መታመን ፣ ለኔ ይቺን ያህል አይረባም ።
ሕሊና ፣ መከበር ፣ ሹመት ፣ ቢሻ አራት እግሩን ይብላ
እንኳን ጉድ የጉድ ጉድ ይፍላ !
ገዳዩን ብቻ ልወቀው ፣ እንኳን ሞት ምጽዓት ቢመጣ
ደሙን ሳልጠጣው አልቀርም ፣ ያባቴን ደም እንደጠጣ !

ንጉሥ
መልካም ።
የውድ አባትክን ባላንጣ ፣ ለማወቅ ሲፈላ ደምህ
ወዳጁንም ጠላቱንም ፣ አብሮ መጥረግ ነው በቀልህ ?

ላርቆስ
ጠላቱን ! ጠላቱን ብቻ ! . . . ወዳጆችማ ቢኖሩት
መቸ ዝም ይሉ ነበረ ፣ እንዲያ ሸፋፍነው ሲቀብሩት ?
አሁንም ወዳጅ ነኝ የሚል ፣ ያባቴን ገዳይ ካሳየኝ
እኔም ወንድሙ ፣ ወዳጁ ፣ የዘለዓለም አሽከሩ ነኝ !
ለኔ ቃሉ ሕይወት ነውና ፣ አባቴ ሕይወት እንደሰጠኝ ።

ንጉሥ
እንዲህማ በጥሞና ፣ ስትጠይቀኝ በቁም ነገር
በመልካም ልጅ አነጋገር ፣ በጨዋ ልጅ አነጋገር
እኔም አሳውቅሃለሁ ፣ በዓመፁ እንደሌለሁበት
አንተም ፣ ወዳጁም ፣ አገሩም ፣ እንዲያውቅ ይሻል ይኸን እውነት ፤
የሱ ሞት የወዳጄ እጦት ፣ ብቸኛ አርጎኝ ይኸውና
ከሐዘኑም አልተላቀቅሁ ፣ እንኳን ደም ልቃባውና ።



ስለዚህ ሳታውቅ አትፍረድ ፣
ሃሰት ስለማያዛልቅ ፣ በሰውም ዘንድ ፣ በእግዜርም ዘንድ ።

—ወፌ-ይላ እያቅራራች ትገባለች—

ላርቆስ
ወዮ እህቴን ! . . . ወየው እኔን ! . . . ወፌ-ይላ . . . . .
ምን ወሰደሽ ? የምን መተት ? ኧረ የምን ዓይነ ጥላ ? . . .
ንቂው ያበባ ዕድሜ መንፈስ ፣ እንደ እርግማን ድንገት ሲፈዝ
እንደ ጫጩ አሮጊት ሲቦዝ ፣ እንደ ቸነፈር ዋግ ሲነብዝ . . . .
ተፈጥሮ ለወጣት ብርሃን ፣ ፍቅርን ብትለግሥም እኮ
መቅሰፍቷም እትከሻው ላይ ፣ ይጠብቃል አብሮት ታክኮ . . . .

—ታቅራራለች—

ወፌ-ይላ
ጀግና ሲመጣ ! ሎጋው ሽቦዬ !
ጐበዝ ሲሰለፍ ! ጊዜ እየለየ !
የጫረው እሳት ፣ ሲፈጀው ታየ . . .
ምሥጢር ነው ብለው ! ደረት ሳይጣል !
አልቃሽ ሳይወጣ ! ይፍታህ ሳይባል !
ምነው እሬሳው ! እንደ ጥንብ ይጣል ! . . .
እሽሩሩሩ ! የንጉሥ ልጅ !
ስሞታህ ብቻ ! ቀረ በኔ እጅ . . . .

ላርቆስ
አይ ዕድልሽ ፣ አይ የናቴ ልጅ ፣ ለዚህ ዳረጉሽ ?

ወፌ-ይላ
እሽረረረረ ! እሽረረረረ ! . . .
እሽረረረረ ! እሽረረረረ ! . . . ዘራፍ ! ዘራፍ ! . . .

—ትወጣለች ። ከደጅ ስታፏጭና ስታንጐራጉር ድምፅዋ ይሰማል—

የእማማ ዶሮ ጭር አለች
ጭር አለች ፣ ጭር አለች ጫጩች
እንቁላልዋን ጨፈለቀች
ጫጩቶችዋን እየዳጨች
ጭር አለች ፣ ጭር አለች ጫጩች . . . .

ላርቆስ
ዓይንህ ያያል አንተ አምላክ ! እውነት ዓይንህ ያያል !

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARIES

ንጉሥ
እኔም በወዳጄ እጦት ፡ ከርሜአለሁ ስብረከረክ
ስለዚህ እረዳዋለሁ ፡ የመንፈስህን መታወክ ፡
አሁንም በጋራ መርዶ ፡ እንደማመጥ ከፈቀድክ
ሐዘኑንም የግል አርገህ ፡ ልትከለክለኝ ካልወሰንክ ፤ . . . .
የልብ የምትላቸውን ፡ ወዳጆችህን መልምለህ
ያባትክን አሟሟት ሥሩን ፡ ተመካክረህ ፡ አሰላስለህ
ጥናቱን ካጣሩ ኋላ ፡ አስገብቷል ቢሉህ እጄን
መንግሥቴም ፡ ዘውዴም ፡ ሕይወቴም ፡ ያለ የሌለኝ ልቅ ይሁን ።
ከገዛ ወዳጆችህ አፍ ፡ እውነተኛው ቃል ሲመጣ
ለኔ ፈርደው ሲገሥጹህ ፡ ስሜን እንኳ እንዳታሳጣ
ያኔ ከትእግሥት ጋር ፡ ደሙን አብረን እንወጣ
እስከዚያ ግን ያለ ፍሬ ፡ በከንቱ አንጨምር ጣጣ ።

ላርቶስ
እኔም ሌላ ጸሎት የለኝ ፡ አንተ አምላክ ፡ ስማኝ ፡ አድምጠኝ
ያባቴን አሟሟት ሰበብ ፡ ምን ነጣቂ እንደ ነጠቀኝ
አብረህ መርምረህ አሳየኝ ።
ሞቱን ወገኑ ሳይሰማ ፡ ተሸፋፍኖ መቀበሩ
በቂ ሥርዓት ሳይደረግ ፡ እንደ ጥንብ መወርወሩ
ላገር ፡ ለንጉሥ በሠራ ፡ መቃብሩ መሠወሩ
መርምረህ ንገረኝ አምላክ ፡ እምን ላይ ነው መነወሩ ?

ንጉሥ
ይነግርሃል አትጨነቅ ፤ በይፋ ታያለህ የግድ
አሁን ተከተለኝና ፡ አመራመሩን እናቅድ . . . .
ወይ በቀልህ እመርከብ ላይ ፡ ካምላክ በተላከ መብረቅ
ማን ያውቃል እንደ ጸሎትህ ፡ ባላንጣህ ላይ እንደማይወድቅ ? . . .

—ይወጣሉ—

# ት ፡ ፮

—ሆራትዮስና አንድ አስተናባሪ ይታያሉ—

ሆራትዮስ
የምን መርከበኞች ናቸው እነሱ የሚፈልጉኝ ?



አስተናባሪ
ኧረ እንጃ ጌታ ፤ ደብዳቤ ይዘናል ይላሉ ።

ሆራትዮስ
አስገባቸዋ ።

—አስተናባሪው ሲወጣ ሁለት መርከበኞች ይገባሉ—

መርከበኛ
ሆራትዮስ ማለት እርስዎ ነዎት ጌታ ?

ሆራትዮስ
ነኝ ።

መርከበኛ
ወደ እንግሊዝ አገር ይጓዙ ከነበሩ የምድረ-ዴን መልእክተኞች መሐከል አንደኛው ነው አደራ ብሎ የላከን ። ሆራትዮስ ለሚሰኝ ሰው በቀር ደብዳቤዬን እንዳትሰጡ ብሎናልና መቸስ . . . .

ሆራትዮስ
ነኝ ፡ ነኝ ፡ ሆራትዮስ ነኝ አይዟችሁ ።

—ደብዳቤውን ተቀብሎ ያነባል—

‘ ይድረስ ለወዳጄ ለሆራትዮስ ፤ ይኸን አንብበህ እንዳበቃህ እኒህ ዳባ የለበሱ ሁለት ጐበዛዝ ፡ ሌላ ለንጉሡ የላክሁት ደብዳቤ ይዘዋልና ፡ ተቀብለህ ፡ ለንጉሡና ለናቴ በእጅ ስጥልኝ ። ፍሬ ሃሳቡ የሚለው ድንገት ሳናውቀው የመርከብ ወንበዴዎች እባሕር ላይ ጦር ገጥመውን እኔን እንደማረኩኝና ፡ — ኋላም ራርተውልኝ ፡ አገሬ ምድረ-ዴን ወደብ ላይ ለነፍሳቸው ሲሉ ስለተዉኝ ፡ እኔም ሳልፈቅድ በግድ ይኸው ተመልሼ እቤቴ መምጣቴን ነው ። ይሁንና ዋናውን ፍሬ ነገር ለብቻህ እንድታውቀው ፡ ባንተ ደብዳቤ ላይ ብቻ አስፍሬአለሁ ። ወንበዴዎቹ የይምሰል እንጂ የእውነት ወንበዴዎች አይደሉም ። ያባቴ ታማኝ ባላገሮች ናቸው ። ሮዘንቅሮስና ገድለ ስምዖን ፡ ንጉሡ ለሶስታችን መተዋወቂያ ብሎ አሽጐ የሰጣቸውን ደብዳቤ ብቻ ይዘው ፡ ከወንበዴዎቹ አመለጥን በማለት ወደ እንግሊዝ ወደብ በመጓዝ ላይ ናቸው ። የተሸከሙት ደብዳቤ ምን መልእክት እንደያዘ አያውቁትም ። እኔ ግን እነሱ ተኝተው ሳለ ተሸሽጌ ስላነበብኩት ፡ አወቅሁት ። ለኔ አንገት መበጠሻ የመጨረሻዩቱ ሜራ ነበረች ።

ሆኖም እነሱ እንደተኙ ፡ ስሜን ከውስጡ ሠርዤ ፡ የነሱን አክዬ ፡ እስከ ዛሬ ተለይታኝ በማታውቀው ባባቴ የቤተ መንግሥት ማኅተም አትሜ ፡ አሽጌ ፡ መልሼ አስቀመጥኩላቸው ። ወዲያው ፡ አንድያህን ዳን ሲለኝ ፡

ተማርኬ ተመለስኩ ። ለኔ የተባለ መጨረሻ የነሱ ሆነ ። ስንገናኝ በዝ ርዝር አጫውትሃለሁ ፤ እነዚህ ወንበዴ መሰል ወዳጆቼ ያለሁበትን ይመ ሩሃልና ለንጉሡ የጻፍሁትን ደብዳቤ ተቀብለህ ፣ በእጅ ከሰጠህልኝ በኋላ ፣ ሌሊቱን ከነሱ ጋር ወደኔ ገሥግሥ ። በሰላም ይግጠመን ። ወዳጅህ ልዑል ጎምሌት ዘምድረ-ዴን ።' . . . .

—መርከበኞቹ ሌላ ደብዳቤ ይሰጡታል ። ይወጣሉ—

## ት ፡ ፯

—ንጉሡና ላርቆስ ይገባሉ—

ላርቆስ
ፈርማውና ማኅተሙ በእርግጥ የሱ ነው ?

ንጉሥ
ነው ።

ላርቆስ
ይምጣ ፣ ይምጣ ፣ ይምጣ !
እዚህ ብትሆን ነው የሞቱ ዕጣ

ንጉሥ
ነው ፣ ነው ፤
ዕጣ ክፍሉ ነው የላከው ። . . . .
ላርቆስ ፣ ጥሩ ዘዴ አለኝ ፣ ፍጹም ፣ ፍቱን ዘዴ አለኝ
ለበቀልክም ፣ ለኔም ዕቅድ ፣ አንተ ቀኝ እጅ ከሆንከኝ ።

ላርቆስ
ለዚህ ነው እንጂ እንግዲያማ ፣ ለዚህ ካልሆንኩ ምንድነኝ !
ላባቴ ገዳይ ደም መላሽ ፣ እኔን መዛሪያ ሲመርጠኝ
ጸሎቴንና ብሽቀቴን ፣ እውነት አምላክ አደመጠኝ ፤
እህቴን እንደማትሆን አርጎ
አባቴን በድንገት ቀጥፎ ፣ ለሽሽግ መቃብር ዳርጎ
ከመጣማ ዓለም ሆነ ! ያውም ሳይጠሩት ፣ ፈልጎ !

ንጉሥ
. . . አንድ የባዕድ አገር ጀግና ፣ ላርቆስ ፣ በቅርብ የሚያውቅህ
በሰይፍ አመካከት ዝናህ ፣ በሙሉ ልብ የሚያደንቅህ ፣
የታወቀ ፈረሰኛ ፣ ያንድ የሩቅ ንጉሥ ባልደራስ
ፈረንሣዊ አገር የሚያውቅህ ፣ የጨዋ ልጅ የዝናህ ዋስ



ስላንተ አድንቆ ሲናገር
ያን ጊዜ እኔም አባትክም ፣ ጎምሌትም እዚሁ ነበር
በቅናት ተቃጥሎ ገብኖ ፣ የደም ሥሩ እስኪግተረተር
ሲያደምጥ የዝናህን ነገር ።
እና ይኸ ባዕድ ጀግና ፣ ሰንጋ ፈረስ ላይ ጉብ ሲል
አብሮ የተፈጠረ እንጂ ፣ የልምድ ሞያ ሳይመስል
ሽንጡ እንደሰንበሌጥ ሲሰብቅ ፣ የጉግሥን ሥርዓትና ውል
ትንግርት ነው እሚያሳክል ፤

ላርቆስ
አውቀዋለሁ ፣ ወዳጄ ነው ፣ እንዴ ፣ ባልደራስ ክልሉ !

ንጉሥ
እሰየው ! እሱም ያውቅሀል ፣ ጀግና ከጀግና ነው ውሉ ።
ታዲያን ስምህ ካፉ አትጠፋም ፣ የጦር አያያዝ ሞያህን
ሲያመጣው አመካከትህን
ያጠቃቅ ፣ ያከላከልክን ፣
ያፈጣጠን ተሰጥዎህን
ዝናህን ሲተርክልህ
ጭልፊት ፣ ጥይት ፣ ነው የሚልህ ፣ . . . .
ምድረ-ዴን አልወለደችም ፣ የለም ፣ ሲል የሚቋቋምህ
ይኸኔ የጎምሌት ቅናቱ
በይፋ ይታይ ጀመረ ፣ ሳምባ እስኪመስል ግርጣቱ ፤
ወዲያው ጥርሱን ገልፈጦ አርጎ ፣ ' እስቲ እንግዲህ እናያለና
ላርቆስ ይምጣና በጤና ፣'
ሲል ጊዜ እንግዳው ጀግና ፣ ከንቀቱ ፣ መደነቁ
አሸንፎት ፣ እንደ ንዴት ፣ በዓይን ብቻ ተሳሳቁ ፤ . . . .
አሁንም ቢሆን እንግዳው ፣ አለ ፣ ጥቂት ቀን ይቆያል ፣
ጠይቀው ፣ ያጫውትሃል ። . . . .
ላርቆስ ፣ እንደራስህ ነፍስ ፣ ትወደዋለህ አባትክን ?
ወይስ ፣ እንደፍትሐት ቄስ ፣ ሐዘን አጐናጽፈህ ፊትክን
በምግባር ብቻ ፣ ያለ ልብ ፣ ለይስሙላ ነው እባክህን ?

ላርቆስ
እንዴት እንደዚህ ይሉኛል !
ምን ቢያስቡ ይጠይቁኛል !
እንዴት ይጠረጥሩኛል !

ንጉሥ
. . . የፍቅር ክብደት በጊዜ ፣ መመጠኗን ስለማምን

ጥርጣሬ ብቻ ሳይሆን ፣ ልፈትነው ነው ልክህን ፤
መውደድ እንደየጊዜው ናት ፣ እሳትዋ ወይ ለብታዋ
ከርሞ ይመጠናል ኃይልዋ ።
ድንገት የመቀየር ሳይሆን ፣ ክብሪቷ እንደተጫረ
ማቀገዘቀገርው በጊዜ ልክ ፣ አለ አብሯት የተፈጠረ ፤
ጽኑ ፍቃድ ግን አይሞትም ፣ ከእምነት ጋራ ከታቀደ
ባለቤቱንም እስከ ግብ ፣ ተያይዞ ካልወሰደ ፤
በጊዜ ብዛት በለዘ
ወይም ጥርሱ ደነዘዘ
የቀደምት ኃይሉ ፈዘዘ
ቢያንቀላፋና ቢያንገላጅ ፣ አይለቅም ሥሩ ከያዘ
ያ የጽኑ ፍቃድ ቁስሉ ፣ አድሮ እያመረቀዘ
እንደንፉግ ሰው ሰመመን ፣ ተግ ይላል እያስተከዘ ፤
. . . ኅምሌት ነገ ተገትቶ ፣ ራሱ ይመጣል ሳንፈቅድ
ምንድነው ታድያ ያንተስ እቅድ ?

ላርቆስ
እስኪመጣ ይታገሱኝ ፤
ማንቁርቱን እንደፍሪዳ ፣ ስተለትል ይጠይቁኝ ።

ንጉሥ
እንደፍሪዳ ፣ እንደሰው ፣ ወይ እንደዶሮም ቀንጥሰው
ፍሬ ነገሩ ሞቱ ነው ፤
ይኸም ፍቱን እቅድ አለው ።
. . . ኅምሌት ሲደርስ ወይም ሳይደርስ ፣ ያንተንም መምጣት ይሰማል
ይኸኔ ያን ጀግና እንግዳ ፣ ወዳጅክን ፣ በጉን ይልኳል ፤
በዝግታ ነገር ማስጫር ፣ ያን ንቀቱን እንዲያስታውስ
ወይም ነገሩን ጠርጥሮ ፣ አሌ እሚል ቃል እንዳይመልስ
ልጅ ላርቆስ ፣ በጉበዝ ወግ ፣ በጦር ቅልጥፍና ሥርዓት
እንዲያው ለጫወታ ያህል ፣ ልትገጥመው መሻትክን ማምጣት ፤
ደም መፋሰስ ከሌለበት ፣ ለትግል ወግ ከተባለ
ምን አለበት ብሎ ይመጣል ፣ ፈራሁ አይል ፣ ይሉኝታ አለ ፤
ሲመጣ በጫወታው ላይ ፣ ያመረርክ ሳታስመስል
በስህተት ድንገት አምልጦህ ፣ ጦርክን እልቡ ላይ ትክል . . . .
ያንተን ሞያ ግማሽ የለው ፣ ወግ ነው ብሎ ሲንደፋደፍ
በቀልህን እንደዋዛ ፣ እፎይ ብለህ ፣ ሰላም ማትረፍ ፤ . . . .
በዚህ ላይ ምናልባት ፣ ድንገት ፣ ወይ ተወግቶ እንኳ እንዳይድን
በስህተት ፣ ልብህ ራርቶለት ፣ ድንገት ፣ ብትገታው እጅህን ፣
ትንሽ ጭረት ካስነካኸው ፣ ለስሙ ያህል ፣ ለወልከፍታ



የሥር ቅመም ብጤ አለቺኝ ፣ የማታዋዛ ለአንድ አፍታ
የመድኀኒትም መድኃኒት ፣ አዳፍኔ ፣ ፍቱን ጠብታ ፤
እስዋን ቀብቶ የጦርክን ጫፍ ፣ ጨዋታው ላይ እንዲያው ለወግ
ለዐመል ያህል አከክ ማረግ ፤
በተረፈ ሆድ ይፍጀው ነው ፣ የኔም ሥጋት ያንተም በቀል
ዓሜን ሳይል ሲፈነገል ።

ላርቆስ
የኔስ ጸሎት ይኸው አደል ።

ንጉሥ
ማረኝ ሳይል ፣ ሳይወተውት ፣ በመርዙ ቅመም ሲቃጠል ፣
ስለበለስ ውሀ አምጡ ሲል ፣ በነፍሱ ጣዕር ሲዋትት
የምሰጠው ጽዋ አለቺኝ ፣ ውሀ አገኘሁ ብሎ ሲጋት
ይጠጣል ሌላ ሥራ ሥር
አንጨፍርሮ እሚከነትር ።

—ንግሥት ትገባለች—

ንግሥት
ገላውዴዎስ ፣ . . . ልጅ ላርቆስ ! እህትህ ! እህትህ !

ላርቆስ
ምን ሆነች ?

ንግሥት
ጉድ ፈልቶብህ ! ጉድ ፈልቶብህ !
በገዛ እጇዋ ተንደርድራ
ከድልድይ ላይ ተወርውራ ፤
ሆን ብላ አዘቅቱን ለይታ
ሞተችልህ ባሕር ገብታ ።

ንጉሥ
መቼ ? የት ?

ንግሥት
በኩሬዋ ሶራ ግርጌ ፣ ተንጠልጥላ የበቀለች
የበልግ አበባ ብጤ አለች ፤
ከወንዝ ውሀ እየታከከች ፣ ቅጠልዋ ሲል ብቅ ጥልቅ
ሽቅብ ከብርሃን ጮራ ጋር ፣ ውሀ ሥር ስታንጸባርቅ
ሥራ ሥሯ ተወሳስቦ ፣ ከሠርዶና ከቄጠማ
ግንድዋን ከፈሳሹ ጋራ ፣ ወደ መውረጃው አጣማ

እረኛና ውሀ ቀጂ ፣ እንደ ግብሯ ስም ሰይሟት
የገደል ማሚቶ ወጥመድ ፣ የውሀ ላይ ማማ ብሏት . . . .
ቀን ሲጠራት ሄዳ ኖሮ ፣ ቀጥፌ ልውሰዳት ብላ
ቁጠማና ሥራ ሥሩን ፣ እንደጨበጠች ገንጥላ
አበባዋን ተንተርሳ ፣ ተኝታለች ወፌ-ይላ . . . .
ለምሽት ሠረቀ ብርሃን ፣ ገጽዋን በእልልታ አፍክታ
ከተሰለበች ልቦና ፣ በፈነጠቀች ፈገግታ
ጸጥታው ተዋህዷት ፣ ጥንቱን ፣ እስክትመስል ፣ ሴህ ተሠርታ
ወፌ-ይላ ካበባው ጋር ፣ ተኝታለች ተዘርግታ ። . . . .

ላርቆስ
ወፌ-ይላ ፣ የናቴ ልጅ . . . የኔን እንባ መች ትሺያለሽ ? . . .
በባሕር ጥልቀት ተጠምቀሽ ! . . .
ኀምሌት ! ኀምሌት !
ወዮ አንተ ሴት !

—ይወጣል—

ንጉሥ
በይ ነይ እንሂድ አንቺ ሴት ፤ ብንከተለው ይሻላል
ወይ አይቷት በበቀል ሲሰክር ፣ ደሞ በኔ ይዞርብኛል ።

—ይወጣል—



## ገቢር ፡ አምስት

## ት ፡ ፩

—ሁለት መቃብር ቆፋሪዎች ይገባሉ—

አንደኛው
ይቺ በገዛ ፍቃድዋ ተንደርድራ መንግሥተ ሰማይ የተመሰገች ኮረዳ ፣ እንደ ክርስቲያን ወግ ፣ ሥርዓተ ፍትሐት ሊሰጣት ኖሯላ ?

ሁለተኛው
ቀጥተኛ ክርስቲያን ናት አልንህ ፤ እና አንተም ተግተህ ቆፍረህ መቃብሯን አቅና አልንህ ፤ አክሊሉን ፣ ጥምጥምና ቆቡን የደፋት የይቅርታ ቡራኬ ውን ደፍተውባታልና ፣ ብቁ ክርስቲያን ናት ተብሏል ።

አንደኛው
ቆይ ፤ ቆይ ፣ . . . ተጠየቅ !

ሁለተኛው
ልጠየቅ !

አንደኛው
. . . ነፍስዋን ለማዳን ስትከላከል ፣ ዘላ ሰጥማ ካልሆነ በቀር ፣ በተብሏል ብቻ መች ይሆናል በል ?

ሁለተኛው
ነፍስዋን ለማዳን ‘ ነው ’ ተብሏል ! . . . በል !

አንደኛው
አድኅነኒ እግዚአ እስመ ሐልቀ ሄር . . . በል እስቲ ፍረድ እግዜር ፤ እኔ ሆን ብዬ ብሰጥም ፣ እኔው አረኩት ማለት ነው ፤ አድራጐቱም ሦስት መልክ ፣ ሶስት አስተያየት አለው ፣ . . . ምንና ምን ነው ቢሉ ፣ አስቀ ድሞ መንቀሳቀስ፣ቀጥሎ ማድረግ፣ሶስተኛ ማከናወን ናቸው ይሏል፤ . . . . እስቲ እንግዲህ ፍረድ በል ፣ የዚህ የሁናቴ ፍች ፣ ሆን ብሎ መስጠም አደል ?

ሁለተኛው
አደል አባ ዘባርቄ ፤ በዚህ መንገድ እኮም አደል ፣ ወዴት ? ወዴት !

አንደኛው
ቆይ ፣ ቆይ ፣ ቆይ ! . . . ወንዙ እዚህ ጋ ነው እንበል ፤ ወዴት ወዴት ! እኮ ቆይ ምነው ሰዎች . . . ሰውዬው ይኸው እዚህ ነው እንበል . . . . በጀ ፣ እንግዲህ በገዛ እግሩ ፣ መጥቶ ሲከሰትበት ፤ በዚህም ሆነ በዚያም ሆነ ባሰኘው መንገድ ሆነ ፣ አድምጠኝ ልጅ ዘባርቄ ፣ መምጣቱ ያው መምጣት ነው ፤ . . . በጀ ፣ ወንዙ ግን ተንደርድሮ ፣ ሞልቶ ፣ አረፋ ገፍቶ ፣ ውጦ ቢሰለቅጠው ፣ ሰውዬውም እንደ ውሀው ጥራት ፣ ከበደሉ ንጡ ነው ፤ . . . .
እግዜር የሰጠውን ነፍስ ፣ በጀሽ አልበጀሽ ብሎ ፣ ራሱ አልቀጠፋትማ ።

ሁለተኛው
ደንቡ ይኸ ነው ባይ ነሃ ?

አንደኛው
እንዴታ መጠርጠሩስ ! የቤተ ክህነቱን ደንብ !

ሁለተኛው
ታድያን ይቺ ኮረዳ ፣ የጨዋ ልጅ ባትሆን ፣ በተስኪያን ቅጥር ግቢ ፣ አትቀበርም በላ !

አንደኛው
. . . ሁሉን አንተ ብለኸው ፣ እኔ ምኑን ልበለው ! . . . ይልቅስ እሚያሳዝነው ፣ ቤህ ዓለም ዓባይ ገነኑ ፣ ካልባሌው ጨዋ ይልቅ ፣ እንደ ፈቀደው ሊሰጥም ፣ እንደፈቀደው ሊሰቀል ፣ መደረጉ ሕግም አደል ። . . . . በል ሕግ ነው በለኛ ! . . . ተው ተው ባክህ በቃህ በለኝ ፤ ጐትጉተህ ዝም አትበለኝ ፤ . . . .
ታድያ እኛም ካካፋ ጋር ፣ እንገፋለን ተያይዘን ፣ ምንም እንኳ የመሠረት ፣ የጨዋ ልጆች ብንሆን ፣ እንደ አዳም እንደአባታችን ፣ ካካፋና ከዶማችን ፣ ከጥንት አንላቀቅ ብለን ፣ እንገፋለን ፤ እንጭራለን . .

ሁለተኛው
አዳም አባታችን ደሞ ፣ የጨዋ ልጅ ነበር በላ !

አንደኛው
ያውም ነፍጠኛ ወታደር ፤ ዶማ ይዞ የሚጋተር ።

ሁለተኛው
ደሞ ዶማ ከየት አምጥቶ ?
በለስ እንኳ የጐረሰው ፣ እንደጠጣ ዛፍ ላይ ወጥቶ !

አንደኛው
በመጽሐፍ ቅዱስ ካላመንክ አረመኔ ነኝ በለኛ ! . . . በመጽሐፈ



ኦሪት የሚያምን ፣ ይኸን አይጠራጠርም ። መጽሐፍ እንደሚናገረው ፣ አዳምም ቆፈረ ይላል ፤ መጽሐፉ ቆፈረ ካለ ፣ እንግዲህ አለመሣሪያ ፣ እንዴት ብሎ ይቆፍራል ! . . . ተጠየቅ !

ሁለተኛው
ልጠየቅ !

አንደኛው
. . . ሌላ ጥያቄ ጠይቄህ ፣ መልሱን ቶሎ ካልነገርከኝ ፣ ክርስቲያን ነኝ እንዳትለኝ ። ለነፍስ አባትህ ነግሬ ፣ ደግሞ ማስጠመቅ አለብኝ ፤ መልሱን ቶሎ ካላወቅህ ፣ ለነፍስ አባት ነው እምሰጥህ ፣ የክርስትና አባት ነው እምሆንህ ፣ የጡት አባት ነው እምሆንህ !

ሁለተኛው
ለምን ጀሀነም አትገባም !

አንደኛው
አስቀድመህ ጥያቄዬን መልስና . . . ተጠየቅ !

ሁለተኛው
ልጠየቅ አልኩህ !

አንደኛው
. . . ከውሀ ልክ አንጣፊውም ፣ ከገንቢውም ፣ ከለሳኙም ፣ ካናጢውም ፣ ማነው በል ቶሎ ተናገር ፣ የበለጠ ቤተ ሠሪ ?

ሁለተኛው
ቃጫ ገማጁ ይበልጣል ። ለምን ቢሉ ፣ እሱ የገመደው ፣ ለስንት ሺህ አንገት በቂ ነውና ።

አንደኛው
ይኸዋ እንደፈራሁት ፣ ክርስቲያንም አደለህ ሙት ። . . . ቃጫ ገማጁ ነው ካልከኝ ፣ ቃጫውስ ደኅና ይጠቅማል ፣ ሆኖም ጥቅሙ በአጥፊ ላይ ነው ። በአጥፊ ላይ ደኅና ይጠቅማል ። ታድያን ቴህ ከበተስኪያን ግንብ ፣ ቃጫ በለጠ ይባላል ! አይ የለም ተሳስተሃል ፤ . . . . በል ነገሬን መልስልኝ ፣ አፌን በዳቦ አብስልኝ ። . . . . ወይ እንደገና ትሞክር ? . . . ንቃ !

ሁለተኛው
'ከውሀ ልክ አንጣፊውም ፣ ከገንቢውም ፣ ከለሳኙም ፣ ካናጢውም ፣ የበለጠ ቤቱ ሠሪ' አደል ያልከው ?

አንደኛው
ነው ። አምጣው ማነው ? እሱን ካወቅህ ፣ ክርስቲያን ነህ ።

ሁለተኛው

ገባኝ ፣ ገባኝ ፣ ገባኝ ፣ ገባኝ ! . . .

አንደኛው

በል ።

ሁለተኛው

ጠፋኝ ።

—ጎምሌትና ሆራትዮስ ከሩቅ ሲገቡ ይታያሉ—

አንደኛው

መች አጣሁት ፣ መች አጣሁት ፣ ክርስቲያን አደለህም ሙት ። . . . . አታስብ ፣ አታምጥ ፣ በቃህ ፣ ግሣት ብቻ ነው እሚወጣህ ። . . . ግን ለማ ናቸውም ነገር ፣ ሁለተኛ ጨዋ መሃል ፣ ይኽን ነገር ብትጠየቅ ፣ በል ከኔ ተምረህ እወቅ ፤ . . . ከሁሉ ከሁሉ ልቆ ፣ የበለጠ ቤተ ሠሪ ፣ መቃብር ቆፋሪው ነው በል ! ማንም ከሱ አይስተካከል ። እሱ የሚገነባው ፎቅ ፣ እስከ ምጽዓት ነው የሚዘልቅ ። መቆፈር ብቻ አይበቃም ፣ የጨዋ ልጅ ነትክንም ፣ እወቅ ። . . . ሰማኸኝ ወይ ልጅ ዘባርቄ ፣ ያቺ እንኮዬ ጠምቃ ይሆን ፣ የኛን ሞኝ አንግሥ አረቄ ?

ሁለተኛው

. . . እንጃልህ ፣ ባሻ ዘባርቄ ።

—ይወጣል—

—አንደኛው ያንጐራጉራል—

አንደኛው

ተገረምኩልሽ ፣ ተደነቅሁልሽ
ደሞ እግር አወጣ ፣ ያምናው ሕመምሽ
ዛሬ ሌሊት በሕልሜ ፣ ፈጦ መጣልሽ
አማን ዘራፍ ብሎ ዳሌና ባትሽ ፤ . . . .
ተገረምኲልሽ ፣ ተደነቅሁልሽ . . . .

ጎምሌት

የት እንዳለም አይሰማው ማለት ነው በል ። መቃብር እየቆፈረ ሲዘፍን ?

ሆራትዮስ

‘የዕለት ልማድ ፣ አታውቅም ጋድ’ ፣ ሲሉም አልሰማህ ? ኑሮው በዚህ ከሆነ ምን ይሰማው ብለህ ነው ?

ጎምሌት

ነው ፤ እውነተኛ የልብ ፍስሐም ከእውነተኛ ላብ አትሸሽም ይላሉ ።



አንደኛው

—ያንጐራጉራል—

ተገረምኩላታ ፣ ተደነቅሁላታ
እንደእረኛ ቡጢ ፣ ጡቶችዋን አግታ
ደረቴን ፈንክቶ ፣ ጭዳ ጣለላታ . . . .
እሸሸ ገዳሜ ፣ እሸሸ ገዳሜ . . . .
አጅሬ መጫጨት ፣ አያ ሽምግልና
ተው አትገፋተር ፣ ያዘኝ ዝግ በልና
ትገላገላለህ ፣ ወይ ትጥለኝና ፤ . . . .
እሸሸ ገዳሜ ፣ እሸሸ ገዳሜ . . . .

ጎምሌት

ያም ዐፅም በጊዜው ተናጋሪ ምላስ ነበረው ፣ ይዘፍንባትም ነበር ፤ . . . . እንዴት እንደኮረት ይወረውረዋል በል ፣ የቃየልን መንጋጋ ያገኘ መሰለው ? ያኛው ደሞ ይኸኔ ያንዱ ፖለቲከኛ አገጭ ይሆናል ፣ ከእግዜር ጋር እሰጥ አገባ ሲል የኾለከ ። ወይም ያንዱ ያደባባይ አሽቃባጭ ይሆናል ።

ሆራትዮስ

ይሆናል ።

አንደኛው

—ዐፅም ይዞ ይዘፍናል—

ወፌ ወፌ ብረሪ ፣ ወፌ ብረሪ ፡
አንቺ የጭቃ ስባሪ ፣ ወፌ ብረሪ
ሰው መሆንሽን ንገሪ ፣ ወፌ ብረሪ ፤

ጎምሌት

ይኸ መንጋጋሙ ደሞ ያንዱ ያስለቸ ነገረ ፈጅ ይሆናል ፣ ወይ ፣ ያራጣ አበዳሪ ፤ . . . ሰሙኝ ወይ አያ ፣ የማን መቃብር ነው ይሄ ?

አንደኛው

የኔ ነው ጌታ ።

—ይዘፍናል—

ወፌ ምን አለች ? የወፌ ምን አለች ?
ሰው ነበርኩ አለች ።
ወፊቱ ብር ብር ፣ ወፊቱ ብር ብር
መንጋጋሽ ምን ታምር . . . .

አንደኛው
እንዲያው ድንገት አደጋ ነው አሉ ።

ጎምሌት
እኮ ፣ እንዴት ድንገት ?

አንደኛው
ቀልቡን ስቶ ነዋ ፣ ኋላ እንዴት ይታበዳል ?

ጎምሌት
እሱስ ነው ፤ ሆኖስ ሰበቡ የት ላይ ነው ይባላል ?

አንደኛው
የት ላይ - . . . ምድረ-ዴን ላይ ነዋ ! ሌላ የት ላይ ሊሆን ነው ? እኔ ሰላሳ ዘመን ሙሉ ላይዋ ላይ መቃብር ስቆፍርባት ያላቃታት ፣ ላንድ ለሱ ማበጃ አትበቃውም ብለህ ነው ጌታ ?

ጎምሌት
ነው ። . . . አንድ ሬሣ ተቀብሮ ፈጽሞ እስኪበሰብስ ስንት ጊዜ ይፈጃል ?

አንደኛው
እንደየሰዉ ዓይነት ይመስለኛል ፤ . . . ለያውም ፣ በቁሙ በስብሶ የሚ ቀበረው ይበዛል ። . . . እያት በል ይቺን ጉድ እይልኝ ፤ የማን ዐፅም ትመስልሃለች በል ?

ጎምሌት
እንዴት አርጌ ልወቀው ?


አንደኛው
እኔስ መቸም ቢሆን አልረሳት ፤ . . . ተጫውታብኝ እንዴት ብዬ ! እስቲ እንግዲህ አያችሁልኝ ፤ ያኔ ገና ለገና ሰውን ላስቅ ብላ ፣ እግብር መሐል አንድ አንኮላ ሙሉ ጠላ ጭንቅላቴ ላይ ትገለብጥ ! . . . አዬ ስታስቅ ! እከድዬ ! አደባባዩ ሁሉ የቀልድ ድርጭት የሚለው የንጉሡ አጫዋች ድንክዬ እኮ ነው ።

ጎምሌት
እውነት ? እውነት ይኸ ድርጭቴ ነው ?

አንደኛው
እንዴታ ! ያ ተረበኛ ! . . . ያቺ ሞላጫ ቀልደኛ ! . . .

—ይወጣል—





. . . . የምርምር እንቆቅልሽ ፣ ቋሚ ትንግርት መፍጠር ሲያምረው ፣ እግዜር አፈር ዘገነና ፣ እፍ ብሎ ሰው ነህ አለው !

ኀምሌት

አይ ድርጭቴ ! . . . ሆራትዮስ እረሳኸው ፣ ያንን ደገኛ ድንክዬ ? እንኮኮ ብሎ ያሳደገኝ ፣ እተከሻው ላይ ታዝዬ ፤ . . . አዬ መሞት ! ኧረ መሞት እንዴት ሩቅ ነው ? ከመቸው ሕልም ይመስላል ሰው ? . . . እንካ እንጉቻ ነው እያለኝ ፣ ሰፊ ጀሮውን ሲያስመኝ ! . . . እስቲ እንግዲህ አሁን የት አል ? የት አል የት አል ቀልዱ ? የት አል ዋዛው ? የት አል ያ ሳቂታ መንፈስ ? ምን ወሰደው? አዳራሽ መሐል ብቅ ሲል በሳቅ የሚያንከተክተው ? . . . የምርምር እንቆቅልሽ፣ቋሚ ትንግርት መፍጠር ሲያምረው፣እግዜር አፈር ዘገነና፣እፍ ብሎ ሰው ነህ አለው ! . . . አንድ ነገር ልጠይቅህ ሆራትዮስ ፣ ንሳ በል ታላቁ እስክንድርም በሕይወቱ ሳለ ያው እንዲሁ ነበር ማለት ነው ? . . . የለም ቆየኝ . . . ታላቁ እስክንድር በዚህ ዘመን ተወለደ ፣ በዚህ በዚህ ዕድሜው የነእገሌ የእነገሌን መንግሥትና ሠራዊት ድል መታ ፣ በዚህ ዘመን ሞተ ፣ በዚህ ሥፍራ ተቀበረ ፣ ማለት ለሱ ምን ትርፉ ነው ? . . . ግን እሱም ሆነ ቄሣርም ፣ አንዴ ከሞተ በኋላ ፣ አይጡ ቢቦጠቡጠው ፣ የክረምት ደለል ቢያጥበው ፣ ነፋሱ ቢቦረቡረው ፣ እንደዚያ መላውን ዓለም ፣ ለጥ ፀጥ ቀጥ ያረገ ፣ ንፋሱ ትቢያ ሲያረገው ፣ ለዐፅሙ እንኳ መከላከያ ፤ ሽንቁር መወተፍ ያቅተው ? መፈጠር ፣ መኖር ፣ መሞትም ፣ ሰማይ የሚያህል ቀልድ ነው ! . . . እኒያ እነ ማናቸው በል ፣ ሬሣ አጅበው እሚመጡት ? . . . ንጉሡና ንግሥቲቱ ባለሟሎቹም አሉበት ፤ . . . . ደሞ ማ ሞቶ ይሆን በል ? . . .

ሆራትዮስ

ለማናቸውም ዞር እንበል ።

—ዞር ብለው ይቆያሉ ። ንጉሡ ፣ ንግሥቲቱ ፣ ላርቆስ ፣ መኳንንቱና ጥቂት ቀሳውስት ሬሣ አጅበው ይገባሉ—

ላርቆስ

ይኸው ብቻ ነው ሥርዓተ ፍትሐቱ ?

ቄስ

. . . አይ ! . . . መቸስ ልጅ ላርቆስ . . . .

ላርቆስ

ይኸው ብቻ ነው ወይ !

ቄስ

. . . መቸም አዎ ፣ ይበቃታል ፤ በዚህ ላይ ትንሽ [ጾም ዝክር
አዘውትሮ መማጸኑ ፣ ይመስለኛል ደኅና ምክር ፤
የሱን ቸርነት ማን ያውቃል ፣ የሥሉስ ቅዱስን ምሥጢር ?



እንደ አሟሟቷስ ከሆነ ፣ . . . እኛማ ማን ዶሎን ቀድሞስ
እንኳን ፍትሐት ለአፍስ ቢሆን ፣ ይፍታሽ ለማለት ፣ ማን ደፍሮስ ?
ይኸውም የትእዛዝ ነገር ፣ ሆኖ ነው እንጂ ልጅ ላርቆስ
አቡነ ዘበሰማያት ፣ እንኳ ይባል ነበር ከቶስ ?
አሁንማ ምን ቀረባት ፣ ንዋየ ቅድሳት ወጥቶ
ሥንክሳሩ ተዘርግቶ
አስከሬኗ ደጀ ሰላም ፣ ቤተ መቅደስ ክበብ ገብቶ ፤
አይደፈር ድፍረት ደፍረን ፣ አይፈርስ ሥርዓት አፍርሰን
ደሞ እንሟገታለን ? . . .
ይልቅስ ይቅር ይበለን ።
በል አሁንም አናቁማት
ግብዐ ከመሬቱ ሆኖ ፣ ሟችቷን አፈር አቅምሳት ።

ላርቆስ

እኮ በቃት ማለት ነዋ ! ፍትሐት እንኳ የላትም ?

ቄስ

አይ እንግዲህ እኛ አናውቅም ።
እግዜር የሰጠንን ሕይወት ፣ ራሳችሁ አጥፏት አይልም
ውግዘቱን ይቅር ለማለት ፣ ቤተ ክህነትም አትደፍርም
ትእዛዙን ማስጸደቅ እንጂ ፣ ትእዛዙን አታስፈርስም ። . . . .
ሁኑ ብጹዓነ ወፍቱሐነ ረስየኒ ረሰይክሙ . . . .

ላርቆስ

አስገቧት መቃብሯ ውስጥ !
ነፍስሽን መልአክ ይቀበል ፣ ሥጋሽ ላፈርና ለምስጥ ።
የሚፈታሽ እግዚአብሔር ነው . . . ስማ አንተ ጠምጣሚ ገበዝ ፣
የምድር ባለ ሥልጣን ሆነህ ፣ ከቶ ስትለፈልፍ መዘዝ ፣
የራስህን ጉድፍ እይ እንጂ ፣ እንዲያውም አያስጋህ የስዋ ።
ከመላእክት ጐን ነው ፣ የእህቴ መቀመጫዋ !

ኀምሌት

እህቴ ! . . . ወፌ–ይላ ? . . .

ንግሥት

የልጄ ሚስት ናት ብዬ ፣ የኀምሌትዬ ሙሽራ
መቀደሚያን መች አውቄ ? ለካስ ለመሬት ተድራ !
የሙሽራ ወግ ሳታዪ ፣ ባፍላሽ ባበባሽ በዕድሜሽ ቅጅ
አፈር ትለብሺ አንቺ ልጅ ?

—ከደጅ ሙሾ ደርዳሪዋ ፣ ( ዋይ ወይ የት ትሄጃለሽ ፣ ) እያለች ስታወርድና አልቃሽ ሲቀበል አልፎ አልፎ ይሰማል—

ላርቆስ

ፍረደኝ ፍረደኝ አንተ ! ኸረ ማን ላይ ነው እሚከሰስ
ቀልቧን ሰልቦ የቀጠፋትን ፣ አንተ ቅጠፍልኝ በለስ !
ቆይ እንዴ ልሰናበታት ፣ ወዮ ወገን ፣ ወዮ አገር !
ኸረ ቀስ በሉ እባካችሁ ፣ አትችልም ይኸን ሁሉ አፈር
ቆዩኝ ላግዛት ባካችሁ ፣ እኔም አብሬአት ልቀበር !
ተዚያ ወዲያስ ደንታም የለኝ ፣ እንደ ተራራ ቢከመር
እኔም ልከተላት በቃኝ ፣ በቃኝ ብቻዬንም አልቀር !

—መቃብሩ ውስጥ ዘሎ ይገባል—

ጎምሌት
እኮ የማን ሰቀቀን ነው ! ምድር ሰማይ እስኪነቃ
እንደ ዛር ውላጅ ተይዞ ፣ የሚወድቅ የሚወቃ
የማን ጭንቀት ! የማን ሲቃ !
ልቡ እስከዚህ የቆሰለ ! አብሯት ሊሞት የፈለገ
ልቅሶው ሰማየ ሰማይን ፣ በአድናቆት እርጭ ያረገ !
ማነው ! . . .
አዎን እኔ ነኝ እወቀኝ
የምድረ-ዴኑ ጎምሌት ነኝ !

ላርቆስ
አንተ ሌት !

ጎምሌት
ኤድያ አትተናነቀኝ ፣ ወዲያ እጅህን ከላዬ ላይ !
የማን አልኩ ባይ ! አስመሳይ ! . . .
እንዳንተም ፈልቶ ባይታይ . . . .
ደሜ ሞት እንደፀነሰ ፣ ባለማወቅህ እንዳይሆን
ድፍን እሳተ ገሞራ ፣ በቀን የተዳፈነ እቶን . . . .
ወዲያ ውሰድ የኋላ ቀን ! ማጫር በቅቶታል የኔ ጐን !

ንጉሥ
ወደዚያ አላቋቸው በሉ
ሬሣ ላይ አይታገሉ ።

ንግሥት
ጎምሌት . . . ጎምሌት !

ላርቆስ
ደምህን ነው እምጠጣው !



ጎምሌት
እኮ ቅዳና ሞክረው
ምሬቱን ቀምሰህ ባታውቀው !

ንጉሥ
ባክህ አብዷል ወዲያ ተወው ።

ላርቆስ
ደምህን ነው እማፈስሰው !

ጎምሌት
ተው ያንቅህል ፣ ባታውቀው ነው ።
ያንተ ሐዘን እንደ ግንድ ሆኖ ፣ የኔ እንደ ተቀጥላ
ሊጣልበት ያንተ ጥላ ?
ፍቅሬን አድበስብሰህ ሊፈዝ ?
አጥላላኸውና ሊቦዝ ?
ሕልውናዬን ሠርዘህ
በገጼ ጽላት ተጎድፈህ . . . .
ምን አሰኘህ ! ምን አሰኘህ !
ተው ወዳጄ ተው ላርቆስ
አትሁነኝ ጦስ ! . . .
የነገሩህ ምን ነገሩህ ? እንዲህ በፍቅሬ ያሳመፁህ ?
የምን መተት አጐረሱህ ! . . .
እንኳን አንድ አንተ ይቅርና ፣ ቢንፈቀፈቅ ሰባ ወንድም
የኔን እጦት አያጣትም ፤
የኔን ቁስል አይቆስልላትም ፤
የኔን መውደድ አይወዳትም ፤
የኔን ሞት አይሞትላትም !
ተው ወዳጄ ተው ላርቆስ
አትሁነኝ ጦስ !

ንጉሥ
እዚያው ያዘው ሆራትዮስ
አንተም ና ሂድ ልጅ ላርቆስ ፤
ጠብስ ቢሉ እንደዚህ ነው ? ተሸፍነን በሐዘን በርኖስ ? . . .
ቻለው ብዬህ ፣ ልጅ ላርቆስ . . . .

—ይወጣሉ—

ት ፡ ፱

—ጎምሌትና ሆራትዮስ ይገባሉ—

ምሌት
ያለኝን ታስታውሳለህ ? . . . ተወው ፣ ተወው አብዱል አለ . . . .
‘ ሙቅ ያኝካል የታደለ ’ . . . .
አባቱን በቀን አፍኖ ፣ እናቱን በቀን አርክሶ
እኔን በቀን አልከስክሶ
የሰው ሰው ልኮ አስገድሎኝ ፣ ደም መላሹን ከኔ እናክሶ
የምጨኛት ወፌ-ይላን ፣ ቀጥፎ ፣ ፊቴ አፈር አልብሶ
ወው አብዱል አለ
ታደለ ! . . .
ያ ወደኛ እሚመጣውን ፣ ታውቀዋለህ ? ማን ይባላል ?

ሆራትዮስ
የባዕድ አገር ጀግና ነው ፣ ፈረሰኛ ነው ይሉታል ፤
ደሞ እዲስ ባለሟል ሆኖአል ።

—ባልደራስ ከልሉ ይገባል—

ባልደራስ
እንኳን ልዑል እግዚአብሔር ፣ ለሚናፍቋት ሀገርዎ ለምድረ-ዴን አፈር ያበቃዎ ልዑል ጎምሌት ።

ጎምሌት
አቤት ፣ አቤት ? . . .

ባልደራስ
እንኳን ልዑል እግዚአብሔር . . . .

ጎምሌት
ሰምቻለሁ ፣ እግዜር ይስጥህ ፤ . . . ይቺን ዝንብ ታውቃታለህ ?

ባልደራስ
አቤት ? አቤት ?

ጎምሌት
ያገርህ ዝንብ ይሻልሃል ፤ . . . አየህ ፣ ይቺ ነገር ፣ አገር ተርፏት ውሀ ተርፏት ፣ ለምለም ተርፏት ፣ ሁሉ ተርፏት ፣ . . . ከግብር ገበታ አት ጠፋም ፤ የሥራ ቤት ወጥ መልከፏን ፣ ትራፊ ላይ መልከስከሷን ፣



ሞዳ ፣ ለወግ መዋረዷን ፣ ቁሻሻ ላይ መርመጥመጧን ፣ ተግባር አርጋ ች ጥምቧን ።

ልደራስ
. . ልዑል እምልዑላን ጎምሌት ፣ አንድ ጊዜ ቢፈቅዱልኝ ፣ ከግርማዊ ገላውዴዎስ ያመጣሁት መልእክት እለኝ . . . . .

ምሌት
ኮ አምጣው በል !

ባልደራስ
ስለፈቀዱልኝ ምሥጋናዬ የልዑልነትዎ ነው ፤ . . . ትንሽ ይወብቃል ልበል ? . . .

ጎምሌት
የፈለከውን በል ፣ ብቻ እምታመጣውን አምጣው ።

ባልደራስ
ነው ፤ . . . ከልጅ ላርቆስ ጋር መቸም አብሮ አደግ ወዳጆች ናችሁ ፤ አጫወተኝ ፤ ጃንሆይም አጫወቱኝ ።

ጎምሌት
አጫወቱህ ?

ባልደራስ
እንዲህ አርጐም አብሮ ማደግ ፣ እንዲህ አርጐም ወዳጅነት ፣ አገር ያወቀው ነው ብለው ። የልጅ ላርቆስ ወዳጅ መሆን ፣ የጨዋ ልጅ የትልቅ ዘር ፣ የጎበዛዝ መጨረሻ ፣ የወጣለት የጦር ጠቢብ ፣ ተብሎ ያለቀለት ወንድ . . . .

ጎምሌት
ታድያስ ፣ ታድያስ ?

ባልደራስ
ሳንጃ ብረት ነው ይባላል ። መሣሪያ ጦር ነው ይባላል ፤ ለልጅ ላርቆስ ጀግና ብቻ አይ ሲዋሐድ ግን ፣ ከእጁ ይልቅ ይቀርበዋል ፤ . . . ላርቆስ ጀግና ብቻ አይ ደለም ፣ ለሰይፍ ሞያ ጠቢብ ነው ፣ ትንግርት ነው ፣ ተአምር ነው ፣ ትር ኢት ነው ፣ ያይን ሲሣይ ፤ . . . ታድያ ጃንሆይ ይኸን ጥበብ ፣ እንዴት ባደርግ ነው እማየው ፣ ትንግርቱን እምካፈለው ፣ ብለው ጭንቅ ቢሉ በት ፤ ልጅዎ ልዑል ጎምሌት ፈቅዶ ፣ ለሞያው አጣማጅ ሆኖ ፣ መልክ እንዲሰጠው ቢገጥመኝ ፣ ለወጉ ያህል ቢቋቋመኝ ፣ ይኸን ችሎታዬን ለርስዎ ፣ ባደባባይ ለማሳየት ፣ ወደ ኋላ የማልል ነኝ ፣ ብሎ ፣ የቡድኑም

ጎምሌት

ከሆነኝ እሞክራለሁ ፣ ያለበለዚያም አፍራለሁ ፣ ግን 'አባቴ' ተወራርደው ፣ ምን ብዬ አሳፍራለሁ ፣ ለትርኢት ያህል እገጥማለሁ ፣ ብሏል በልልኝ ወዳጄ ።

ባልደራስ

ወዲያውም ንግሥት እናትዎ ፣ ' ልጅ ላርቶስን አስቀየምከው ፣ ልጄ ይቅርታ ጠይቀው ፣ ' ብለህ ንገር ብለውኛል ።

ጎምሌት

. . . እዎን እውነቷን ብላለች ፣ ስህተትን ማመን ይበጃል ፣
አይከፋም ይቅር መባባል

ባልደራስ

ለልዑልነትዎ የተገባ፣ሰላምታዬን እያቀረብኩ፣ግጥሚያው ላይ እስከንገናኝ እሰናበትዎታለሁ ።

—ባልደራስ ይወጣል—

ሆራትዮስ

መረታትክን አውቀኸዋል ?

ጎምሌት

. . . ማን ያውቃል ? . . . ሃፍረቱ እንደሁ ተዋህዶኛል ።
ሃፍረት እንጂ ምን ይመጣል ? . . . ልቤ ግን ብቻውን ይዞአል . . . .

ሆራትዮስ

እማይሆን መሆኑን ካወቅህ ፣ ሂጂ ባስቀረው ይሻላል ። . . . .

ጎምሌት

አዬ ሆራትዮስ አይሆንም ፤
ያው ሃፍረት ነው ቃል ማፍረስም ። . . . .
ድምቢጥ እንኳ ከፍጥረታት
ስትወድቅ ረቂቅ ምክንያት አላት
ጌታ የመዘገበላት ፤ . . . .
ጥሪው አሁኑን ከሆነ ፣ ቀጠሮ የለም ማለት ነው ፣
ቀጠሮ ከሌለ ደሞ ፣ ጥሪው አሁን ነው ማለት ነው ፤
ደሞ አሁን አደለም ቢባል
ጥሪው ይዘገያል እንጂ ፣ በቀጠሮው ጊዜ ይመጣል ።
ዋናው ነገር መጠንቀቁ
ተዘጋጅቶ መጠበቁ

ለሰው አልተባለምና ፡ ቀኑን በቅድሚያ ማወቁ ።
ቀጠሮ ፡ የጠሪ ምሥጢር ፡ ለተጠሪ መደበቁ . . . .

—ይወጣሉ—

—እምቢልታና ነጋሪት ይሰማል ። ጋሻ ጃግሬዎች ፡ የእልፍኝ አስከልካዮች ፡ ባለሟሎች ፡ የጦር መኰንኖች ፡ ንጉሡንና ንግሥቲቱን አጅበው ይገባሉ ። ጎምሌትና ላርቆስ ጥሩር አጥልቀዋል ። አንድ ማብረጃ ጽዋና የጦር መሣሪያዎች ከያዘው ጠረጴዛ ላይ ፡ ባልደራስ ክሊሉና ሆራትዮስ ጦርና ጋሻ ያደራጃሉ—

ንጉሥ
በል ና እስቲ ጎምሌት ልጄ ፡ ይቅር ለእግዜር ተባባሉ ፤

ጎምሌት
ላርቆስ ፡ ወዳጄ ፡ ከልብ ፡ ይቅር ለእግዜር ትለኝ ይሆን ?
አስቀይሜሃለሁ አዎን ፤ . . . .
ጀምበሬ ስትጠልቅ ፡ ነፍሴ ፡ በሰቀቀን ባልቃተተ
ከቶ እንደበቴም ባልሳተ ፤ . . . .
ይቅርታህን የጨዋ ልጅ ፡ ወግ ነው ብለህ ፡ አትወርውርልኝ
ይልቅ የሰው ልጅ ጥሞና ፡ ነው ብለህ ፡ አበርክትልኝ ።
መቸም አልቀረህ ሳታውቀው
ውስጤን ያበሰለኝ ቁስል ፡ ድንገት አመርቅዞብኝ ነው ።
ክብርህንና ስምህን ፡ ያሳደፈ አፍ እልፊቱ
የኔ ሳይሆን ፡ ነው የዕብደቴ ። . . . .
ታድያስ ላርቆስን የገፋ ፡ የጎምሌት አንደበት ነው ከቶስ ?
ፈጽሞ አደለም ላርቆስ ፤
ጎምሌት ቀልቡ ተመንጥቆ ፡ ልቡና መች ኖሮት ቀድሞስ ?
እንግዲያ ጎምሌት ያለቀልቡ ፡ ላርቆስ ወዳጁን ቢያስቀይም
አጥፊው ጎምሌት አይባልም ።
ምነው ቢባልም በውነቱ
ጎምሌት ሳይሆን ፡ ነው ዕብደቱ ።
ስለዚህ እንኳንስ ሊገፋ ፡ በሱም ግፍ ተውሎበታል
ዕብደት ወዳጁን ዘልፎበት ፡ ለራሱም ጠላት ሆኖታል ፤
እንግዲያስ ወዳጄ ላርቆስ ፡ ስታገል ዕብደት ጠላቴን
የሠነዘርኩት መሣሪያ ፡ ግቡን ስቶ ፡ አንተን ወንድሜን
መትቶብኛልና ድንገት ፡ እባክህ አትቀየመኝ ፡
በችሎት ፊት ተማጸንኩህ ፡ በችሎት ፊት ይቅር በለኝ ።

ላርቆስ
ይህ ይቅርታ የኔ ሳይሆን ፡ የፈጣሪ ይቅርታ ነው
በሱ እጅ ነው እምተወው ፡
ይቅር ባይ እኔ ነኝ ብሏል ፡ የሱ ፍቃድ ፍቃዴ ነው ።



ማለት ፡ በዚች ባሁን ሰዓት ፡ አውቃለሁና የሱን መንገድ
በቀሌን እንድበቀላት ፡ በሙሉ ልቡ እንደሚፈቅድ
እስከዚያ ድረስ ግን ጎምሌት ፡ ከሃሳቡ ገለልተኛ ነኝ
ይኸ የጨዋ ልጅ ቃሌ ነው ፡ ሽንጐ መርምሮ እስኪፈርደኝ ፤
ስሜና ክብሬ አድፈልና ፡ ፍርዱን ለነሱ ትቻለሁ
በይቅርታው ግን አልገባም ፡ ይኸው እጄን ታጥቤአለሁ ።
እስከዚያውም ቃል ልግባልህ ፡ ያላዋቂ ፍርድ ሳልሰጥ
ያበረከትክልኝን ፍቅር ፡ ተቀብዬ ለማስቀመጥ ።

ጎምሌት
ፍቅሬን ብቻ ካወቅህልኝ ፡ እኔም ሌላ አልጠይቅህ
ይቅርታውን ሽንጐ እስኪፈርድ ፡ እንዳከበርከኝ ያክብርህ ፤ . . . .
በቃ ትርኢቱን እንጀምር
የጦሩን ሥርዓት ውድድር
ጫወታችንን በፍቅር ።
ና በል ፤ . . . .

—ይሻኮታሉ—

ላርቆስ
እንካ ጦርክን . . . .

ጎምሌት
በል እንግዲህ አይተህ ማረኝ
እኔ መቸም ለጥበቡ ፡ ሙከራ እንጂ ባይተዋር ነኝ ፤
ብታሳፍረኝም እንኳ ፡ በመጠኑ አሳፍረኝ ፤ . . . .

ላርቆስ
ተው ጌታዬ አታንጓጠኝ ፤

ጎምሌት
ወዳጄ ሙት ፡ ተው እመነኝ ፤

ንጉሥ
በል ባልደራስ ፡ ይጀምሩ ፤

ባልደራስ
ሶስት ዙር ነው ውድድሩ ፤
ሶስቱንም መጋጠም አለ ፡ ሳያቋርጥ በድምሩ ።
ሕጉን መቸም ታውቃላችሁ ፡ ስትወጉ ፡ ስትሠነዝሩ
ለምልክት ያህል እንጂ ፡ እንዳታልፉ ከድንበሩ ።
ተጠንቀቁ ፡ ለማሸነፍ ስትሞክሩ

ሥርዓቱንም እንዳትሰብሩ
ቅልጥፍና እንጂ ኃይል የለም ፥ ኋላ ደሞ እንዳታመሩ ።
በሉ ፥ ሁለታችሁም በርቱ
ሰውነታችሁን አፍታቱ ።

ላርቆስ
. . . ምነው ይኸ ከበድ አለኝ
በል ያንኛውን ጦር ስጠኝ ።

ንጉሥ
ሰማህ አንተ ሆራትዮስ ፤
ኀምሌት ልጄ እንዳሸነፈ ፥ ትእዛዝ ስጥ መድፍ እንዲተኮስ ።

ኀምሌት
ኧረ እኔ እንጃልኝ አላውቅም ፤

ንጉሥ
ግድ የለም እኔ ተስፋ አለኝ ፥ ያውም አልጠራጠርም ። . . . .
ደሞ የምን መጠራጠር !
ባልደራስ ፥ ይልቅ ይጀመር ።

— እምቢልታ ይነፋል ፤ ከበሮ ይጐሰማል—

ባልደራስ
በሉ ፥ ሥርዓት እንዳትሠብሩ . . . .
አንድ ! ሁለት ፥ ጀምሩ !

— ይጀምራሉ—

ኀምሌት
አንድ አለብህ ።

ላርቆስ
በጭራሽ !

ኀምሌት
ዳኝነት !

ባልደራስ
ነው ፤ . . . ለልዑል ኀምሌት የመጀመሪያው ዙር ድል !

ላርቆስ
ደግ ፥ እንቀጥል ።



ንጉሥ
ቆይ ! . . . እሰይ የኔ ግሥላ ፤ ይቺ ያባቴ ያልማዝ ቀለበት ያንተ ትሁን ፤

—አልማዙን ጽዋው ውስጥ ይጥልና—


እንካ በል አብረሃት ከዚች ከቀዝቃዛዋ ጐንጨት
ስጠው አንተ ። በል ፤ . . . ና

— ከበሮ ይጐሰማል ። እምቢልታ ይነፋል—

ኀምሌት
ቆዩኝ አንዴ ይቺን ልወጣት ፤ . . . ና በል ፤

— ይቀጥላሉ—

አለብህ ።



አንድ አለብህ !

ላርቆስ
አዎ ! . . . መቼ ካድኩህ !

ባልደራስ
ነው ፤ . . . የሁለተኛው ዙሪያ ድል ለልዑል ኀምሌት ።

ንጉሥ
እሰይ ! ልጃችን ረታልን አደል ገርትረድ !

ንግሥት
. . . ምን ሰውነቱ አልቆ ፣ ሳስቶ ፤ . . . እንካ መሃረቤን ላብክን አብ ስበት ኀምሌት ፤ . . . አንተ በታገልክ ልጄ ፣ ባንተ ሥጋት እኔን ጠማኝ ፤ . . . .

ንጉሥ
ተይ አትጠጪ ገርትረድ !

ንግሥት
ምነው ?

ንጉሥ
የ—የኀምሌት ነው አትጠጪበት !

ንግሥት
ታድያ የልጄን ብጠጣ ፣ አይከለክለኝ ፤ . . . .

—ትጠጣለች—

ንጉሥ
. . . ኧረ ! . . .

ንግሥት
ና የግንባርክን ላብ ልጥረግልህ . . . .

—እምቢልታ ይነፋል ፤ ከበሮ ይጐሰማል ፡
ሦስተኛውን ዙር ይጀምራሉ—

ባልደራስ
ያሁኑ ዙር እኩል በኩል ነው ። እንደገና !

—ይቀጥላሉ—

ላርቆስ
. . . ይቀመስልህ !

—ጦራቸው ይቀላለፋል ። ኀምሌት ይቆስላል ። ላርቆስም ይቆስላል—

ንጉሥ
በቃ አላቋቸው ተማርረዋል ።

ኀምሌት
ኧረ ግድ የለም ፣ . . . እንቀጥላለን ፤

—ይቀጥላሉ ። . . . ላርቆስ ተወግቶ ይወድቃል ። ንግሥቲቱም ተመርዛ ትወድቃለች—



ንግሥት
. . . መጠጡ መ—መጠጡ ኀምሌት . . . ጽ—ጽዋው ልጄ . . .
መ—መርዝ ነው . . . .

—ትሞታለች—

ኀምሌት
መርዝ ! . . . ዐመፅ ! ዐመፅ ሸተተ ! . . . ዝጋ በሩን !
አውጧት አሁን ! አሁን ! !

ላርቆስ
ኀምሌት ፣ ኀምሌት ፣ አንተም ሟች ነህ
ሟች ነህ ፤ ምንም ጊዜ የለህ ፤
የግማሽ ሰዓት እንኳ ዕድሜ
የለህም ኀምሌት ፣ የለህም ፣ ተመርዘሃል ወንድሜ ።
የያዝካት መሣሪያ ላንቃ
በመርዝ ቅመም ተዘፍቃ
እንኳን ወግታና ብትጭር
ወድያው ነው እምታንጨፈርር . . . .
ላንተ ተብሎ ነበርዩ ፣ ካጥማጅህ ጋራ ያጠመድኩ . . . .
ለኔ መትረፉን መች አወቅኩ . . . .
ይኸው ካንተ ጋር ተነደፍኩ
ተለበለብኩ ፣ ተለበለብኩ . . . .
እናትህም ያው መርዝ ነው ፣ አሁን ጠጥተው የሞቱት
ንጉሡ በበጠበጡት ፤
አትልቀቅ ንጉሡ ናቸው ፣ የሁለታችንም ወጥመድ
ሌላ ባላንጣ የለህም ፣ ከንጉሡ ራስ አትውረድ ። . . . .
ኀምሌት ባክህ ይቅር በለኝ ፣ አንዴ ይቅር በለኝ እኔን . . . .

ኀምሌት
ዓሜን ! ዓሜን ! ዓሜን ! ዓሜን !

—ንጉሡን ወግቶ ይገድላል —

ንጉሥ
. . . ያ—ያዙት ፣ ያ—ያዙ — እ — እንዳይወጣ . . . .

ኀምሌት
እንካ ይቺን እንካፈል ፣ ጠጣ ፣ ጠጣ ፣ ጠጣ ! . . .

ላርቆስ
. . . ባ— ባክህ ይቅር በለኝ እኔን ፣

ኀምሌት
ዓሜን ።... ይቅር ይበልህ እግዚአብሔር ። . . . ሆራትዮስ ያዘኝ እጄን . . . .
አንተ የዚህ ሁሉ መተት ፣ ድዳ ተመልካች በመሆንህ
አያሌ ግዳጅ አለብህ ፤ . . . .
ይልቅስ ወዳጄ ከሆንክ ፣ እኔን መከተልህ ቀርቶ ፣
ስሜ እንዳይሞት ንገር ፣ ከቶ . . . .

ሆራትዮስ
ተው ጌታዬ ፍቀድልኝ ፣ ብቻዬን አልቅር በከንቱ
ከዋንጫህ አካፍለኝና ፣ ልካፈልህ ከመሞቱ . . . .
አይሆንልኝም መቅረቱ
አብረን ኖረን ፣ አብረን መሞት ፣ ይሻላል ወገኛነቱ ። . . . .

ኀምሌት
ሆራትዮስ ፣ አንት ደካማ ፣ . . . እንግዲያማ ለምን ኖርኩት ?
አንተ ሸሽተህ ከተከተልክ ፣ እኔም ልሙት ? ስሜም ይሙት ? . . .
በል ጽዋዬን ለኔ ስጠኝ ፣
ጠማኝ ፣ ስጠኝ ፣ ስጠኝ ፣ ስጠኝ ፣ . . . .
ተከትለህ እንዳትከደኝ
ከስሜስ ጋር እንዳትቀብረኝ ። . . . .
ምንድነው በሉ ይኸ ሃኬት ፣ እንደሞት ከሩቅ እሚጮህ ? . . .

ባልደራስ
የልዑል ፎርጠንብሮስ ነው ፣
ምድረ-ፖላንድን ድል አርጎ ፣ እግረ መንገዱን የሚያልፈው ።

ኀምሌት
. . . ሆራትዮስ እግዜር ያጥናህ ፣ በርታ ፣ በርታ ፣ በርታ ፣ . . . .
ፎርጠንብሮስን ፣ አደራ በለው ፣ ዴን እንዳትመታ ፤
በሃኬት እንዳትፈታ ።
ለኔማ ከእንግዲህ ወዲያ ፣ ፀጥታ ብቻ . . . ፀጥታ . . . .
ለምድረ-ዴን ብለህ በርታ ፣ በርታ ፣ . . . በርታ . . . .

—ይሞታል—

ሆራትዮስ
. . . እንቺ ልጅሽን ምድረ-ዴን ፣ . . . አንድ ልጅሽ ተከተተ . . . .
አገር ! ሰው ሞተ ፣ ሰው ሞተ ።

—ፎርጠንብሮስ በድል አድራጊነት ፣ እምቢልታ እያስነፋና ከበሮ እያስጐሰመ ይገባል—



ፎርጠንብሮስ
ሰውም የለ ልበል ባገር ?

ሆራትዮስ
. . . ሞት እንጂ ኧረ ሰውስ ነበር ።



ጦር ሜዳ ቀርቶ በአዳራሽ ፣ ይኸ ሁሉ አስከሬን ሲያጥጥ
ሁሉ አለቦታው ያጣል ቅጥ ፣ . . . .

ፎርጠንብሮስ
ሞት ? . . . አዎን ፣ ይኸው አ'ነድ ራሱን
እየሁት ገብቶ መንገሡን ፤
በነገሥታት ላይ መንገሡን
በልዑላን ላይ መንገሡን ፤
ኧረ ስንቱን ! ስንቱን ! ስንቱን !

ሆራትዮስ
ልዑል ፎርጠንብሮስ ፈቅደው ፣ ሬሣውን ብናስነሳ አሁን
ለርስዎም ፣ ላላዋቂውም ሕዝብ ፣ አሳውጃለሁ ታሪኩን ።

ፎርጠንብሮስ

. . . ለጀግና ሞት ክብርም ቢባል
የሱ አሟሟት ያሳዝናል ። . . . .
ታድያን የሬ አመጣጥ እንኳ ፣ አንድ ያባቴን የደም ድንበር
ከምድሬ-ዴን ግዛት ላይ ፤ ዛሬ ለመፋለም ነበር ፤

ሆራትዮስ

ስለሱም እንዳዋይዎ ፣ ሟቹ ሰው አደራ ብሏል ።

ፎርጠንብሮስ

. . . አራት ፊታውራሪዎቼ ፣ የኀምሌትን አስከሬን በክብር
ንሱ ፣ አሁን አዘጋጁ ፣ ለሚገባ ሥርዓተ ቀብር ፤
ለጐበዛዝ በሚገባ
ለወንድ ልጅ በሚገባ
በተሟላ ሥነ ሥርዓት ፣ ጦሩ የነገሥታት ደንብ
በጀግና አቀባበር ይቅረብ ፤
በዝናው መስከሯልና ፤ ጀግና መሆኑን የወጣለት
እምቢልታ ፣ ከበሮና መድፍ ፣ አስተጋብተው ይመስክሩለት ። . .
ጦር ሜዳ ቀርቶ በአዳራሽ ፣ ይኸ ሁሉ አስከሬን ሲያጥጥ
ሁሉ አለቦታው ያጣል ቅጥ ፣ . . . .
ለኀምሌት ይተኮስ ፣ ትእዛዝ ስጥ ።

—እምቢልታ ይነፋል ፣ ከበሮ ይጐሰማል ፣ መድፍ ይተኮሳል ፤ የኀምሌትን አስከሬን ተሸክመው በሰልፍ ሲወጡ የኪራራይሶ ሕብረ ዜማ ያስተጋባል—

ተፈጸመ ።